

የአገሪቱ የታሪክ ዘውድ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ የሰጣቸው ግርማና ሞገስ እንዲህ ነበር

ጥያቄውንም መልሱንም አዳፍኔ እያዳፈነ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ቀጠለ፤ ይሄ ትውልድ አለፈና ሌላ ትውልድ መጣ፤ 1966 ዓ.ም. አሁን ደግሞ የጦር ሠራዊትና የዓየር ኃይል አንድ ላይ ሆነው! ያን ጊዜ የአዳፍኔ ብልሃቱ ሁሉ ጠፋ፤ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እኔ ነኝ ባለተራ ብሎ በአዳፍኔ መንበር ላይ ተቀመጠ፤ ደርግ መቶም ሆነ መቶ ሃያ መንግሥቱን አዳፍኔ ከመሆን አልገቱትም፤ ዝምብም አልገድል እያለ ብዙ ሰዎችን ጨረሰ፤ ጄኔራል አማንን ከስድሳ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች ጋር ያለምንም ፍርድ ረሸነ፤ ተምረዋል የሚባሉትንና ጥያቄ የሚጠይቁትን ጓደኞቹን አንድ በአንድ ጊዜ እየጠበቀ ቀጫቸው፤ ብዙ በጣም የሚበልጡትና ሊያስተምሩት የሚችሉ ሰዎችን በትዕቢት ጨረሰ፤ የመጨረሻው ጥፋቱ በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ የሚባሉትንና በትምህርትም በልምድም ለኢትዮጵያ ይጠቅማሉ የተባሉትን ጄኔራሎች በንዴትና በደም ፍላት ከፍርድ ውጭ አሰቃይቶ ገደላቸው፤ እዚህም ላይ ጥያቄ አለ፤-

1. የደርግ አባሎች ምን ጥያቄ አነሡ?





2. የደርግ ሠራዊትና የዓየር ኃይሉ ምን ጥያቄ አቀረቡ?
3. ደርግ ከስዒረ መንግሥት ሙከራው ምን ተማረ?

ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ከዚህ በታች የሚታየው ፎቶግራፍ እንኳን አጼ ኃይለ ሥላሴን ለሚያውቋቸውና ለማንም በጣም የሚያሳዝንና ልብን የሚሰብር ነው፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ውርደት አግዝፎ የሚያሳይ ነው፤ ሦስት ያህል ትውልዶችን የገዙ ንጉሠ ነገሥት፣ በስንት ዓይነት ቤተ መንግሥት የተስተናገዱ ሰው፣ ከስንት ታላላቅ የዓለም መሪዎች ጋር የተወያዩ መሪ፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአፍሪካ ዕጣ-ፋንታ ላይ በብዙ መንገድ ተጽእኖ ያደረጉ ትልቅ ሰው፣ ከቤተ መንግሥታቸው በአንድ ትንሽ ቮልክስዋገን ተይዘው ወደአራተኛ ክፍለ ጦር ሲወሰዱ ሕዝብ ‹‹ሌባ! ሌባ!› እያለ



*የአገሪቱ የታሪክ ዘውድ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ የሰጣቸው ግርማና ሞገስ እንዲህ ነበር*

ጥያቄውንም መልሱንም አዳፍኔ እያዳፈነ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ቀጠለ፤ ይሄ ትውልድ አለፈና ሌላ ትውልድ መጣ፤ 1966 ዓ.ም. አሁን ደግሞ የጦር ሠራዊትና የዓየር ኃይል አንድ ላይ ሆነው! ያን ጊዜ የአዳፍኔ ብልሃቱ ሁሉ ጠፋ፤ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እኔ ነኝ ባለተራ ብሎ በአዳፍኔ መንበር ላይ ተቀመጠ፤ ደርግ መቶም ሆነ መቶ ሃያ መንግሥቱን አዳፍኔ ከመሆን አልገቱትም፤ ዝምብም አልገድል እያለ ብዙ ሰዎችን ጨረሰ፤ ጄኔራል አማንን ከስድሳ የአጼ ኃይለ ሠላሴ ባለሥልጣኖች ጋር ያለምንም ፍርድ ረሸነ፤ ተምረዋል የሚባሉትንና ጥያቄ የሚጠይቁትን ጓደኞቹን አንድ በአንድ ጊዜ እየጠበቀ ቀጫቸው፤ ብዙ በጣም የሚበልጡትና ሊያስተምሩት የሚችሉ ሰዎችን በትዕቢት ጨረሰ፤ የመጨረሻው ጥፋቱ በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ የሚባሉትንና በትምህርትም በልምድም ለኢትዮጵያ ይጠቅማሉ የተባሉትን ጄኔራሎች በንዴትና በደም ፍላት ከፍርድ ውጭ አሰቃይቶ ገደላቸው፤ እዚህም ላይ ጥያቄ አለ፤-

1. የደርግ አባሎች ምን ጥያቄ አነሡ?



*ቀልብ ሲገፈፍ! በአራተኛ ክፍለ ጦር እስረኛ ሆነው*

የሸኞቸው፣በአራተኛ ክፍለ ጦር እንዲህ በሚያሳዝን ሁኔታ ታስረው የቆዩና የሞቱ (የተገደሉ) ሽማግሌ፣ ተገቢ ቀብር እንኳን ያላገኙ የመጨረሻው ንጉሠ ነገሥት ናቸው፤ ፎተግራፉ የሚያሳየው የግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ፣ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያን መክሸፍ ነው፤ የሶስት ሺህ ዓመታት የኢትዮጵያ ታሪክ መክሸፍ ነው፤ ከአክሱም ሐውልትና ከላሊብላ ቤተ ክርስቲያኖች ወደኀጆ ከመውረድ የማይለይ መክሸፍ ነው፤ መክሸፍ በየፈርጁ የኢትዮጵያውያን ባህል መሆኑን ያሳያል።

አጼ ኃይለ ሥላሴ ከራሳቸው ትውልድና ከተከታታይ ሁለት ትውልዶች የተሰነዘረላቸውን ጥያቄ ቀም ብሎ ለማሰብ ፍላጎቱ አልነበራቸውም፤ የደረሱባቸውም አንዳንድ ፈተናዎች እንዲያስቡ






አላስገደዷቸውም፤ ውድቀታቸው ለሳቸውም፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብም፣ ለአገራቱም አሳፋሪ ነበር፤ በሳቸው የሥልጣን ፍቅርና እልህ ምክንያት ለብዙ ምዕተ-ዓመታት የቆየው ታሪካዊ የዘውድ አገዛዝ ተገረሰሰ፤ በዴሞክራሲ ዘመን የተፈጠሩና አጼ ኃይለ ሥላሴ ራሳቸው በዘመናዊ ትምህርት ያስደጓቸው ትውልዶች የዘመኑን ጥያቄ ሲጠይቁ በአዳፍኔነት ለመቀጠል ፈልገው፣ አገሩንና ሕዝቡን ለባሰ አዳፍኔ አስረክበው ወደቁ፤ ኢትዮጵያንም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብንም ለውርደት አጋለጡ።

እንግዲህ በዘመናችን ያየነው ከአያት ከቅድማያት የተላለፈ የመንግሥት ሥርዓት ከዘመኑ ጋር መራመድ አቅቶት ተዋርዶ ሲያዋርድ ከመክሸፍ ሌላ ምን እንለዋለን? እውነትን ለመቀበል የምንቸገርበት አንድ ባህላዊ ጋሬጣ ያለብን ይመስላል፤ ዱሮ ብርሃኑ ዘሪሁን የአንድ የአማርኛ ጋዜጣ አዘጋጅ በነበረ ጊዜ (በ1954 ግድም ይመስለኛል፤) በየሳምንቱ እንድጽፍለት ጠይቆኝ መጻፍ ጀመርሁ፤ አንዱ የጻፍሁት ኢትዮጵያ በእርሻ በኩል ያላትን ክህሎት ለማሳየት ነበር፤ ጽሑፉ ውስጥ የበረሃነት ጠባይ ያላቸው ቦታዎች የኢትዮጵያን ከሃምሳ ከመቶ በላይ የቆዳ ስፋት ይሸፍናሉ የሚል ነበረ፤ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ (የማስታወቂያ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ይመስለኛል፤) እንዴት ተብሎ ኢትዮጵያ አአድማስ እስካድማስ ለምለም ሆና የተፈጠረች አገር፣ እንዴት በረሃ አለባት ይላል ብለው ሳይታተም ቀረ፤ በዚህ እምነታቸው ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያን በረሃማ ቦታዎች ጠባይ በጭራሽ አልቀየሩም።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ስለፕላኒንግ ቦርድ አንድ ጽሑፍ ለብርሃኑ ሰጠሁ፤ የፕላኒንግ ቦርድ ኮሚሽነር የነበረ፣ እንግሊጣር ኢኮኖሚክስ የተማረ ሰው ጥንቃቄ ያስፈልጋል ብዬ ላቀረብሁት ሀሳብ ድጋፍ እንዲሆነኝ በእንግሊዞች ላይ በታንጋኒካ የደረሰውን የለውዝ እርሻ ከፍተኛ ኪሳራ ጠቅሼ ነበር፤ ይህ በውጭ አገር ኢኮኖሚክስ የተማረ ሹም ሲመልስልኝ በታንጋኒካ በእንግሊዞች ላይ የደረሰው ዓይነት ኪሳራ እንዳይደርስብን ጸሎታችን ነው፤ ይላል፤ ለዚህማ ብዙ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ሞልተዋል፤ ፕላኒንግ ቦርድ ምን ይሠራል? ብዬ መለስሁሏቸ!



*ቀልብ ሲገፈፍ! በአራተኛ ክፍለ ጦር እስረኛ ሆነው*

የሸኛቸው፣በአራተኛ ክፍለ ጦር እንዲህ በሚያሳዝን ሁኔታ ታስረው የቆዩና የሞቱ (የተገደሉ) ሽማግሌ፣ ተገቢ ቀብር እንኳን ያላገኙ የመጨረሻው ንጉሠ ነገሥት ናቸው፤ ፎተግራፉ የሚያሳየው የግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ፣ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያን መክሸፍ ነው፤ የስንት ሺህ ዓመታት የኢትዮጵያ ታሪክ መክሸፍ ነው፤ ከአክሱም ሐውልትና ከላሊብላ ቤተ ክርስቲያኖች ወደኃጀ ከመውረድ የማይለይ መክሸፍ ነው፤ መክሸፍ በየፈርጁ የኢትዮጵያውያን ባህል መሆኑን ያሳያል።

አጼ ኃይለ ሥላሴ ከራሳቸው ትውልድና ከተከታታይ ሁለት ትውልዶች የተሰነዘረላቸውን ጥያቄ ቆም ብለው ለማሰብ ፍላጎቱ አልነበራቸውም፤ የደረሱባቸውም አንዳንድ ፈተናዎች እንዲያስቡ

አንድ ሌላ ጠንካራ ምሳሌ ልጨምር፤ በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የሚከሰቱና ብዙ ሕዝብን የሚጨርሰውን ችጋር ለማጥናት ተነሣሁ፤ በዚህ ጊዜ በጣም ያስደነቀኝ ነገር ችጋሩ ሰዎችን እየረፈረፈ ባለበት ጊዜ ለጊዜውም ይሁን ለወደፊቱ የሚደረግ ምንም ዓይነት ዝግጅት አለመኖሩ ነበር፤ በትግራይ ራስ ሥዩም ለአውራጃ ገዢዎች ሁሉ ያስተላለፉት ትእዛዝ ሕዝቡ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተሰበሰበ እንዲጸልይ ነበር፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ይህንንም ማድረግ አይችሉም ነበር፤ በአገሩ ውስጥ ችጋር ገብቷል ብሎ የሚነግራቸው ማን ነው? ማንም! ‹‹ስለችጋር መስማት አይፈልጉም!›› ስለትግራይ ችጋር በአበበ ከበደ በኩል መርዶውን የላክሁላቸው እኔ ነኝ! በጊዜው የአበበን ስም ጠቅሼ በአደባባይ ይህንንም መናገር አይቻልም ነበር።

እነዚህን ምሳሌዎች መጥቀስ ግድ የሆነብኝ መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ በአንዳንዶች ሰዎች ላይ ያስነሣውን ንዴት፤ አጉል ንዴት በመገንዘብ ነው፤ ታሪካችንን ሁለቱንም ዓይኖቻችንን ግልጥ አድርገን ማየት ይጠበቅብናል፤ ጥሩ ጥሩውን ነገር ብቻ እየመረጥን መኩራራቱ ስሕተቱን ይከምራል እንጂ ጥቅም አያስገኝም፤ ስለዚህ ታሪካችንን በሌላ መንገድ ልንፈትሸው እንገደዳለን፤ ከታሪክ እየተማርንና ስሕተቶቻችንን እያረምን በመሄድ የወደፊቱ ኑሮ የተሻለ እንዲሆን ይረዳናል።

ከዚህ በላይ በአጼ ኃይለ ሥላሴ፤ በደርግና በወያኔ የአገዛዝ ዘመኖች የሆኑትን ዛሬ ካለንበት ሁኔታ ጋር እያስተያየን ለምን ወደተፈለገው የእድገት ለውጥ አልደረስንም? ለምን ሌሎች አገሮች የደረሱበት የእድገት ደረጃ ላይ አልደረስንም? እያልን መጠየቅ ያስፈልገናል፤ ለእነዚህ ጥያቄዎች በምንሰጣቸው መልሶች ላይ አዲስ ማኅበረሰብ መገንባት እንጀምራለን፤ አዲስ ማለት ከዱሮዎቹ ስሕተቶች የጠራና የእድገት ለውጥን የሚለምድ ማለት ነው፤ ስለዚህም ሦስት በተመሳሳይ ችግር ውስጥ እየገቡ የሚያልፉ ትውልዶች ሳይሆኑ አዲሱ ከቀድሞው እየተማረና የራሱንም እየጨመረ በመለወጥ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ የሚችል ትውልድ እንዲበቅል ሁኔታዎች ይመቻቹለታል ማለት ነው።





ስለዚህም ታሪካችንን ስንማር እንደዚህ ሆነ፤ እንደዚህ ሆነ ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሆነም ማወቅ ይጠቅመናል።

በሺህ ዓመታት የሚቆጠረውን ታሪክ እናቆየውና ከንግሥት ዘውዲቱ በኋላ የሆነውን ከዚህ በላይ በአጭሩ እንዳየነው ታሪካችን ቁልቁል መንከባለልን ብቻ ያሳየናል፤ ምክንያቱ ምንድን ነው ብለን ጠይቀን ብዙ ምክንያቶችን መደርደር እንችላለን፤ ነገር ግን ዋና የሚባሉትን ብቻ መርጠን ብንነጋገርባቸው ይሻላል በማለት በመጀመሪያ አዳፍኔን እንወቀው፤ ናላችንን በኩርኩም እየነደለ፤ ሲፈልግም በአጣና ዱላ፤ ሲፈልግም በላስቲክ ዱላ፤ ሲፈልግም በጠመንጃ፤ ሲፈልግም በመትረየስ እየረፈረፈ፤ እየገደለ፤ እያቆሰለና አካለ-ጎደሎ እያደረገ የሚገራን ቢሆንም ብዙዎች አያውቁትም።

# ምዕራፍ ፫
# አዳፍኔና መከሸፍ

## መከሸፍና አዳፍኔ

መክሸፍን ለማስተዋወቅ በሞከርሁበት ጊዜ ብዙ የተማሩና የተመራመሩ ኢትዮጵያውያን እንግዳ ነገር ሆኖባቸው ነበር፤ በዘር ማሰብ ከጀመርን አንድ ትውልድ ማለቱን በመገንዘብ መክሸፍንም በዘሩ ለማስረዳት ልሞክር ነው፤ የመክሸፍ አባት አዳፍኔ ይባላል፤ አዳፍኔ እንደልጁ ጭምት አይደለም።

በኢጣልያ የወረራ ዘመን ወደአዲስ አበባ በሚያስገቡት ኬላዎች ላይ ‹‹ፖስቶ ብሎኮ››[14] የሚባል አላፊ-አግዳሚውን የሚፈትሽ ጣቢያ ነበር፤ በዚያ ኬላ ላይ ጠርቡሻቸውን[15] ከነመነሳንሱ አድርገው፣ በአንድ እጃቸው ረጅም የብረት ዘንግ በሌላ እጃቸው አኮርባጅ[16] ይዘው ይቆማሉ፤ ከገጠር እህል በስልቻ ጭኖ ወደገበያ የሚመጣውን ሁሉ እያስቆሙ በአለንጋው ሰዎቹን ቸብ እያደረጉ፣ በሹሉ ብረት ደግሞ ስልቻዎቹን እየሰረሰሩ የሚፈትሹ ባንዳዎች ነበሩ፤ እነዚህ የአዳፍኔ ሎሌዎች ናቸው፤ እንደዚህ ያሉ ወገኖች ዛሬም አሉ።

ዱሮ ገና በአሥራ ዘጠኝ መቶ ሃምሳዎቹ፣ የዛሬ ስድሳ ዓመታት ግድም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (ነፍሱን ይማረውና!) ውስጥ አንድ የውይይት መድረክ ነበር፤ ተወያዮቹ ሲጨርሱ እኔ አንድ ጥያቄ አቅርቤ ነበር፤ ኬንያ ጆሞ ኬንያታ

[14] ከደርግ ዘመን ጀምሮ እስካሁንም የፍተሻ ኬላዎች አሉ፤ ከጣልያን ዘመን በኋላ ተቋርጦ የነበረው ቀጥሏል።
[15] ባንዶች ራሳቸው ላይ የሚያደርጉት ረዘም ያለ ባርኔጣ።
[16] ጉማሬ፤ አለንጋ።





አለው፣ ታንዛንያ ጁልየስ ኒየሬሪ አለው፤ ... ኢትዮጵያ ትልቅ ሰው ለምን የላትም? ብዬ ስጠይቅ በአዳራሹ ትንሽ የማጉረምረም ድምጽ ተሰማ፤ አንዱ ጮሌ ተወያይ (ዛሬ አሜሪካ ያለ ይመስለኛል) እንደማፌር እያለ ‹‹እኛም ጃንሆይ አሉን፤›› አለ፤ እኔ እንደገና ተነሥቼ ጃንሆይ ሲወለዱ ትልቅ ነበሩ፤ እኔ የጠየቅሁት በሥራው ትልቅ የሆነ ሰው ነው፤ ብዬ አብራራሁ፤ ለእኔ እስከዛሬም መልሱ ትልቅ ሰው የለንም ነው፤ ኢትዮጵያ ቆማ ያስወለደቻቸው የአፍሪካ አገሮች ብዙ ታላላቅ ሰዎችን አፍርተው ለዓለም መድረክ አቅርበዋል፤ ዓለም-አቀፍ ሽልማቶችን የተሸለሙ ከደቡብ አፍሪካ እስከግብጽ አሉ፤ እንዲህ ዓይነት ሰዎች በኢትዮጵያ ቢወለዱም አዳፍኔ እየቀጨ በሎሌነት አስቀርቷቸዋል፤ በትውልድ ትልቅ የሆኑትን ጊዜ ሻራቸው፤ በጉልበት ትልቅ የሆኑትን ጉልበት ሻራቸው፤ ገና ከመሬት ብቅ ሲሉ አናቱን በኩርኩም እያፈለሱ ተርታ እንዲገባ የሚያደርጉ የአዳፍኔ አሽከሮች ሞልተዋል፤ በአዳፍኔ መንደር ትልቅ ሰው ከየት ይመጣል! ረግጦ ከሚገዛው ከአንድ ሰው በቀር ሌላ ትልቅ የሚባል ሰው የለም፤ የዚህ ሰው ሎሌዎች ምንጣፉ ናቸው፤ ሕዝቡ ደግሞ የሎሌዎቹ ምንጣፍ ነው፤ --

*ሞት ማለት*
*አለመናገር ነው፤ ጭው ያለ ዝምታ፤*
*የመቃብር ሰላም፤ የሬሣ ጸጥታ፤*
*ደሀ በሰሌኑ፣ ሣጥን ገብቶ ጌታ፣*
*የውሸት ልዩነትተጋድሞ በተርታ፣*
*አይመሽ ወይ አይነጋ፤ ጠዋት የለ ማታ፤*
*ሐዘን የለ ለቅሶ፤ ደስታ፣ ፈገግታ፣*
*ዘፈኑና ለቅሶው የምስጥ ሹክሹክታ፤*

*ሞት ማለት*
*አይረገዝበት፤ አይወለድበት፤*
*የመቃብር ዓለም፣ ጭንጋፍ የጭንጋፍ ቤት!*
*የሰው ልጅ እንደእበት ትል የሚሆንበት!*

*ክርክር የለበት፤ ውድድር የለበት፤*
*ውሸትና እውነት በማይበርድ ፍትወት*
*የተሳሰሩበት፤*
*የድብቅብቅ ዓለም፤ ምሥጢር የበዛበት!*
*ሁሉም በየጉድጓድ የተሸሸገበት፡፡[17]*

አዳፍኔ የአፍሪካ በሙሉ በሽታ ነው፤ ከቅኝ ግዛት የተወረሰ በሽታ ይመስለኛል፤ የእኛ ግን የቆየና ስንፈጠር የተጠናወተን መድኃኒት ያላገኘንለት በሽታችን ነው፤ በአገሩ ትልቅ ሰው እንዳይበቅል ሁሉም ተግቶ ይጠባበቃል፤ አንዱ ብቅ ብሎ ከፍ እንዳይል ሌላው ሁሉ ለመጥለፍ ያሴራል፤ የአዳፍኔም ኩርኩም አናት ይበሳል፡፡

አዳፍኔ የመክሸፍ ወላጅ አባት ነው ብለናል፤ አዳፍኔ የአገዛዞች ሁሉ የባሕርይ ስም ነው፤ አዳፍኔ ጸረ-ነጻነት ነው፤ ለምን ቢባል ከአዳፍኔ በቀር ማንም ሌላ ነጻነት ሊኖረው አይችልም፤ አዳፍኔ ጸረ-እኩልነት ነው፤ ለምን ቢባል ከአዳፍኔ እኩል መሆን የሚችል ሌላ የለም፤ ሎሌዎቹም በበኩላቸው ከሕዝቡ ውስጥ ከእነሱ እኩል የሚሆን የለም ይላሉ፤ አዳፍኔ ጸረ-ፍትሕ ነው፤ ለምን ቢባል ከአዳፍኔ ውጭ ምንም ሕግ፣ ምንም ደንብ፣ ምንም ባህል የለም፤ አዳፍኔ ጸረ ነጻነት በመሆኑም ጸረ-ልማት ነው፤ ለምን ቢባል አዳፍኔ ሀብት ልብን ያሳብጣል፤ ትእቢትን ይጋብዛል ብሎ ስለሚያምን ለሱ የሚመቸው የሕዝብ ደሀነት ነው፤ በደሀነት እየተጠበሰ ሲኖር ሕዝቡ ለማኝ ይሆናል፤ ሕዝቡ በሆዱ ብቻ የሚገዛ ይሆናል፤ ለነፍሱም ቢያስብ ካህናቱን ሎሌ አድርጎ ለሆዳቸው እንዲገዙ በማድረግ በአዳፍኔ ስር ማስገባት ይቻላል፤ በዚህ ሁሉ ምክንያት አዳፍኔ እግዚአ-ደሀነት፣ የደሀዎች ጌታ ነው፡፡

አዳፍኔ የአገሩ ባለቤት ነው፤ አዳፍኔ የአገሩ መሬት ባለቤት ነው፤ አዳፍኔ የአገሩ ማዕድን ባለቤት ነው፤ አዳፍኔ የአገሩ ወንዞች፣ ሐይቆች ጎርፎች፣ በአጠቃላይ የአገሩ ውሀ ባለቤት ነው፤ በአገሩ የሚገኝ ሀብት የሚባል ነገር ሁሉ የአዳፍኔ ነው፤

[17] መስፍን ወልደ ማርያም፣ *ዛሬም አንጉርጉሮ*፣ አዲስ አበባ፣ 2006





በአጋጣሚ የውጭ ሀብታሞችም በአገሩ ውስጥ ከተገኙ አዳፍኔ ወይ በሎሌነት ወይ በአቀባባይነት ያቀርባቸዋል፤ የአዳፍኔን ምኞትና ፈቃድ በማንም ላይ፣ በማናቸውም ጊዜ ለማስፈጸም የተሟላ ጉልበትና ሀብት ያላቸው ሎሌዎች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው፤ ስለዚህ ጥቂት ሎሌዎቹን ምድርን የለቀቁ ሀብታሞች መስለው እንዲታዩ ይፈቅድላቸዋል፤ እውነቱ ግን ችላ ያለ መስሎ ወጥመድ ውስጥ ያስገባቸዋል ማለት ይሆናል፤ ሀብታም ሎሌዎች በበረከቱ መጠን የደሀዎች ብዛት እየጨመረ ይሄዳል፤ ደሀው ሙልጭ ይወጣና የሚቀርለት እያቃሰተም ቢሆን ለምኖ በሕይወት የመኖር ዕድል ብቻ ይሆናል፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን መስሎ እግዚአደሀነት ሆኖ ይተከላል፡

እግዚአደሀነትን ማስረዳት ያስፈልጋል፤ እግዚአብሔር ከሚለው የመጣ ነው፤ ለእግዚአብሔር በማናቸውም ነገር ድንበር የለውም፤በሁሉም ነገር፣ በሁሉም ቦታ በማናቸውም ጊዜ ይገባል፤ እግዚአደሀነትም ልክ እንደእግዚአብሔር ድንበር የለውም፤ በፈለገበት ጉዳይ፣ በፈለገበት ቦታና ጊዜ ገብቶ የራሱን ፈቃድ ማስፈጸም ይችላል፤ አንዱ መረዳት ያለብን ይህንን ነው፤ ሁለተኛው መረዳት ያለብን ሕዝቡ በሙሉ ደሀ መሆኑ አስፈላጊ መሆኑን ነው፤ደሀ ሲሆን ጠዋት ከእንቅልፉ ተነሥቶ ማታ ደክሞት እስኪተኛ ድረስ አንድ ጥያቄ አእምሮውን ሲያስጨንቀው እንዲውል ያስፈልጋል፤ «ምን እበላለሁ?» ደሀን ይቺን ጥያቄ ብቻ ካሸከሙት ጸጥ-ለጥ ብሎ ይገዛል፤ ከዚህ ጋር አብሮ መታሰብ ያለበት ደሀ በምንም ዓይነት መንገድ ሀብት ማካበት እንዳይችል ማድረግ ነው፤ ኑሮው ከእጅ ወደአፍ ብቻ እንዲሆን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ እንዳይጠግብ እየጠበቁ እንዳይራብም ጉልበቱን መጠገን ያስፈልጋል፡

እያንዳንዱ ሰው ሀብት እያካበተ ብዙ ሰዎችን ለመቅጠር የሚያስችለው ከሆነና ጊዜ ከተሰጠው ተወዳዳሪ ኃይል ለመሆን ይቃጣዋል፤ ለዚህ ነው አዳፍኔ በሀብት ብቻ ሳይሆን በትምህርትም፣ በእውቀትና በጥበብም፣ በዘፈንም፣ በልመናም ቢሆን ማንንም ከተወዳዳሪነት ውጭ ማድረግ የሚፈልገው፤ የማሰብ፣ ሀሳብን የመግለጽ፣ ደመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ሰላማዊ

ሰልፍ የመውጣት መብቶችና ነጻነቶች ጥያቄ የማይነሣባቸው ቢሆኑም አዳፍኔ የማይፈልጋቸው ናቸው፤ እነዚህንና ሌሎችንም ርእሶች በትንሹ በየቦታቸው እናነሣቸዋለን፡፡

አዳፍኔ በምንም ነገር ተወዳዳሪዎችን አይፈልግም፤ በትክክለኛው መንገድና ሥርዓት የተገኘ ትምህርት አእምሮን ነጻ ያወጣል፤ አእምሮና ሀሳብ የግል ሀብት መሆናቸውን ያስገነዝባል፤ የራስንም ሆነ የሌሎችን ሰዎች ልክ ለማወቅ ይረዳል፤ የሰውነትን ክብር ለአዳፍኔ ምንጣፍ ማድረግ የሚያደርሰውን የመንፈስና የአስተሳሰብ ዝቅጠት በግልጽ ያሳያል፤ በዚህም ምክንያት በትክክለኛው መንገድና ሥርዓት የተገኘ ትምህርት ከአዳፍኔ ጋር በቀጥታ ያጋጫል፤ **እውነትን ተናግሮ የመሸበት ማደር** አዳፍኔን እንደጦር የሚወጋው አስተሳሰብ ነው፤ ስለዚህም የትምህርትን ኃይለ-ቃል ለማዶልዶም አዳፍኔ ትምህርትን ወደማሠልጠን ይለውጠዋል፤ **ማሠልጠን ማለት መግራት ማለት** ይሆናል፤ በቁሉም ሆነ ፈረስ ወይም ውሻ እንደሚገራ፤ የሰውም ልጅ ለሎሌነት እየተመለመለ ይገራል፤ በመማርና በመሠልጠን መሀከል ያለው ዋናውና ትልቁ ልዩነት የተገራ ሎሌ አያስብም፤ የሚንቀሳቀሰው ጌታው በሚሰጠው ትእዛዝ ብቻ ነው፤ እሱ የሚያስብበት የራሱ አእምሮ የለውም፤ እሱ መንፈሱን የሚመዝንበት ልቡና የለውም፤ ከጌታው ውጭ ወገን የለውም፡፡

## አዳፍኔ የመክሸፍ ወላጅ አባት

*አዳፍኔ ሉዓላዊ ኃይል ነው፤ ከእሱ በላይ ምንም የለም፡፡*
*አዳፍኔ አረመኔ ነው፤ መንፈሳዊ ስሜት በጨረፍታም አይደርስበትም፤*
*አዳፍኔ ብቻውን ነው፤ ዘመድ፣ ወገን፣ ባልንጀራ፣ ጓደኛ የሚባል የለውም፤*
*አዳፍኔ ጨካኝ ነው፤ ምሕረት የሚባል ቃሉንም አያውቀውም፤*
*አዳፍኔ ከራሱ ሕይወት በቀር የማንም፣ የምንም ሌላ ሕይወት ለእሱ ዓላማ መሣሪያነት ካልሆነ በቀር ፋይዳ የለውም፤*
*አዳፍኔ መውደድንም መወደድንም አያውቅም፤*





*አዳፍኔ ጥረቱ ለማስፈራትና ለመፈራት ነው፤*
*በትምህርትና በእውቀት ላይ ያልተመሠረተ አገዛዝ፣ በነጻነትና በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ የሕዝብ ስብስብ፣ በእድገትና መሻሻል ላይ ያልቆመ ኑሮ በየፈርጁና በየደረጃው መክሸፍ እንደሚጠብቀው ታሪካችን ያሳያል፡፡*

## ትምህርትና ማኅበረሰብ

ትምህርት የኑሮ ዘዴ የመሆኑን ያህል እንስሳት ሁሉ ይማራሉ፤ ከተወለዱ ቀን ጀምሮ ወላጆቻቸው ምግባቸውን ከየትና እንዴት እንደሚያገኙ፤ ጠላት ማን እንደሆነና እንዴት እንደሚከላከሉ ይማራሉ፤ ይህ ለዕለት-ተዕለት ለመኖር ሲባል የሚደረግ ግዴታ ነው፤ የሰው ልጅ ግን በዕለት-ተዕለት የተፈጥሮ ግዴታ ላይ አይቆምም፤ ወደኋላው ዞር ብሎ ከየት እንደመጣና እንዴት እንደመጣ የማወቅ ፍላጎት ስላለበት መሠረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላት አልፎ የመጣበትንም ይማራል፤ እንዲሁም ተፈጥሮ ያበረከተለትን መልቀም ብቻ ሳይሆን ራሱም እየሠራ ፍሬን የሚያመርትበትን መንገድና ዘዴ ይማራል፤ ከወላጆቻቸው በተማሩት እውቀት ላይ ልጆቹ በራሳቸው የፈጠሩትን እውቀት ይጨምሩበታል፤ እንዲህ እያለ አዲሱ ትውልድ ከአለፈው ትውልድ የተሻለ፣ የበለጸገ፣ የጠነከረ ሆኖ በልማት ይገሰግሳል፤ በምድር ላይ እየተሰቃየ በደህነት የሚኖር ሳይሆን ዙሪያውን እያየ ከጨረቃም አልፎ ሌሎች ዓለማትን የሚዳብስ ይሆናል፡፡

አዳፍኔ ባለበት ግን ይህ አይቻልም፤ **ትምህርት የአዳፍኔ ጸር** ነው፤ ስለዚህም **አዳፍኔም የትምህርት ጸር** ነው፤ አዳፍኔ የሚመቸው ደካማ ማኅበረሰብ ነው፤ ስለዚህም ትምህርት የሚባል ነገር የአዳፍኔን ጆሮ የሚቆረቁር ነው፤ ከአጼ ምኒልክ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ ትምህርት ቤት በመባል የታወቀው በክርስቲያንና በእስላም ካህናት የሚካሄደው ነበር፤ ዛሬ ሌላ ስም ወጥቶለታል፤ የቄስ ትምህርት ቤት ወይም የቀሎ ትምህርት ቤት ይባላል፤ ለአዲሱም በሰሜን ኢትዮጵያ **አስኳላ** የሚል የኢጣልያን ስም ተሰጥቶታል፤ **ስለባህላዊ ትምህርትና** ትምህርት ቤቶች ብዙ ጽሑፎች አሉ፤ የኔ ጉዳይ ስለነሱ ሳይሆን ስለአገዛዙና

ስለትምህርት ነው፤ በሁለቱ መሀከል የነበረው ግንኙነት አብዛኛው ሃይማኖታዊ ቢሆንም አንዳንዴ ልዩ እውቀት በሚያስፈልግበት ጊዜ ሊቃውንት ከቤተ ሃይማኖት ይፈለጉ ነበር።

ትምህርት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ቢቆራኝም የሕዝቡ ሸክም ነበር፤ የቤተ ክህነት ተማሪዎች በየአካባቢያቸው ያሉትን መንደሮች ለቀፈፋ እንዲመቻቸው ደልድለው ምግባቸውን ይሰበስቡ ነበር፤ በኋላ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የትምህርት ታክስ ከሚሉት ጋር ተመሳሳይ ነበር፤ ተማሪዎቹ ከሩቅ ቦታዎች ስለሚመጡ የዕለት ምግባቸውን የሚያገኙት በየተደለደሉበት መንደር በመቀፈፍ ነበር።

አገዛዙ ስለትምህርት ምንም ዓይነት ፍላጎት አልነበረውም፤ የነበረው የትምህርት ዓይነትም ስለዓለማዊ ጉዳይ ምንም ዓይነት ፍላጎት አልነበረውም፤ አገዛዙና ሃይማኖት የሰውን ልጅ ተቃርጠው፤ ለሁለት ገንጥለው ሥጋውን ለአገዛዙ ነፍሱን ደግሞ ለሃይማኖት አድርገው ተካፍለዋል፤ አንዱ ሥጋውን የበደለ ለነፍሱ ያደረ ሲል ሌላው ከሰው መርጦ ለሹመት እያለ የመሳፍንትና የመኳንንት አደግዳጊዎቹን ያጠናክራል፤ የነፍሱ ነገር እዚህና አሁን በቦታና በጊዜ በታጠረ ኑሮ ላይ በቀጥታ የሚያሳየው ነገር የለም፤ የሥጋ ጉዳይ ግን ሆድ ይቆርጣልና ወዲያው ይሰማል፤ ስለዚህ እንኳን ተራው የሃይማኖት ምእመንና ካህናቱና መንፈሳውያን መሪዎች የተባሉትም ለሆዳቸውና ለምቾታቸው ሲገዙ እያየን ነው፤ (አንድ ጊዜ ስብሐት ነጋ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቲያትር አሁን ብሔራዊ ቲያትር በተባለው ውስጥ በአደባባይ ከጳጳሳቱ መሀል አንድም የሚረባ ሰው የለም፤ አንድ ቢገኝ እንዲሸለም አደርግ ነበር ሲል ብዙ ሰዎች ሰምተናል፤ እንደሚያውቃቸው አልጠራጠርም፤) በቅርቡ የእስላሞቹንም ሹሞች የእስልምና ምእመናን ሲያወግዙ ሰምተናል፤ መንፈሳዊነት ከአገዛዙ ጋር በሽርክና መቆሙ ብቻ ሳይሆን ከሕዝብ ጋር ተቃራኒ መሆኑ እንደአሁኑ ጊዜ ገሀድ ወጥቶ አያውቅም፤ **አዲስ የሆነው ቤተ ሃይማኖት ከሕዝብ ጋር በተቃራኒነት መቆሙ ነው።**

ፍሬ ነገሩ ባህላዊው የሃይማኖት ትምህርት ሰዎችን ነጻ ለማውጣትና በነጻነት እንዲያስቡ፤ አእምሮአቸውን ለእውነትና ለጥበብ እንዲከፍቱ የሚያደርግ አልነበረም፤ ከባህላዊው ትምህርት





ተነሥተው ወደከፍተኛ የማሰብ ደረጃ የደረሱ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፤ **በመሠረቱ ባህላዊው ትምህርት እውቀትን ከእውነት ጋር አላገናኘውም ነበር፤** ስለባህላዊ ትምህርት አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን ማወቅ አለብን፤ አንደኛ ባህላዊ ትምህርት ከቤተ መንግሥት ውጭ ነው፤ ከቤተ መንግሥት ውጭ ነው ማለት በመንግሥት ቁጥጥርና መመሪያ ስር አይደለም ማለት ነው እንጂ ከሀገረ-መንግሥት ውጭ ነው ማለት አይደለም፤ የባህላዊ ትምህርት ዓላማውም ሥርዓቱም ከቤተ ሃይማኖት ጋር የተያያዘ ነበረ፤ ሁለተኛ **ባህላዊ ትምህርት ምንም ዓለማዊ ይዘት አልነበረውም፤** ሙሉ በሙሉ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ብቻ የሚመለከት ነበር፤ ስለእርሻ፤ ስለቤት ሥራ ወይም ስለህክምና ምንም ትምህርት አልነበረም፤ የሚያስደንቀው ትንሽም በህክምናና በሥነ ልቡና አንዳንድ ያልተጣሩ እውቀቶች ነበሩ ቢባልም በምሥጢር የተጠበቁ ሆነው መቅረታቸው ነው፤ ሦስተኛ **ባህላዊ ትምህርት ከነጻነት ውጭ ነበረ፤** በትምህርቱ ውስጥ ከመምህሩ ከተሰጠው ውጭ ምንም የሚጨመር ወይም የሚቀነስ ነገር አልነበረም፤ **ትልቁ ጉድለቱ የተቀበለውን እንደተቀበለው የማስተላለፉ ግዴታ ነው፤ ማሰብ ሲቆም መክሸፍ ይመጣል።**

የባህላዊው ትምህርት የመጨረሻ ውጤት ሰዎችን ወደእግዚአብሔር እንዲቀርቡ ለማድረግ ሲሆን አቀራረቡም ከጸሎት ወይም ከልመና የማያልፍ ነበር፤ ይህም ማለት በበጎ ተግባር ላይ ሳይሆን፤ ወይም ለግል ኑሮ እያንዳንዱ ሰው ያለበትን ኃላፊነት በማስታወስ ሳይሆን **መለመንን እንደዋና የችግር መፍቻ በማድረግ ነው፤** እንዲያውም እግዚአብሔርንና ሰውን ዋናው የማቀራረቢያ መንገድ **ፍርሃትና ማጣት** ነበር፤ ደሀው ሕዝብ እግዚአብሔርንም ሆነ ባለሥልጣኖችን የሚለምነው ወይ በማጣት፤ ወይ በመፍራት ነበር፤ ዛሬ አንዳንድ ሰዎች ይህ አመለካከት እየተለወጠ ነው ብለው ያምናሉ፤ እሰይ! እንበል፤ ግን እውነት ሆኖ ገና አላየነውም፤ ካህናት ስለገሃነመ እሳት ሲሰብኩ በጣም ያስፈራል፤ አዳፍኔ በቤተ ሃይማኖትም ሆነ በቤተ መንግሥት በፍርሃት የሰውን ልብ ሁሉ እንዲገዛ ይፈልጋል፤ እንዲህ ያለው

ሁኔታ ይመቸዋል፤ በፍርሃት ቆፈን ሽባ ያደረጉትን ሕዝብ ‹‹አሰሁልህ!›› እያሉ ለመቀስቀስና በተፈለገው አቅጣጫ ለመንዳት ይቻላል።

ፍሬ ነገሩ የኢትዮጵያ ባህላዊ ትምህርት **ሥርቶ ለመበልጸግ፣ ወይም በነጻነት እስቦ ራስንና አካባቢን ለመለወጥ አይጠቅምም ነበር፤ ይህ ዓላማውም አልነበረም።**

## ትምህርትና ለውጥ

**ትምህርት የለውጥ መሣሪያ** ነው፤ የሰው ልጅ በኑሮው ላይ ሊያመጣ የሚፈልገውን በጎ ለውጥ የሚያራምድበት መሣሪያ ነው፤ ስለዚህም ትምህርት ለውጥ፣ ያውም በጎ ለውጥ የሚያራምድ እንዲሆን ይፈለጋል፤ ይህንን ሳያደርግ ሲቀር ማኅበረሰቡ ገና ከአዳፍኔ አፈና ስር አልወጣም፤ አውቆም ሆነ ሳያውቅ ነገንም እንደዛሬ ለማድረግ የወሰነ ነው ማለት ነው፤ በሌላ አነጋገር አዳፍኔ የትምህርትን የመለወጥ ችሎታ በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ማኅበረሰቡ ነገ ከዛሬው የተለየ እንዳይመኝ ያደርጋል ማለት ነው፤ አዳፍኔ ማኅበረሰቡን ያደነዝዘዋል፤ ያደንዘዋል፤ ያደነቁረዋል፤ ትምህርት የለውጥ መሣሪያ ሲሆን ማኅበረሰቡ ይነቃል፤ ጥያቄዎችን ያበዛል፤ የገዢዎቹን ድንቁርና ያጋልጣል፤ ትእዛዞቻቸውንም እምቢ ማለት ይጀምራል።

ፍርደ-ገምድል እንዳንሆን የማኅበረሰቡንም ኃላፊነት በአግባቡ መደልደል አለብን፤ ማኅበረሰቡ ለምዕተ-ዓመታት በፍርሃት ቆፈን ተይዞ በአዳፍኔዎች እየተገዛ በባርነት መኖር ከተስማማው በአዳፍኔ ላይ ብቻ ለመፍረድ አይቻልም፤ ኃላፊነቱን ማኅበረሰቡም መጋራት አለበት።

የባህላዊ ትምህርት ዓላማ ሰውን ለመለወጥ አልነበረም፤ ለውጥ የሚጠላና የማይፈለግ ነገር ነበር፤ ስለዚህም ትምህርት የለውጥ መሣሪያ አልሆነም፤ እንዲሆንም አልተፈለገም፤ እንዲያውም፣ አዳፍኔ ለውጥን ለመከላከል መሣሪያ አደረገው፤ ዛሬም ቢሆን ትምህርት የለውጥ መሣሪያ መሆኑ ያጠራጥራል፤ **የዩኒቨርሲቲን ነፍስ ጥፍፍ አድርገው አውጥተው ስያሜውን ለመቃብር ቤቱ ድንጋይ ሰጥተውታል፤** የአዳፍኔ ዓላማ የዛሬው





ትውልድ እንደትናንቱ፣ የነገው ትውልድ እንደዛሬው እየሆነ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ እንዲቀጥል ነው፤ ትምህርትም እንደማናቸውም ዋና ቁም-ነገር ቁሞ-ቀር መሆኑ ለአዳፍኔ የተመቸና ሕዝቡን ሁሌም ኋላ-ቀር አድርጎ ለአገዛዝ የሚያመቻችለት ነው፤ አገዛዝ ለትምህርት ያለውን ክፉ ጥላቻ ከመቼውም የበለጠ በወያኔ ዋአገዛዝ ዘመናት እያየን ነው፤ ሕንጻ እየተሠራ ሲፈርስ፣ መንገድ እየተሠራ ሲፈርስ፣ ወዳጅነት እየተገነባ ሲፈርስ ... እያየን ነው፤ የማይገኙ መጻሕፍት ከቤተ መጻሕፍት እየተፈነገሉ በኪሎ ሲሸጡ እያየን ነው፤ የትምህርት ነጻነት እየተገፈፈ አስተማሪዎች በሎሌነት እያገለገሉ ነው፤ ትምህርት ማለት ግለሰቡን ለውጦ ማኅበረሰቡን የመለወጫ መሣሪያ የሚያደርግ ሳይሆን በብዙ የሕዝብ ገንዘብ የሚገዛ አጉል ጌጥ እየሆነ ነው፤ በደርግ ዘመንም በሽታው ጀምሮ ነበር፤ ነገር ግን ዶክተር ሆኛለሁ ብሎ ያወጀው የደርግ አባል መሳለቂያ በመሆኑ ከፎቅ ላይ ተወርውሮ ምኞቱን ቀጨው፡

የሰው ልጅ ከአንዱ ትውልድ ወደሌላው ትውልድ ሲሸጋገር በእውቀት እያደገና ኑሮውን እያሻሻለ እንዲሄድ ከተፈለገ ትምህርት የለውጥ መሣሪያ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፤ይህ የሚሆነው በደመ-ነፍስ አይደለም፤ እስቦ፣ እውቀት እንደሚጠቅመው ተረድቶ፣ የእውቀትን ዋጋ ተገንዝቦ፣ እውቀትን ለማዳበር የሚያስፈልገውን መሰናዶ እያደረገ ነው፤ መሰናዶው የእውቀትን ውጤት በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን ቁርጠኛነትን ይጨምራል፤ በሥራ ላይ የማያውሉት እውቀት ለኑሮ አይጠቅምም።

**ትምህርት እውቀትን የመገብየት ሥርዓት ነው፤** ለጊዜው በዘመናዊ ትምህርት ላይ እናተኩር፤ አንድ ልጅ በስድስት ዓመት ትምህርት ቢጀምር አሥራ ሁለተኛ ክፍል ሲጨርስ አሥራ ሰምንት ዓመት ይሆነዋል፤ ወደከፍተኛ ትምህርት የገባ እንደሆነ እንደትምህርቱ ዓይነት፣ ከአራት እስከስድስት ዓመት ይፈጅበታል፤ ሲጨርስ ዕድሜው ከሃያ ሁለት እስከሃያ አራት ይሆነዋል፤ እንግዲህ በግልም ቤተሰቦቹ እየከፈሉ ቢያስተምሩትም፣ ወይም በመንግሥት ወጪ ቢማርም-ያው የኗገር ሀብት ነው፤ ዋናው

ነገር አስተማሪዎችንና ትምህርት ቤቶችን በማቅረብ ልጆች የተሟላ ትምህርት እንዲያገኙ የሚያደርጋው ዞሮ ዞሮ ሕዝብ ነው፤ ይህ ወጪ በወርና በዓመት ሲሰላ ቀላል አይደለም፤ በተለይ ለደሀ ሕዝብ ከባድ መስዋእት ነው፤ በአሁኑ ጊዜ አንድ ባለሀብት ለአንድ ሥራ አንድ መቶ ሚልዮን ብር ቢያወጣ የዚያን እጥፍ በአምስት ዓመታት አገኘለሁ ብሎ ሊሆን ይችላል፤ አንድ ሕዝብ በብዙ ቢልዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ አውጥቶ ልጆቹን ሲያስተምር በስንት ዓመት ወጪውን ይመልሳል ተብሎ ነው? ተማረ የሚባለው ሰው ሁልጊዜም ሊያስብበትና መልስ በመስጠት ኃላፊነቱን ለመወጣት የኅሊና ግዴታ መቀበል የሚጠበቅበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው።

ትምህርትን በመሣሪያነቱ ስናስብ መሣሪያነቱ ለማን እንደሆነም አብረን ማሰብ ያሻል፤ በአጠቃላይ አዳፍኔ ባለበት የትምህርት መሣሪያነት በመጀመሪያ ለአዳፍኔ፣ ቀጥሎም ለቤተ ሃይማኖት ነው፤ አዳፍኔ ቤተ ሃይማትንም በአጠቃላይ እንደመሣሪያው ያየዋል፤ ትምህርት ለእድገትና ለመሻሻል፣ ለትርፋማ ኑሮ የሚያገለግለው በዋነኛነት መሣሪያነቱ ለግለሰቡ ሲሆን ነው፤ ግለሰቡ በሙሉ ነጻነት አእምሮውን እንደልቡ ለማሠራት ሲችል ነው፤ እውቀት ከነጻነትና ከእውነት ጋር አብሮ የተፈተለ ነው፤ አዳፍኔ እውቀትንም ሆነ ነጻነትን፣ ወይም እውነትን አይወድም፤ ስለዚህም የግለሰብን ነጻነት በሆነ ባልሆነው ማዳፈን ይፈልጋል፤ እዚህ ላይ አንድ ዋና የኋላ-ቀርነት ባሕርይ ያጋጥመናል፤ ኋላ-ቀርነት የግለሰብ ባሕርይ አይደለም፤ ኋላቀርነት የማኅበረሰብ ባሕርይ ነው፤ የጅምላ አስተሳሰብ ባሕርይ ነው፤ ለዚህ ነው በአማርኛ ነጻነት ስንል ለጅምላው፣ ለጠቅላላው እንጂ ለግለሰብ አድርገን አንገነዘበውም፤ የአገር ነጻነት፣ የሕዝብ ነጻነት በሚገባ እናውቃለን፤ ስለአገር ነጻነትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎ የታወቀ ነው።

የግለሰብ ነጻነትን ግን እንደዋናና እንዳስፈላጊ የሰው ባሕርይ አድርገን አናየውም፤ የግለሰብ ነጻነት ለአዳፍኔ በጣም አደገኛ ነው፤ የግለሰብ ነጻነት በተስፋፋበት ሕዝብ መሀከል የአዳፍኔ ኃይልና ተሰሚነት በጣም ደካማ ይሆናል፤ስለዚህም አዳፍኔ የሚሰብከው





ነጻነት የጅምላ ነጻነትን ነው፤ አዳፍኔ የሚሰብከው ነጻነት ለሱ ሥልጣን እስኪ የሚሆነውን ሁሉ ለመቋቋም መሣሪያ የሚሆነውን ነው፤ ይህ ነጻነትን እንደግለሰብ ሳይሆን እንደጅምላ አገራዊ ባሕርይ ብቻ አድርጎ መመልከት ከባድ ጉድለት አለበት፤ ዋናው ጉድለቱ ትምህርት በግለሰቡ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን የእድገትና የመሻሻል ኃይል ነቅሎ ያስወጣዋል፤ የትምህርት ኃይልና የመራባት ችሎታ ከግለሰብ ነጻነት ጋር የተሳሰረ ነው፤ የግለሰብ ነጻነት በሌለበት ትምህርትና እውቀት ይመክናሉ፤ ከግለሰብ ነጻነት ማጣት ጋር ተያይዞ የሚመጣው የትምህርትና የእውቀት መምከን የኅብረተሰብና የአገር መምከን ነው፤ መክሸፍ ነው፤ ስንጀምር ማሰብ የግለሰብ ሥራ ነው ብለናል፤ ማናቸውም ዓይነት እድገት የግለሰብ የማሰብ ውጤት ነው፤ ግለሰቡ በነጻነት በሀሳቡ መጋለብ በማይችልበት ማኅበረሰብ በማናቸውም ዓይነት እውቀት መራመድና እድገትን ለማኅበረሰቡ ማምጣት አይቻልም።

## ትምህርትና ውጤቱ

ትምህርትና እውቀት በመሠረቱ ዓላማቸው የኑሮን ጣጣ ለመቋቋምና ሕይወትን የተደላደለና አስደሳች ለማድረግ ቢሆንም የሰውን ልጅ እውነተኛ ባሕርይ አጉልቶ ማውጣቱ ዋናው ነው፤ የሰው ልጅ በመንፈሳዊነቱ፣ በአእምሮው አሳቢነቱ፣ በፍቅርና በመተሳሰቡ፣ በዓይነ አእምሮው የወደፊቱን ለማየት ባለው ችሎታው ከእንስሳት የተለየ መሆኑን የሚያሳይበትን ሁኔታ መፍጠርም ከዋና ውጤቱ አንዱ ነው ለማለት ይቻላል።

እውቀት ዓላማን፣ ፈቃደኛነትን፣ ጥረትንና ችኮነትን ይጠይቃል፤ እውቀት ከማስተዋልና ከማሰብ የሚመጣ ነው፤ ማስተዋልም ሆነ ማሰብ የግለሰብ ሥራዎች ናቸው፤ በደቦ ወይም በጎሣ ማሰብ አይቻልም፤ ማኅበረሰቡ ማሰብ ትልቅ ሥራ መሆኑን ተረድቶ የሚገባውን ዋጋ የሚከፍለው ሲሆን የማሰብ ሥራ ይስፋፋል፤ የማሰብ ሥራ ሲስፋፋ እውቀት ይስፋፋል፤ እውቀት ሲስፋፋ ኑሮ ይሻሻላል፤ ማኅበረሰቡ ያድጋል፤ የማሰብ መሣሪያና የእውቀት ምንጭ የሆነው አእምሮ የግለሰብ ሀብት ነው፤ ይህንን

እውነት ያላወቀና ያልተቀበለ ማኅበረሰብ ባለበት ቆሞ ይቀራል፤ አእምሮ የግለሰብ ሀብት መሆኑን አለማወቅ የሚያስከትለው ጠንቅ በእውቀት ወደኋላ መቅረትን ብቻ አይደለም፤ ለእድገት በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ጉዳዮችንም ይነካል፤ ለምሳሌ ሕጋዊ ሥርዓት የሚቆመው በግለሰብ ላይ ነው፤ ሕግን የሚያከብረው ወይም የሚጥሰው ግለሰብ ነው፤ የሚሽለመው ወይም የሚቀጣው ግለሰብ ነው፤ መብትንና ግዴታን ከነጣጣቸው የተጎናጸፈው ግለሰብ ነው፤ የሚሞቀውም ሆነ የሚበርደው ግለሰብ ነው፤ የሚራበውና የሚጠማው ግለሰብ ነው፤ የሚኖረውና የሚሞተው ግለሰብ ነው።

## ትምህርትና ኀሠኛነት

ራሱን እንደነጻ ሰው፣ እንደግለሰብ ማየትና በዚያው መሠረት መወሰን የማይችል ፍጡር ከአየርላንድም ይምጣ ከፓኪስታን፣ ወይም ከስኮትላንድ፣ ከኢትዮጵያም ይምጣ ከኬንያ ወይም ከሶማልያ ገና በጣም ዝቅተኛ የሰውነት ደረጃ ላይ ያለ ነው፤ ገና የራሱ ባለቤት አልሆነም ማለት ነው፤ ወደግለሰብነት ደረጃ ላይ ያልደረሰና የግለሰብነትን የኃላፊነት ባለቤትነትን ያልተረዳ በሰውነት ደረጃ ዝቅተኛ ነው፤ ከዚህ በፊት መለስ ዜናዊ በጠቅላይ ሚኒስትርነት መቀጠልና አለመቀጠሉን ሲጠየቅ ደጋግሞ ጉዳዩ የሚወሰነው በእርሱ ሳይሆን በፓርቲው እንደሚሆን ተናግሮ ነበር፤ ነገር ግን እሱ በስንት ሰዎች ሕይወት ላይ ውሳኔ እንደሰጠ ስንገነዘብ እምነቱ የከሸፈ እንደነበረ ለመረዳት አያዳግትም፤ መለስ ዜናዊ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ፓርቲውን ሳያስፈቅድ የሚፈጽማቸው ነገሮች ከሚያስፈቅዳቸው በጣም የበዙ መሆናቸው አያጠራጥርም፤ እንኳን በዚህ ዓለምና በወዲያኛውም ቢሆን ጽድቅና ኩነኔ የግል ነው።

ይህንን ያልተማረ ወይም ያልተገነዘበ ግለሰብ ከእንስሳት ደረጃ አልወጣም፤[18] ነገር ግን ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ፣ በዩኒቨርሲቲ

የሚያስተምሩና የሚማሩ ሰዎች በኀሠኛነት ሕመም ተይዘው እየተሰቃዩ ማደግና መሻሻል የሚባሉት ነገሮች በየት በኩል ገብተው አእምሮአቸው ውስጥ ቦታ ያገኛሉ? አእምሮ ክፍት መሆን አለበት፤ አእምሮ ነጻ መሆን አለበት፤ አእምሮ ከጥላቻና ከቂም እድፍ መጽዳት አለበት፤ አእምሮ በሕገ ኀልዮትና በተጨባጭ ማስረጃዎች የመማረክ ልማድ እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ እድገትንና መሻሻልን አዝሎ የሚመጣው ለውጥ ምንጩ የግል አእምሮ ነው፤ ሥምረቱና መገለጫው የሚታየው ግን በሕዝብ ላይ ነው፤ ስለዚህም በሀሳብ ደረጃ አመራር ሰጪ ነው የሚባለው የተማረውና የተመራመረው፤ አእምሮው በሕገ ኀልዮት እንዲያስብ የሠለጠነው ሰው ወርዶ ወርዶ የወጣበት ማኅጸን ላይ የሚያተኩር ሲሆን ሰፊውን ዓለም፣ ሰፊውን አገር፣ ብዙውን የሰው ልጅ፣ ብዙው ሕዝብን ከትኩረቱ የሚያወጣ ብቻ ሳይሆን ከአንድ ማኅጸን ውጭ ካለው ሁሉ ጋር የሚያጋጭ ይሆናል።

[18] በዚህ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ነገርና የብዙ ሊቃውንትን አስተያየት ለማወቅ ለሚፈልጉ በእንግሊዝኛ ያሳተምሁት «The Horn of Africa: Conflict and Poverty, Addis Abeba, 1999» በተለይ Chapter I Social Development and the Individual የሚለውን በጥሞና ማንበብ ብዙ ውዥንብሮችን ከአእምሮ ለማጽዳት ይረዳል።

# የመክሸፍ መሠረት
## ምዕራፍ ፩

መነሻ

ገና ከመጀመሪያው ስነሣ መክሸፍ የሚለውን ቃል የምጠቀምበት ትርጉም እንዴት ያለ እንደሆነ እንደሚከተለው ገልጬ ነበር፤---

መክሸፍ የምለው አንድ የተጀመረ ነገር ሳይጠናቀቅ ወይም ሳይሳካ እንቅፋት ገጥሞት መቀጠል ሳይችል፣ ዓላማው ሲደናቀፍና በፊት ከነበረበት ምንም ያህል ወደፊት ሳይራመድ መቅረቱን ነው፤ የእድገት፣ የመሻሻል፣ የመለወጥ ጉዞ መቋረጥን የሚያመለክት ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ታሪክ አብዛኛውን ጊዜ ከታችኛው ደረጃ ወደላይኛው ደረጃ የሚያደርስ፣ ከተንሳቀሰ ኑሮ ወደተሻለ ኑሮ የሚያመጣውን ጉዞ የሚያመለክት የእድገት ጎዳና ሆኖ ይታያል፤ አንዳንድ ጊዜ ግን አንዳንድ ሥልጣኔዎች ቶሎ ያብቡና ሳያፈሩ ቶሎ ይደርቃሉ፤ ደርቀው አይቀሩም፤ ተፈጥሮ ቆሞ መቅረትን አይደግፍም፤ለውጥ ግዴታ ነው፤ወደተሻለ ደረጃ ካልተለወጡ ወደባሰ ደረጃ መውረዱ የማይቀር ነው፣ወይም በሌላ አነጋገር ካላደጉና ካልተሻሻሉ መሻገትና መበስበስ፣ በስብሶ መፈራረስ ግዴታ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ መክሸፍ ለብዙ ምዕተ-ዓመታት ግዙፍ ቦታ የያዘ ይመስለኛል፤ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ የማውቀው አንድም ጥናት የለም፤[19] አንድም ኢትዮጵያዊ የታሪክ ምሁር ይህንን ጉዳይ የነካ አላውቅም፤ ይህ ራሱ ኢትዮጵያውያት

[19] የጥንቱ ሮም አወዳደቅ ብዙ ጥናቶች ተደርገውበታል፤ በሌሎችም የአውሮፓ አገሮች ተመሳሳይ ጥናት አለ፤ የውድቀቱን ወይም የመክሸፉን ምክንያት ካላወቁ እየከሸፉ መቀጠል የማይቀር ይሆናል።





የታሪክ ሊቃውንት ዓላማቸው ከኢትዮጵያ ውጭ መሆኑን፤ ወይም ታሪክን የሚያዩት እንደተረት መሆኑን ያመለክታል፤ መነሻ የሌለው፣ አቅጣጫ የሌለውና ዓላማ የሌለው አድርገው በጊዜ በታጠረ ብቅ-ጥልቅ ውስጥ የሚነገር ተረት አድርገውታል።

ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ እንድ አስተማሪው ያስታጠቀውን ጉዳይ ይዞ አንድ መጽሐፍ አሳትሞአል፤[20] በሀያኛው ምዕተ-ዓመት በኢትዮጵያ ውስጥ የለውጥ ፈር ቀዳጆች የሆኑ ሊቃውንት የሚላቸውን መርጦ በነሱ ታሪክ ዙሪያ ከኢትዮጵያ የትምህርት፣ የማኅበራዊ፣ የነገረ ንዋይና የፖሊቲካ ጉዳዮች ጋር እያነካካ መተንተኑ ግሩም ሥራ ነው፤ ከዚህ በፊትም ያልተሠራ አዲስ ነገር ይመስለኛል፤ ነገር ግን አንደኛ ለኢትዮጵያውያን አልተጻፈም፤ ሁለተኛም ከመጀመሪያው አልጀመረም፤ በኢትዮጵያ የትምህርት ገበታ ያሰፋትን ሊቃውንት ዜሮ ለማድረግ ቢዳዳውም፣ እንደብላቴን ጌታ ኅሩይ ያሉትን በቸልታ ለማለፍ አልቻለም፤ ሌሎችን ለማየት ግን አልቻለም፤ ባሕሩ የፈረንጁ ትምህርት ፍሬ በመሆኑ የጥንቱን ሳያውቀው ይችላል፤ ታዲያ ሊቅነት የማያውቁትን ለማወቅ መጣር አይደለም እንዴ? የጥንቶቹ ሊቃውንት በትምህርት፣ በፍትሕና በአስተዳደር፣ እንዲሁም በሥነ ጥበብ ያደረጉት አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም፤ የጸሐፌ ትእዛዝ ሹመት ከቤተ ክህነት ትምህርት ወደፓሪስ ዩኒቨርሲቲ ቢተላለፍም፣ ትእዛዝ ከመጻፍ አልወጣም፤ በፈረንጅ አገር ለተማሩት ሊቃውንትም. ቢሆን ባሕሩ ከመተረት አላለፈም፤ በመደምደሚያውም እነዚህ በየፈረንጅ አገሩ የተማሩ ሊቃውንት ምንም ለውጥ አላመጡም፤ የከሸፉ ነበሩ፤ ለምን እንደከሸፉ ባሕሩ ሊነግረን አልቻለም፤ ምክንያቱም መክሸፋቸውን እሱም ራሱ አልተገነዘበም ወይም አልተቀበለም፤ ወይም ...

የመክሸፍ ምንጭ

በዋናነት የመክሸፍ ምንጩ ሁለት ይመስለኛል፤ አንደኛው ትናንትን አለማስታወስ ሁለተኛው ነገን አለማሰብ፤ ትናንትን አለማስታወስ ማለት ታሪክን አለማወቅ፣ የወጣነውን ዳገትና የወረድነውን ቁልቁለት ለይተን አለመረዳት፣ ዳገቱን እንዴት እንደወጣንና ቁልቁለቱን እንዴት እንደወረድን በትክክልና በእውነት አለመገንዘብ ናቸው፤ ክብርንና ኩራትን ማን ወይም እነማን እንዳስገኙልን ተጨንቀን ሳናስብና ሳንመዝን ለማይገባው እንሰጣለን፤

[20] Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century, Addis Abeba, 2002.

ውጤቱም የሠራው እየተረሳና እየኮሰሰ፣ ያልሠራው እየተወሳና እየተወደሰ ከትውልድ ወደትውልድ ይተላለፋል፤የተገፋው ያንጎራጉራል፤

*እናት ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፤*
*የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ፤*

ስለዚህም መሥራት የማያስከብርና የማያከብር ይሆናል፤ ስለዚህም የሚያስከብረውና የሚያከብረው ሥልጣን ብቻ ከሆነ እንደምንም ብሎ ወደሥልጣን በመጠጋት ሳይሠሩ ለመክበርና ለመከበር መጣር ባህል ይሆናል፤ በኢትዮጵያ ሆኖአልም፤ ታሪክ የሠራተኞች፣ የጠቢባንና የአዲስ ነገር ፈጣሪዎች፣ የሊቃውንትና የአሳቢዎች አይሆንም፤ ታሪክ የክፉ ሰዎች፣ የሰነፍ ሰዎች፣ የተንኮለኞችና የጨቋኞች፣ የጀብደኞችና የግፈኞች ውዳሴ ይሆናል፤ በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደሰ!

ትናንትን በትክክል ካላስታወሱ ነገን በትክክል መገንባት አይቻልም፤ ለነገም የትናንትን መልክ ሰጥተን ነገንም ትናንትን ለማስመሰል እንጮኩራለን፤ ነገን እንፈራዋለን፤ ነገን የምንፈራው በሁለት ምክንያቶች ነው፤ አንዱ ነገ አዝሎ የሚመጣውን አለማወቃችን ነው፤ ሁለተኛው ምክንያት ነገን በፍላጎታችን ለመቅረጽ ችሎታም ሆነ ብቃት እንደሌለን ራሳችንን በማሳመን ነው።

| *እኛና ይቺ መሬት - ሕይወትና ሞት* |
|---|
| *መስፍን ወልደ ማርያም /በግል/[21] 1989* |
| *ልደት የሞት ዋዜማ ነው። ሕይወት የሞት ጥሪ ነው። ኑሮ የሕይወት ጻዕር ነው። እንስሳት ይህንን እውነት አያውቁም። ይወልዳሉ፤ ተፈጥሮ የሚያስገድዳቸውን ሁሉ ፈጽመው ይሞታሉ። ለእንስሳት ሕይወት፤ኑሮና ሞት የተፈጥሮ ግዴታዎች ናቸው።* |
| *የስፔይኑ ፈላስፋ ኦርቴጋ ኢ ጋሴት እንዳስገነዘበን በሰው ልጅና በእንስሳ መሀከል ያለው ትልቁና ዋናው ልዩነት የማስታወስ ችሎታ ነው። የዛሬ ስድስት ሺህ ዓመት የተወለደ ማናቸውም እንስሳና ዛሬ የሚወለድ እንስሳ ምንም ልዩነት የላቸውም። ሁለቱም* |

[21] በግል የምለው በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በምሠራበት ጊዜ ወያኔ የምናገረውን ሁሉ ከፖሊቲካ ጋር በማያያዝ ኢሰመጉን ለመወንጀል ስለሚሞክር፣ ኢሰመጉን ለማዳን በግል እያልሁ እጽፍ ነበር።





*ሕይወታቸውን የሚገፉትና ኑሮአቸውን የሚያራምዱት በተፈጥሮ ግዴታቸው መሠረት እያንዳንዱን ቀን ልክ እንደአዲስ እየጀመሩት ነው። ትናንት የለም። ነገ የለም። አሁን ብቻ!*

*የሰው ልጅ ግን ከአለፉት ትውልዶች የሚወርሰው ሀብት አለው። ሀብት ሲባል ግዙፍ ንብረት ብቻ ሳይሆን የአእምሮ እድገትንና የሥራ ችሎታን መሻሻል፣ ሥርዓትን ሕግን አበጅቶ የመኖርንና የመደጋገፍን፣ የመማማርንና የመተራረምን፣ የመተሳሰብንና የመረዳዳትን፣ የመፈቃቀርንና የመከባበርን የመንፈስ ቅርስንም ሁሉ ይጨምራል።*

*አሁን በከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ደርሰው በሀብታምነታቸውና በኃያልነታቸው የታወቁት አገሮች የእንስሳ ባሕርያቸውንና የተፈጥሮ ዝንባሌአቸውን አሸንፈው ሰብአዊ ወይም የሰውነት ባሕርያቸውን ያዳበሩት ናቸው። በአሜሪካኖችና በእኛ፣ ወይም በጃፓኖችና በእኛ በኢትዮጵያውያን (ሌሎችም እንደኛ ባሉ) መሀከል ያለው ልዩነት ይኸው ከሰውነትና ከእንስሳ ባሕርይ የትኛው የማየሉ ጉዳይ ብቻ ነው። ገና ከክርስቶስ ልደት በፊት ሶቅራጥስ እንዳስተማረው መማር ማለት ማስታወስ ነው፤ ማስታወስ ማለት መማር ነው። መማር በተማሪ ቤት ገብቶ ዓመታትን መቁጠር ብቻ አይደለም። ማስታወስ የምንችል ከሆነ ከኑሮአችንና ከአካባቢያችን በየቀኑ የምንማረው ብዙ ነገር አለ። ስንጀምር በሥልጣኔ ከቀዳሚዎች ሆነን ዛሬ ከውራዎቹ ጋር የቆምንበት ምክንያት ሌላ አይደለም። የእንስሳት ባሕርያችን ከሰውነት ባሕርያችን ላይ በማየሉና የማስታወስ ችሎታችን ዝቅተኛ በመሆኑ ነው።*

*አርኖልድ ቶይምቢ የሚባል የእንግሊዝ የታሪክ ፈላስፋ ኢትዮጵያንና ጃፓንን ያወዳድራል። ሁለቱም አገሮች በምዕራባውያን የጦር ኃይል የመመታትንና የመሸነፍን ውርደት የቀመሱት በተቀራረበ ጊዜ ውስጥ ነበር ይላል። እ.ኤ.አ. በ1853 በአሜሪካ ጦር፣ በ1863 ደግሞ በተቀነባበረ የምዕራባውያን ጦር ጃፓን ተመታች። ኢትዮጵያ ደግሞ በ1868 በእንግሊዝ ጦር (በናፒየር አዝማችነት) ተመታች። ለጃፓኖች ውርደቱ የማይረሳ ትምህርት ሆናቸውና መሳፍንቱና መኳንንቱ አገራቸውን ወደምዕራባውያን ሥልጣኔ ለማስገባት ሲሉ የክብራቸውን ልዩ መብትና ሥልጣን በፈቃዳቸው ለቀቁ። የጃፓን የእውቀት ኃይል በጣም ዳብሮ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሜሪካንን በጦርነት ለመጥራት በቃች፤ ጉልበትዋ የተሰበረው በአቶሚክ ቦምብ ነበር። የአቶሚክ ቦምብ*

የተፈተነባት የመጀመሪያዋ አገር ሆነች። አቶሚክ ቦምብ በጃፓን ላይ ብቻ መጣሉ ዘረኛነትንና ጃፓንን እስከመጨረሻው ለመስበር ፍላጎት እንደነበር ያመለክታል። ሆኖም ዛሬም ጃፓን ምዕራባውያንን ቀድማ ትገኛለች።

ቶይንቢ እንደሚለው ኢትዮጵያውያን ግን ከናፒየር ዘመቻ ምንም ሳይማሩ ሁለት ትውልዶች አልፈው እንደገና ለማይጨው ውርደት ተዳረጉ። በጃፓኖችና በእኛ መሀከል ያለው ልዩነት የማስታወስ ችሎታ ነው። ሁልጊዜም የትናንትናውን ሳናስታውስ ዛሬ በአዲስ ለመገንባት የምንሻ ነን። ለእኛ ትናንት የለም፤ ዛሬ ብቻ። የናቁን እንተወውና ማነው ዛሬ በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ የተፈፀመውን ግፍ የሚያስታውስ? እንኳን አዲስ አበባና አሥመራም ተረስቶአል። ወጣቶቹማ በፍጹም አያውቁትም። የአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ የአርበኞች ታሪክ በጥንቃቄ ተፅፎ ለትውልድ እንዲተላለፍ አልፈለገም። ማስታወስ አንፈልግም። የደርግ አገዛዝ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ አወዳደቅ ምንም የተማረው የለም። የወያኔ አገዛዝ ከደርግ አገዛዝና አወዳደቅ ምንም አልተማረም። ለአፄ ኃይለ ሥላሴ፣ ለደርግ፣ ለወያኔ፣ ትናንት የለም። ነገ የለም፤ ዛሬ ብቻ።

ይህ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው? በእንስሳት ዓለም የሁሉም ነገር ሚዛን ጡንቻ ነው። አእምሮ፣ መንፈስ፣ ማሰብና መተሳሰብ፣ ሕግና ሥርዓት፣ ፍትሕና ነፃነት፣ እኩልነት፣ ሕይወትና ክብር ዋጋ የሌላቸውና ሚዛን ውስጥ የማይገቡ ናቸው። ኢትዮጵያም ውስጥ እንዲሁ ነው። ሕግና ሥርዓት ከሌለ መተማመን ሊኖር አይችልም። በቅርቡ በቴሌቪዥን የታየ ነገር አለ፡[22] የታክሲ ነጂዎች ማህበር 25 ያህል ታክሲዎች አስመጥቶ ለዘጠኝ ወራት ያህል በጉምሩክ ተይዘው ቆመዋል። ታክሲዎቹ ከመምጣታቸው በፊት የፅሁፍ ማረጋገጫ ለባለታክሲዎቹ ተሰጥቶአል። መኪናዎቹ እስኪመጡ ድረስ አዳዲስ ደንቦች ወጥተዋል። ታክሲዎቹም ታክሲ የሚያሰኛቸውን ጠባይ አጥተዋል። እያንዳንዱ ታክሲ በቀን 200 ብር ይሠራል ብንል በዘጠኝ ወሮች ውስጥ 1350000 ብር ኪሳራ ደርሶአል ማለት ነው። አገር የሚለማው እንደዚህ ነው? ባለሀብቶች ማባበል የሚቻለው እንደዚህ እየተደረገ ነው? ትናንት የለም። ነገ የለም፤ ዛሬ ብቻ።

[22] ይህ የሆነው ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት ነው።





ነገሩ በጣም ያስገርማል፤ በጣምም ያሳዝናል። ክርስትናም ሆነ እስልምና ኢትዮጵያ ውስጥ የገቡት ገና በጥንስሱ ሳሉ ነው። ነገር ግን ከስንት ምዕተ ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያ አሁንም ጡንቻና ወርቅ የነገሡባት አገር ነች። ይህንን ማለት ቀላል አይደለም። ስንትና ስንት ሰማዕታትን ከኔ ጋር አዘቅት ውስጥ ለመክተት የምቃጣ ይመስላል። ሰው አላፈሩም እንጂ ሰዎችስ ነበሩ። በኢትዮጵያ ቤተክርስትያን በኩል

በእኔው ዘመን አቡነ ጴጥሮስ ያሉበትን የሰማዕትነትና የክብር ከፍታ ደመና ሸፍኖት ልናያቸው አንችልም። ስለማናያቸውም አናስታውሳቸውም፤ስለማናስታውሳቸውም አያስተምሩንም። እንዲያውም ስለሳቸው የተደረሰው የጸጋዬ ገብረ መድኅን ቴያትር እንዳይታይ የዛሬው አገዛዝ መከልከሉ እንደሳቸው ዓይነቱን ለማስታወስ የማንፈልግ መሆናችንን ያሳያል። ደርግ አፄ ኃይለ ሥላሴ እስከናካቴው መፈጠራቸውን ወደመካዱ ተቃርቦ ነበር።

በሰማዕቶቻችን ላይ የምንፈፅመው ግፍ አለማስታወሳችን ብቻ አይደለም። እንዲያው ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል - በላይ ዘለቀን ሰቅለናል። አበበ አረጋይን፣ መስፍን ስለሺን፣ ብዙ ሌሎችንም በጥይት እየደበደብን ገድለናል። የኢትዮጵያ ጡንቻኞች ወይም ጉልበተኞች የኢትዮጵያውያንን የመስዋዕትነት ተግባር ከሚዛናቸው ውስጥ ሳያስገቡ ፈርደው ገድለዋቸዋል። የሞቱት ሁለተኛ ሞት ነው። እንደኛ ሰማዕታቱን የሚገድል ሌላ ሕዝብ እኔ አላውቅም። ሌሎች ሕዝቦች ለሰማዕቶቻቸው ሐውልት ይሰራሉ። ገድላቸውን ይፅፋሉ። መታሰቢያ ያቆማሉ - ለሚቀጥለው ትውልድ አርአያ እንዲሆኑ።

አንድ ቀን ከውጭ ስመለስ አውሮፕላን ማረፊያ ደራርቱ ቱሉ ከእኛ ጋር ተሰልፋ አየሁአት። ስንቱ እዚህ ግባ የማይባል ክብር ተሰጥቶት በክብር መግቢያው በኩል ሲገባ ደራርቱ ቱሉ ተራ ሆና ተሰልፋለች። እንደእስዋ ዓይነቱን ሰው ማክበሩ ውርደት መስሎ የሚታያቸው አሉ። እኛ አርአያ የማንፈልግ፣ አርአያ የሌለን ሕዝብ ነን። በጡንቻ የአገዛዝ ወንበሩ ላይ የወጣ ሁሉ ከእኔ በፊትም ይሁን ከኔ በኋላ መሪ አልነበረም፤ አይኖርምም በማለት ነው እንደእንስሳ ከባዶ ለመነሳት የሚሻው። መሪው እንዲህ እዝጭ ብሎ ወደእንስሳ ደረጃ ሲወርድ ተመሪው ሕዝብ በሰውነት ደረጃ ላይ ሊሆን አይችልም። አይችልም ማለት ከባድ ነው። የራሱን የሰውነት ደረጃ

ለመጠበቅ ሕዝቡ መሪውን ለመለወጥ የመንፈስ ወኔው ካለው ይችላል። አይችልም የምለው ከባድ ነው ለማለት ነው። ለዚህ ነው ወደእንስሳነቱ የምንጠጋው። የማስታወስ ችሎታችን ተሟጧል። አንዳንዴ ስለሰማዕቶቻችን ማውራት የሚቃጣን ራሳችንን ካለንበት የእንስሳ ደረጃ ያወጣን እየመሰለን ስንመፃደቅ ነው።

የሸዕቢያ ወንድሞቻችን ከዚህም አልፈው የማስታወስ ችሎታቸውን ከደውታል። አባቶቻቸውን ከደዋል። የአባቶቻቸውን እምነት ከደዋል። የአባቶቻቸውን ታሪክ ከደዋል። አባቶቻቸው ለኢትዮጵያ መሞታቸውን ከደዋል። የማስታወስ ችሎታቸውን ክደው ከእንስሳት ጋር ተዛምደዋል። አዲስ አበባም ቢሆን የኢትዮጵያን ታሪክ የሚክዱና የሚያጎድፉ የዘመኑ መኳንንት ምልተዋል። ባለፉት ስድስት ዓመታት ውስጥ "የኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ አለበት" ብለው በአደባባይ ሲናገሩ የሰማሁት አቶ ስዬ አብርሃን ብቻ ነው። ለሳቸውም አልበጃቸው ይሆናል። ለመሆኑ ሌሎቻችንስ ምን እያደረግን ነው? ምንም። ወሬ እንደሥራ ካልተቆጠረ በቀር። ማውራትም የሚፈሩ ሞልተዋል።

እኛ ለሆዳችን፣ ለምቾታችን፣ በአጠቃላይ ከሌሎች በልጠ ለመታየት ፋታ የማይሰጥ ግብግብ ውስጥ ነን። በዚህ ግብግብ ውስጥ አገር አይታሰብም። ወገን አይታሰብም። በግፍ የሚሰቃየው ሁሉ አይታሰብም። ታሪክ፣ የሩቁ ሳይሆን የትናንቱ ታሪክ አይታሰብም። ትልቁ ብሶትና ምሬት ኤርትራውያንና ትግሬዎች ቀደሙን፣ አሁን ደግሞ ታምራት ላይኔ ቀደመን ነው።

ብሶትና ምሬቱ ስለሕግና ስለሥርዓት አይደለም። ይህ ነው ሌላው የእንስሳነት ምልክቱ። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በከተማም ሆነ በገጠር ለመሬት የነበረው ግብግብ በዘመኑ የነበረ ሁሉ የሚያውቀው ነው። መሬት ከደሀው እየተነጠቀ ወይም በነፃ እየተገኘና እየተሸጠ ቪላዎች ተሠርተው ነበር። ደርግ ሲመጣ የበቀልና የምቀኝነት ስሜቱ ዓይኑን ጋርዶት ስለነበር "ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ" እያለ በልፋታቸውና በላባቸው ያገኙትንም በአንድ ላይ ዘረፋቸው። በአንድ ቀን የነበረው ሁሉ የሌለው ሆነ። ለፍቶ ማግኘት ኃጢአት ሆነ። ይህ የደርግ ፍርደ ገምድልነት ዛሬም አልታረመም። እንዲያውም ያላፈሩትን ሀብት በጨረታ በመግዛት በሰው ንብረት ከብረው የመኖር ሽሚያ ተጀምሮአል። ለንብረቶቹ እውነተኛ ባለቤቶች የሕግ ፀሐይ ሳይወጣላቸው ይቀራል ብለው ነው? ወይስ እንደእንስሳ በልቼ





ልሙት ነው? ለፍተው ላካበቱት ሰዎች ያልሆነ ንብረት ከዘራፊ ለገዛው ይረጋሰታል ብሎ ማሰብ ለአገሪቱና ለሕዝቡ ትልቅ ስድብ ይመስለኛል፣ ስድብ የሚሰማው ሰው ካለ።

ከትናንቱ ታሪክ መማር የማይችል ሕዝብ ከስሕተቱ አይማርምና ስህተቱን እንደ እንስሳ እየደጋገመ ይኖራል። ትናንት በሌሎች ላይ ሲፈፀም ያየነውን ግፍ ዛሬም እንዲቀጥል ተባባሪ መሆን ለራስ ሳይሆን ለልጅና ለልጅ ልጅ ፍዳን ማውረስ ነው። ይህም ያው እንደ እንስሳ መሆን ነው። ቆም ብሎ ላሰበ በልፋቱና በወዙ ያፈራውን በሚነጠቅበት አገር በማጭበርበርና በዘርፊያ ያገኘው ወደፊት የማይወረስበት ምን ምክንያት አለ? ትናንት አያስተምር። ነገ አይታሰብ፣ ዛሬ ብቻ።

አረ ለመሆኑ ልጆች የሚወለዱት ለምንድን ነው? እንስሳት የተፈጥሮ ግዴታ የሆነውን ፍትወተ ስጋ ሲፈፅሙ ልጆችን ይወልዳሉ። ልጆቻቸውን ከጥቃት ሲጠብቁም ለሕይወታቸውም ባለመፍራት ነው። ዶሮ ጫጩቶችዋን ከጭልፊት ስትከላከል ያላየን የለንም። ለሰውም እንደዚሁ። ልጆች የሚወለዱት የተፈጥሮ ግዴታ ውጤት ሆነው ነው? ወይስ ተፈልገው? አሜሪካውያንና አውሮፓውያን ባልና ሚስቶች ልጅ የሚወልዱት ልጅ እንውለድ ወይስ መኪና ወይ ቤት እንግዛ? የትኛው ይቀድማል? ተባብለው ተማክረው ነው። "በዕድሉ ያድጋል" የሚባል ነገር የለም፣ እንደኛ በጣም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃካሉት በስተቀር። ልጅ መውለድ ከባድ ኃላፊነት አለበት። ማብላትና ማጠጣት፣ ማልበስና ማስተማር ብቻ አይበቃም። ልጆቹ የሚኮሩባቸው አባትና እናት ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል። ቢያንስ ሲያፍሩባቸው አይገባም። የመጣውን ነፍጠኛ ሁሉ እየተለማመጡና እሱን እያላሱ መሸኘት ውርደት ከመሆኑ ሌላ የልፋትን ውጤት ለልጅና ለልጅ ልጅ ለማስተላለፍ አይረዳም። አፄ ኃይለ ሥላሴና መኳንንቶቻቸው ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ምን አተረፉ? ይኸው በሥርዓት እንዲቀበሩ እንኳን ለማድረግ በፍርሃትም ይሁን በምቀኝነት ሳይቻል ቀርቶአል። ኮሎኔል መንግሥቱና ጓደኞቻቸውስ? በቅርቡ አንድ ጋዜጣ ላይ የተዛፈው እውነት ከሆነ የአቶ መለስ እናት ስጋትም ይኸው ነው። የእናትነት ልባቸው ያለፈውን ታሪክ በግዴታ አስታውሶአቸው ነው። አቶ መለስ ግን አያስታውሱትም።

የግሪኩ ፈላፋ ሶቅራጥስ ማሰብ•የሚችል ሰው እንጂ ትንቢት ተናጋሪ ነቢይ አልነበረም፦አምስት ምቶ ዓመታት ከክርስቶስ ልደት

በፊት እንዲህ ብሎ ነበር "የግፍ አገዛዝ ቁንጮው ላይ ያለውን ሰው እንቅልፍ ያሳጣዋል። ደህና ደህና ሰዎችን አያስጠጋም። የሚከበበው በአልባሌዎች ነው። እነሱም ቢሆኑ በልባቸው ይጠሉታል። ስለዚህም ጠባቂዎች በብዛት ይመለምላል። በየጊዜውም ይለዋውጣቸዋል። ከአስጠጋቸውም ውስጥ የተሻሉት በየጊዜው ወደ ውጭ እየሄዱ ወይም እየተሰወሩ ይከዱታል።" ይላል። ግፈኛ ገዢን "ፈሪ ወዳጅ የሌለው፣ የክፋት ሁሉ ማህደር፣ አብድ፣ የምኞቱ ባሪያ" ይለዋል። "በአገሩ ሰዎች ጠባቂዎች መግዛት ካልሆነለት ሕዝቡን በሌላ አገር ሥር በባርነት ቀንበር ውስጥ ለማስገባት አይመለስም።" ይላል ሶቅራጥስ።

አንድ የእንግሊዝ ምሁር እንዳለው ማንኛውም ሕዝብ የሚያገኘው መንግሥት የሚገባውን ነው። የማይስማማው ከሆነ የመለወጥ ኃይል አለው። ግፍን የለመደና በጉጉት የሚኖር ደሀ ሕዝብ መለማመጥንና መለመንን ባህሉ ያደርጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀሎት የግፉን ፅዋ ሲግቱት ነፍስ እስክትወጣ ድረስ ትዕግስት እንዲኖረው ነው። ያንን ግፍ እንዲታገልና እንዲያሸንፍ ኃይልና ብርታትን አይለምንም። የገዛ መብቱን ለማስከበር ከሚከፍለው ቀንሶ ጉቦ ይከፍላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ምድራዊ ባለሥልጣኖችንና ሰማዕታቱን፣ መላዕክቱን፣ ማርያምንና እግዚአብሔርንም ጭምር በልመና ለመደለል ይሞክራል። ስዕለት ምን ማለት ነው? "ይህንን ያደረግህልኝ እንደሆነ ይህንን አደርግልሃለሁ" ማለት ነው። ሀያዋን ለነገሥታት፣ ሙታን ለካህናት ይገብራሉ የሚለውን የባህል መግለጫ ልብ በሉት። እየታወቀ ነው ማለት ነው። "ለሰዎች ሲሆን እጅ መንሻ፣ ገፀ በረከት ወይም ጉቦ ማለት ነው። ዓላማው ያው ነው። ይህንን አድርግልኝና ይህንን እሰጥሃለሁ።" ማለት ነው። ሕግንና መብትን ተገን አድርጎ በልበ ሙሉነትና በክብር ማስገደድ ሲቻል በመልፈስፈስና በመለማመጥ፣ ካልሆነም በጉቦ በመደለል ኑሮን ለመግፋት ይሞክራል። ነገም፣ ተነገ ወዲያም ያው ማላስ ነው። ባለሥልጣኑም ማላስ ያስለመደውንና ሀብታም ባየ ቁጥር እንደ ፓቭሎቭ ውሻ ለሀጩ ይዝረከረካል፣ ጥፋ ለጥፋ ሲገናኙ። ትናንት የለም፣ ነገ የለም፣ ዛሬ ብቻ።

በየጊዜው የሚመጡትን ሹማምንት ጎትቶ የመንፈስ አዘቅት ውስጥ የሚጨምራቸው ማን ነው? አፄ ኃይለ ሥላሴ ከስደት እንደተመለሱ በአርበኞችና በእውነተኛ የውስጥ አርበኞች ላይ የሚፈፀመውን በደል እኔ ሰማቸውንና ታሪካቸውን እንጂ በአካል





የማላውቃቸው ሰው በዚያን ዘመን አፄ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት በቲያትር መልክ አሳይተውት ነበር ይባላል። ሰውዬው ዮሐንስ ረምሐ የሚባሉ የትግራይ ሰው ነበሩ። በኢጣልያ ወረራ ጊዜ የውስጥ አርበኛ ሆነው ጠጅ እያስነገዱ በሚያገኙት ገንዘብ ጥይት እየገዙ ለአርበኞች ይልኩ ነበር። ጃንሆይ ከተመለሱና ዙፋናቸውን ከያዙ በኋላ ባንዳች በአርበኞችና በስደተኞች ላይ አይለው በማየታቸው የተሰማቸውን ቅሬታ በቲያትር አሳዩ ሲባል ከእውነተኛ ምንጭ ሰምቻለሁ። ቁም ነገሩ ባንዳዎች ለመኳንንቱና ለመሳፍንቱ ጉቦ እየሰጡ የውስጥ አርበኞች ይባሉ እንደነበረ ለመግለፅ ነበረ። ዮሐንስ ረምሐም በግዞት የሞቱ ይመስለኛል።

የደርግን ሹማምንትስ የመንፈስ አዘቅት ውስጥ የከተታቸው ማን ነው? በመርማሪ ኮሚስዮን ውስጥ ከጦር ኃይሉ ክፍል ተመርጠው የመጡ መኮንኖች ነበሩ። ሥራቸውን ከሌላው እኩል ወይም የበለጠ እየሰሩ ደመወዛቸው እንዳንዶቻችን ስናገኝ ከነበረው ግማሽና ከግማሽ በታችም ነበር። ጎሊናዬን ስለከበደው ለኮሎኔል መንግሥቱ ባመለከት "ሁላችንም የምንኖረው በድርው ደመወዛችን ነው። መለወጥ አይቻልም" አሉኝ። በህብት ጉጉት በኩል ሲጀመር የነበረው መንፈስ ንፁህ ነበር ለማለት ይቻላል። ወደ መጨረሻው ላይ የደርግ መኳንንት ሁሉ በአዋጅ የተነገራቸው ይመስል ትልልቅ ቤት ሲያሠሩ አንዱን "እንዴት ነው ገንዘብ ተፈቀደላችሁ ወይ?" ብዬ ብጠይቀው "ይህን ያህል ዘመን አገልግዬ ይህ ይበዛብኝ ወይ?" አለኝ። እኔም የጠየቅሁት ይበዛበታል ብዬ አልነበረም። "ገንዘብ ከየት መጣ" ለማለት ነበር? ለማናቸውም እነዚያ በአሥራ ሰባት ዓመት ቤት ሰሩ ብለን ስንደነቅ በአምስት ዓመታቸው በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት የሚያካብቱት ተተኩ። "ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ" አለ መንግሥቱ ለማ፤ ነፍሱን ይማረውና። ትናንት የለም። ነገ የለም፣ ዛሬ ብቻ።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሀብት ማለት መሬት ስለነበር በሚሊዮን የሚቆጠር ጥሬ ገንዘብ የነበረው መኖሩን አላውቅም። በደርግ ዘመን በሚሊዮን የሚቆጠር ጥሬ ገንዘብ ያላቸው ተፈለፈሉ። አሁን በኢሕአዴግ ዘመን ደግሞ እንደ አሸን ፈሉ። በደርግና በኢሕአዴግ መሀከል ልዩነቱ አሁን ባለሥልጣኖቹም በቀጥታ ያለምንም ሃፍረትና ይሉኝታ የሥልጣን ብቻ ሳይሆን የሀብትም ባለቤቶች መሆናቸው ነው። ኢትዮጵያን ሬጂስተር በሚባለው አሜሪካ በሚታተም መፅሔት ላይ በተከታታይ የወጣው ፅሑፍ

በማያጠራጥር ማስረጃ የተደገፈ ሆኖ የኢሕአዴግ ሹማምንት በሀብት ዝርፊያ ላይ እንደተሰማሩ በግልፅ ያሳያል። በዚች በደሀ አገር በዕድሜ ሙሉ የማይገኝ የጥሬ ገንዘብ ሀብት በአጭር ጊዜ ውስጥ ማከማቸታቸው የዝርፊያ ስልታቸውን ብቻ ሳይሆን የዝለቂታ ዓላማቸውን ይጠቁማል። ቂልነታቸውንም በጉልህ ያመለክታል። የትናንቱን የማስታወስ ችሎታ ማጣት፣ የወደፊቱን ለማየት እንዴት ብሎ ይረዳል? የትናንቱን ፀሐይ የሞቀውን እውነት ማስታወስ ያልቻለ የነገውን ምሥጢር እንዴት ይረዳዋል? ትናንት የለም። ነገ የለም፤ ዛሬ ብቻ።

የደርግ አገልጋዮች በየእስር ቤቱ ታጉረው በየዕለቱ በየፍርድ ቤቱ እየቀረቡ የተከሰሱበት ወንጀል በራዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ እየተነገረ የወያኔ አገልጋዮች ደግሞ ያንኑ ወንጀል እየፈፀሙ ናቸው። የአሰፋ ማሩ ገዳዮች ነገ እነሱም በእስር ቤት ታጉረው ለፍርድ እንደሚቀርቡ አይታያቸውም። አእምሮአቸውም ሆነ ኅሊናቸውም በሆዳቸው ተጋርዷል። ትናንት የለም፣ ነገ የለም፣ ዛሬ ብቻ፡

ወይዘሮ አለማሽን፤ የአቶ መለስን እናት የእናት ሆዳቸውን እያንሰፈሰፈ የሚያንገበግባቸው ነገ እየታያቸው ነው። "ልጄ መለስ ካለፋት፣ ከቀደሙት የሚማር ይሁን" እያሉ ደጋግመው ተናግረዋል: : አቶ መለስን የሚያንገበግባቸው ደግሞ የነገው አይደለም ዛሬ መታሰራቸው ነው። በነገራችን ላይ ኮሎኔል መንግሥቱም እንደዚሁ ብለው ነበር። በእናትና በልጅ መሀከል ያለው የአስተሳሰብ ልዩነት ድልድይ ሊሰራለት የማይችል መሆኑን ሳስበው የወይዘሮ አለማሽ ጭንቀት በሙሉ ኃይል ይሰማኛል። እግዚአብሔር ፀሎታቸውን ሰምቶ ልጃቸውን ነገን ለማሰብ ያብቃላቸውና የእናት ልባቸውን ከጭንቀት ያድንላቸው።

ጉልበተኛ ነኝ ባዩና አጥቂው ብቻ አይደለም ትናንትንና ነገን የሚረሳው። ሌላውም ምንም ሳያደርግ በምኞትና በፀሎት ብቻ ከጥቃትና ከበደል አመልጣለሁ ብሎ ያስባል፤ የሌላው በደልና ጥቃት አይሰማውም። ወይም ደግሞ ዛሬ የአጥቂው አገልጋይ በመሆኑ ሆዱን ሞልቶ ነገ የሚደርስበትን ጭራሽ አያስበውም። አንድ የኢኮኖሚክስ ሃሳብ አለ። "ለማግኘት ማጣት ያስፈልጋል" የሚል። የእኔ ትርጉም ለመጀመሪያው ግራ የሚያጋባ ቢመስልም ቀላል ሃሳብ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው አንድ ብር ብቻ ኪሱ ውስጥ አለው እንበል። ቡና ለመጠጣት ይፈልጋል። የቡናው ዋጋ አንድ





ብር ነው እንበል። እንግዲህ ሰውዬው ቡናውን ለማግኘት ብሩን ማጣት አለበት ማለት ነው። ብሩንም ቡናውንም ማግኘት አይችልም። ብሩን ከፈለገ ቡናውን ማጣት አለበት። ቡናውን ከፈለገ ብሩን ማጣት አለበት። የኢኮኖሚስት ባለሙያዎቹ ሃሳቡን እንዲህ እንደ እኔ አያቀሉትም። ለማናቸውም ይህ ከገበያው ህጎች አንዱ ነው። ሃሳቡን ያመጣሁት የማላውቀውን ኢኮኖሚክስ ለማስተማር ሳይሆን ለሌላ ሃሳብ መንደርደሪያ እንዲሆነኝ ነው።

ግፍን ለማስወገድና ለሁሉም የሚበጅ ሕጋዊ ሥርዓትን ለመትከል ዋጋ መክፈል ያስፈልጋል። ያለው አማራጭ ዋጋውን ከፍሎ ከግፉ መገላገል፣ ወይም ግፉን ተሸክሞ እያቃሰቱ መኖር ነው። መኖር ብቻ አይበቃም። ለመኖር ብቻ መኖር ለልጅና ለልጅ ልጆች ቀንበሩን ማስተላለፍም ነው። ለአቶ መለስ መድረኩን ልልቀቅና የሚሉትን እንስማ፦

የዴሞክራሲ እጦት ወደባርነት የሚያስጠጋህ ከሆነ ዳቦ አገኘህ አላገኘህ መኖርህ ትርጉም የለውም። ባርያ ሆኖ ከመኖር መሞት ይሻላል። ይህ አዲስ ነገር አይደለም። እንደዛ ስለሆነ ነው የታገልነው። ተገፍተህ፣ ተማርረህ፣ ባርያ ሆነህ ከመኖር ታግለህ ድልን ልታገኝ ትችላለህ። ባትችል ደግሞ በሰላም ትገላገላለህ። ስለዚህ የከፋ ግፍና መከራ ካለ ዳቦ ተገኘ አልተገኘ ትርጉም የለውም። ግፍ እምብዛም የማይመርር ከሆነና ዳቦ አጥቼ የምራብ፣ የምሞት ከሆነ ግን ዳቦውን እመርጣለሁ። .....(ሪፖርተር ግንቦት 25 ቀን 1989)

ይህ መልስ (መልስ ከተባለ) የተሰጠው "ለአንድ አፍታ ወደ ተማሪነትዎ እንመልስዎት። አቶ መለስ ከሚከተሉት ቢመርጡ ሀ)ዳቦ፣ ለ)ዴሞክራሲ" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ነው።

በ1943 እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ሳስተምር አንድ ቀን ክፍል እንደገባሁ የተማሪዎቼን ንቃት ለመፈተን "ምንቸት አብሽ የሚባለው ድንጋይ እንዴት ያለ ነው?" ብዬ ጠይቄ ነበር። ጋዜጠኛው ስለሚጠይቀው ጉዳይ ምንም መሠረታዊ ዕውቀት የሌለው ይሁን ወይም የአቶ መለስን ንቃት ለመፈተን ይሁን ለማወቅ አልቻልም። መልሳቸው ግን ለእኔ አንዳንድ ልጃገረዶች የተፈጩ ድንጋይ ነው ያሉት ዓይነት ነው። ጆን ስቱዋርት ሚል የሚባል የታወቀ የእንግሊዝ ፈላስፋ "የተደሰተ አሳማ ከመሆን ያልተደሰተ ሰው መሆን፣ የተደሰተ ጅል ከመሆን ያልተደሰተ ሶቅራጥስን መሆን ይሻላል" አቶ መለስ የሚቀበሉት አይመስልም።

ለማናቸውም ይህ ሸዋናው ጉዳያችን ያርቀናል። በነገራችን ላይ ዳቦ ከዴሞክራሲ ጋር ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርበው በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ የነጮች አገዛዝ ጊዜ ነበር። ከዚያ ውጭ ያለው ያለማወቅ ውጤት ነው።

በአቶ መለስ አስተሳሰብ ግፍ ሁለት መልክ አለው፤ ግፍና ክፉ ግፍ። ወይም የሚቻልና የማይቻል ግፍ። የሚቻለው ግፍ ከረሃብ ይመረጣል። የማይቻለው ግፍ ግን ረሃብን ያስመርጣል። አስተሳሰቡ ለእኔ አልገባኝም። ምናልባት ዛሬ እሳቸው ካሉበት ደረጃ ሆኖ ሲታይ ግፍ የሚቻል ይመስል ይሆናል። የአሰፋ ማሩ አባትና እናት፣ ወንድሞችና እህቶች፣ ባለቤቱና ጨቅላ ልጆቹ ሌሎችም እንደነሱ በነፍሰ ገዳዮች ዘመድ ያጡ የሚቻል ግፍ ነው የሚሉት አይመስለኝም። እኔ የማውቀው ግፍ አንድ ነው። ይህም ሕግና ሥርዓትን ጥሶ ሰውን ማጥቃት ነው። ሁለት የሚሆነው ትግሉ ነው። ኮሎኔል መንግሥቱ "የታጠቀ፣ የታገለ፣ ያሸንፋል" ይሉን ነበር።

ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሚገባ አድርገን የምናውቀው አንድ እንስሳ አለ። ከከብቶቹም፣ ከበጎቹም የተለየ - አህያ። የአህያ ትዕግስት የማያልቅ ነው። አህያ የኢትዮጵያ ባቡር ነው። ሴንትራ ነው። አያያዛችን ከአገልግሎቱ ጋር የሚዛመድ አይደለም። የዛሬ አርባ ዓመት ግድም ስለአህያ ውርንጭላ የፃፍሁት አንድ ግጥም አለ። ሃሳቡን ብቻ ልግለፀው። አህያ በውርንጭላነቱ በጣም ንቁና ሲቦርቅ ሜዳ የማይበቃው ነው። ሲያድግና እየተጫነ በዱላ ሲነረት የደነዘዘ፣ የፈዘዘ ፍጡር ይሆናል። ልብ ብሎ ላስተዋለ ለውጡ በጣም የሚገርም ነው። አህያ ንዴት የለው፣ ጠብ የለው፣ ምሬት የለው፣ ፍቅር የለው። ድንዝዝ፣ ፍዝዝ ያለ ነው። ማን እንዲህ አደረገው? ግፍ! አህያ በዱላ ሲነርቱት መልሶ አይራገጥ። በአንገሩ ውሻን ተመልከቱ። ፍቅር አለው፤ ንዴት አለው። ሲፀዛበት ደግሞ ተንከባክቦ ያሳደገውን ሰው እንኳን ይናከሳል። ግፍ አይችልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈሪ ነው የሚለው አስተያየት በራሳችንም ሆነ በሌሎች ሰዎች በየጊዜው መሰማት ጀምሮአል። በበኩሌ አልቀበለውም። የዛሬው ትውልድ ፈሪ ነው ለማለት ይቻል ይሆናል፡ ፡ ታሪካችን ፈሪነትን አያመለክትም። ባህላችንም ፈሪነትን አይደግፍም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋ ነው። ጨዋነቱ በባለጌዎች ያስጠቃዋል። የጨዋ የትግል ዘዴ ግንባር ለግንባር አይደለም። የጨዋ የትግል ስልት ከውርደትና ከሃፍረት ነፃ የሆነ ነው።





ለባላንጣው ከሚያስፈልገው በላይ ጊዜ ይሰጣል። በልበ ሙሉነት ያስጨርሰዋል። ፈሪ የሚያስመስለው ይህ ነው። አድፍጠው ለሚጠብቁ የሥልጣን ጥመኞች የሚመቸውም ለዚሁ ነው። ስልቱን መለወጥ አለበት። የጨዋነት ስልት ተሞክሮ፣ ተሞክሮ አላዋጣም። ጨዋነትን ሳይሆን ስልቱን፣ በተለይ ትዕግስቱን "እስቲ እንዋልበት፣ እስቲ እንደርበት" ማለቱን መለወጥ አለበት። የግፍ ቋቱ አንድ ቀን መሙላቱ አይቀርም። ያኔ ብዙ ደም ይፈስሳል።

በትዕግሥትና በፍርሃት መሃከል ያለው መስመር ከፀጉር የቀጠነ ነው። ዘመናዮችና ባለጌዎች ትዕግሥት የማይገባቸውና እንደፍርሃትም የሚመለከቱት ለዚህ ነው። ጨዋ የሆኑም ትዕግሥታቸው ያቺን ቀጭን መስመር ማለፉንና ወደ ፍርሃት መጠጋቱን የማይገነዘቡት ለዚሁ ነው። አንዳንዴ ትዕግሥት ወደ ፍርሃት የሚለወጥበት ደረጃ ላይ ሲደርስ አለማየት ራስን ማታለል ነው። ራስን ማታለል ደግሞ ይለመዳል። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ራስን ማታለል የተራቀቀ ፍልስፍና ሆኖአል። ምሁር የሚባለው ሁሉ ራሱን እያታለለ ከካርታ ጨዋታና ከመጠጣት የተሻለ ተግባር አላገኘም። የኢንዱስትሪ ባለቤቱና ታላላቅ ነጋዴው ሕይወት ማለት ለመጣው እየገበሩ፣ እያማረጡ እንደልብ መብላትና መጠጣት ብቻ ሆኖበታል። ትልቁ ችግሩ ይበልጥ መብላትና መጠጣት አለመቻሉ ነው። ደሀው ከእንቅልፉ ከነቃበት ጊዜ ጀምሮ "ዛሬ ምን እበላለሁ? ልጆቼን ምን አበላቸዋለሁ?" በሚል የማይበርድ የዕለት ተዕለት የተፈጥሮ ግዴታ ተቀስፎ ሲንከራተት ይውላል። ሰቀቀኑ አንዳንዴ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። አንዲት ወጣት ሴት አንድ ቀን ችግርዋን አጫወተችኝ። ባልዋ ታስሮባታል። ሥራ የላትም። ጌጦችዋን ሁሉ እየሸጠች ባልዋንና ልጆችዋን ትመግባለች። "አሁን" አለችኝ ይቺ ወጣት ሴት "እየቸገረኝ በመምጣቱ ዳቦ እገዛና ለባለቤቴ ልውሰድለት? ወይስ ለልጆቼ ላብላቸው?" እያልሁ የምጨነቅበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። ይህ ደግሞ ሌላ ችግር ነው። ያለው ለሁሉም ስለማይበቃ ማን በልቶ ማን ጦሙን ይደር? ከዚህ የበለጠ ምን የሚያስከፋ ጭንቀት አለ? የአገዛዝ ሥርዓት ሁሉ ጭንቀትን መፍጠር ባሕርዩ ነው።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጭሰኛ የነበረውን ገበሬ ሁሉ ባለርስት ለማድረግ የተካሄደውን ትግል ደርግ በተወላገደ አስተሳሰብ ቀልብሶ ባለርስቱንም ጭምር ጭሰኛ አደረገው። የተፈለገው ጭሰኛውን ከባለርስቱ ጋር ማስተካከል ሆኖ ሳለ ባለርስቱን

ከጭሰኛው ጋር አስተካከለው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ገበሬ በሙሉ የደርግ ጭሰኛ ሆነ። አሁንም ገበሬው በጭሰኝነት ተሰንን እንደተያዘ ነው። እንግዲህ ምሁሩም፣ ባለኢንዱስትሪውም፣ ትላልቅ ነጋዴውም፣ ደሀውም፣ የባልዋና የልጆችዋ ረሃብ ስቀቀን የሆነባት ሴትም፣ገበሬውም ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ግፍን በትዕግስት አጎናፅፎ የሚያቀማጥል ነው ሲባል ነው? ወይስ ችግራቸው ረሃብ የሆነውና ችግራቸው ቁንጣን የሆነው በፍርሃት ተስማምተው ነው? ቁንጣን ነው የፍርሃት ማሀደር። ችጋር የሰውን ልጅ ከፍርሃት ውጭ ነው የሚያደርገው።

የአንድ ኅብረተሰብ አባሎች መተሳሰብ አለባቸው ሲባል በችጋር የሚቆራመዱት በቁንጣን ለሚታመሙት፣ ባልዋንና ልጆችዋን የመቀለብ ኃላፊነት በራስዋ ላይ ጭና የምትጨነቀው በቁማር በሽታ አይደለም። ውሃ ቀልቀል እንደሚፈስ ሁሉ የኅብረተሰብ ኃላፊነትም ተቀበልነው አልተቀበልነው ከላይ ወደታች ነው። የሞላው ለጎደለው የአለው ለሌለው ነው ኃላፊነቱ። የአለው ሲባል ገንዘብ ብቻ አይደለም። እውቀትም፣ ጉልበትም፣ ጊዜም ያለው ይሆናል፡

የኅብረተሰብ ኃላፊነት የመንፈስ ግዴታ ነው ማለት በአፍአዊ ወይም ከእኛ ውጭ በሚመጣ ተፅእኖ የሚጫንብን ሳይሆን እያንዳንዳችን በውስጣችን ከአለው የመንፈስ ኃይል የሚመነጭ ነው፡ ፡ ይህ የመንፈስ ኃይል ከሌለን ቀደም ሲል እንደገለፅሁት እንስሳነታችን አይሉኣል ማለት ነው። በእንጉርጉሮ እንዳልሁት -

ሌሎች ሲበሳጩ፣ ሌሎች ሲሸበሩ፣
ብዙ ነገር ጎድሎ
ሞልቶለት ደስ ያለው፣
ከዙሪያው መበስበስ፣ ከዙሪያው መሸነት፣
እሱ ተገንጥሎ
የማይቆረቁረው፣
የሰው አውሬ እሱ ነው።

የሰው ልጅ እንደማናቸውም እንስሳ ከሞት አያመልጥም። ከፍፁም ሞት የሚያመልጠው ለሚቀጥለው ትውልድ፣ ለልጆቹ በሚያስተላልፈው ሥራው ነው። ይህንን ለማድረግ ብቃት የሚኖረው ትናንት እንደነበረና ከትናንትም የተረከበውን አሻሽሎና





አበልጽጎ በማስተላለፍ ነገ ከዛሬ የተሻለ እንዲሆን የሚያስፈልገውን መስዋዕት ለመክፈል የተዘጋጀ ሲሆን ነው።

ብንራብም፣ ብንጠግብም በዚች አብረን በቆምንባት መሬት ላይ ነው። ኑሮአችን የተመሠረተው በዚች መሬት ላይ ነው። እትብታችን የተቀበረውና አፈር የሆነው በዚች መሬት ውስጥ ነው። እኛም በጊዜያችን የምንቀበርባትና አፈር የምንሆነው በዚችው መሬት ውስጥ ነው። አንድነታችን በልደትም፣ በኑሮም፣ በሞትም ነው።

በሕይወትም ሆነ በኑሮአችንም፣ በሞታችንም የኔ ብላ የምታቀራኘን ይቺ መሬት ነች። ከአፈርዋ ጋር ተዋሀደው በመንፈስ ከእኛ ጋር ያሉትንም እናቶቻችንንና አባቶቻችንን ይቺ መሬት ከእኛ ጋር በግዙፍ ታያይዛቸዋለች። እኛ ይህቺ መሬት ነን። ይቺ መሬት እኛን ነች። እኛ ከስዋ ጋር አንድ ነን። እኛም ከእኛ ጋር አንድ ነን።

ከዚህ በላይ በአጥር ውስጥ የሚታየው ጽሑፍ በ1989 በጦብያ መጽሔት ላይ የወጣ ነው፤ ልለውጠው ስላልፈለግሁ አንዳንድ በዘመኑ የነበሩ ጉዳዮች ከመነሣታቸው በቀር ‹ትናንት የለም፤ ነገ የለም፤ ዛሬ ብቻ፤› የሚለው ሀሳብ በዋናነት ይወጣል፤ ይህ ጽሑፍ የመክሸፍን ምንጭ በትክክል ይገልጻል፤ በተለይ በዚህ ክፍል የመክሸፍ ምንጭ ምን እንደሆነ ያሰብሁትን በከፊልም ቢሆን ያስረዳል፤ ትናንትን መርሳት ማለት ወላጆቻችንና ወላጆቻቸው የሄዱበትንና እኛም በከፊል የሄድንበትን መንገድ ሳናውቅ መጓዝ ድካም ብቻ ይሆናል፤ የወላጆቻችን ወላጆች ምን ችግር አጋጥሟቸው ነበር? ወላጆቻቸውስ ምን ችግር አጋጥሟቸው ነበር? ችግሮቻቸውን እንዴት ፈቱ? ችግሮቹ የተለያዩ ነበሩ ወይስ ተመሳሳይ? መፍትሔዎቹስ የተለያዩ ነበሩ ወይስ ተመሳሳይ? ለምሳሌ እኔ በደንብ የማውቀውን ልናገር፤ በትግራይ በ1951 ዓ.ም. ክፉ ችጋር ነበር፤ በየመንገዱ ላይ ሰው ይሞት ነበር፤ በ1965 እንደገና በትግራይና በወሎም ክፉ ችጋር ነበር፤ ከአሥራ አራት ዓመታት በፊት የተከሰተና የብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት የቀጠፈ ችጋር እንዴት ተጠናክሮና ተስፋፍቶ እንደገና ሊመጣ ቻለ? በእውነቱ ያንን ከማይጨው እስከመቀሌና እስከአዲገራት፣ ከዚያም እስከአድዋና እንዳ ሥላሴ በየመንገዱ ላይ የነበረውን የጻዕር ዋይታ ያየ፣ ያንን እንደገና አንኳን በኢትዮጵያና በየትም ቢሆን ለማየት አይፈልግም፤ እኔ አልፈልግም፤ በዚህም ምክንያት በ1965 ወደወሎ ከሄደው ቡድን ጋር አልሄድሁም።

የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ችጋርን በተደጋጋሚ እያዩ ዘለቄታ ያለው መፍትሔ አለመፈለጋቸው የችሎታቸውን ማነስ ብቻ ሳይሆን ለሕዝቡ ያላቸውን ግምት የሚያመለክት ነው፤ ኃላፊነቱን በባለሥልጣኖቹ ላይ ብቻ መለጠፍ የሚቻል አይመስለኝም፤ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በነዚህ ስፍራዎች ከገበሬዎች ጋር ስነጋገር አንዳንዶቹ እነዚህን የችጋር ጊዜዎች የማያስታውሱ መሆናቸው በጣም አስደነቀኝ፤ እንግዲህ እነሱም ባይሆኑ የቅርብ ዘመዶቻቸው የተጎዱባቸው ሰዎች ካላስታወሱ ማን ያስታውሳል? በአገዛዝ ደረጃ እንደሆነ ሰዎችም በችጋር በሚሞቱበት ጊዜ ችጋር መኖሩን ይክዱ ነበር፤ ራስ ሥዩምና ሌሎች የትግራይ ባለሥልጣኖች እግዚአብሔር ያመጣው ቁጣ ነው በማለት ሕዝቡ በየቤተክርስቲያኑ እየተሰበሰበ ምህላ እንዲያደርስ በደብዳቤ ትእዛዝ አስተላልፈው ነበር፤ ዛሬ የችጋር ስጋት ሲመጣ ባለሥልጣኖቹ በመጀመሪያ የሚያስታውቁት ለአሜሪካና ለአውሮፓ መንግሥታት ነው፤ ስለዚህ መፍትሔዎቹ ከጸሎት ወደቀጥታ ልመና ተሸጋግረዋል (እግዚአብሔርን ከመለመን የምዕራባውያን መንግሥታትን ወደመለመን፤ ምዕራባውያን መንግሥታት እግዚአብሔርን ተክተዋል ማለት ነው)፤ በዚህም ምክንያት በአለፉት ሃያ ያህል ዓመታት ያለእህል እርዳታ ያለፈ ዓመት የለም፤ በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎችን በገፍ የሚገድል ችጋር አልተከሰተም፤ ነገር ግን ምጽዋቱ ቢቋረጥ ችጋር እንደሚመለስ በበኩሌ አልጠራጠርም።

ትናንትን አለማስታወስም ሆነ ለነገ አለማሰብ በተደጋጋሚ በደረሰው ችጋር ጉዳይ በጉልህ የሚታይ ነው፤ ልመናን እንደመፍትሔ የመጠቀሙ አጉል ዘዴ አንድ ቀን የባሰ ?ጋን እንደሚያስከትል ታይቷል፤ ኃላፊነትንና በራስ መተማመንን የማያዳብር የችግር መፍትሔ አያስተምርም፤ አያሳድግም፤ አንድ ችግር፤ ምንም ዓይነት ችግር ቢሆን በአንድ አገር ላይ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊደርስ አይገባም፤ ያው ችግር ከዓመት ዓመት እየተመላለሰ ሕዝብን የሚያጠቃ ከሆነ እንዴት መፍትሔ መፈለግ ያቅታል? በምን ምክንያት ነው ሕዝቡ መፍትሔ የማያገኝለት? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የማይችል ሕዝብ አያድግም፤ ከችግርም አይወጣም፤ ሕዝቡ ችግሩን ከራሱ አውርዶ በማንም ላይ ሊወረውር አይችልም።





## ትናንትን አለማስታወስ

ትናንትን እንደአንድ ቀን ሳይሆን እንደብዙ ዘመን ካየነው ብዙ ትውልዶች የወጡበት ወይም የወረዱበት ነው፤ወይም ወጥተው የወረዱበት፤ ወይም ወርደው የወጡበት፤ ያላቸውንና የሌላቸውንም የተቀባበሉበትና ያለፉበት መንገድ ነው፤ ስለዚህም ትናንትን ማስታወስ በሁለት በኩል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ በአንድ በኩል ትናንት የተገኘውን እውቀትና ጥበብ በተግባር ላይ በማዋል አዳብሮ ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ትናንት የተሠራውን ስሕተት ዛሬ እንዳይደገምና ለሚቀጥለውም ትውልድ እንዳይተላለፍ የስሕተት በሩን ለመዝጋት ይረዳል።

ትናንትን በችግር አልፎ ዛሬም ያው ችግር የሚገጥመው ግለሰብ ወይም ማኅበረሰብ ግለሰቡ ወይም ማኅበረሰቡ ራሳቸው ችግር የሰባቸውም ወይ ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን፤ ጥያቄውም ለኋላ-ቀርነት ሁሉ መሠረት የሆነውንና የሚሆነውን ሕመም ማመልከቱን እንጠቁማለን፤ ነገር ግን ርእሱ ልዩ ጥናትና ልዩ ዝግጅት ስለሚያስፈልገው ጥያቄውን መዝግበን በጠቅላላ ዳሰሳ እናልፈዋለን።

ትናንት ማኅበረሰቡ በምግብ አቅርቦት፤ በጤንነት፤ በእውቀት፤ በማኅበራዊ ኑሮ የነበረውን ጥንካሬ ለዛሬው ማኅበረሰብ እንዴት አድርጎ አስተላለፈ? እንዲሁም የትናንቱን ድካም ተሸክሞ የመጣው ለዛሬው ትውልድ እንዴት አስተላለፈ? ከትናንቱ ማኅበረሰብ የተላለፈው ጥንካሬ ለዛሬውም ኑሮ ምን ችግር ወይም እንቅፋት ፈጥሮ ይገኛል? ወይስ ምን ያህል አሻሽሎታል? የእነዚህ ጥቂዎች መልሶች ሁነቶችን ብቻ ሳይሆን ምክንያቶቻቸውን ጭምር በተጨባጭ ማስረጃዎች መደገፍ ያስፈልጋል፤ የብዙዎቹ እንቅፋቶችና ችግሮች ፈጣሪ አዳፍኔ እንደሆነ አይጠረጠርም፤ ግን አዳፍኔን የሚያግዙና በመሣሪያነት የሚያገለግሉት ሠራዊት አሉት፤ እነዚህም ሰዎች መሽጦ የሆኑበትን ምክንያት ፈልፍሎ ማውጣት ያስፈልጋል።

መሽጦነት ከማጭበርበር ንግግር አልፎ ዛሬ ብዙ መጻሕፍት የተጻፉበትና በጋዜጣም በቴሌቪዥንም የሚወደስ ጉዳይ እየሆነ ነው፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴም፤ በደርግም፤ ዛሬ በወያኔም ያለውን የመለዮ ለባሽና የደኅንነት ሠራዊት «ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የወጣ ነው፤» የሚባል ማደናገሪያ እያለበሱ ከመሽጦነት አውጥተው የክብር ቦታ ለመስጠት የሚሞክሩ ሞልተዋል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በማናቸውም አዳፍኔ ስር የሚመሠረት የመለዮ ለባሽና የደኅንነት ሠራዊት የአዳፍኔን ክብርና

ልዕልና የሚጠብቅ ነው፤ የአዳፍኔን ክብርና ልዕልና የሚጠብቅለትም የኢትዮጵያን ሕዝብ መብቶች እየጨፈለቀ፣ ሀብቱንና ንብረቱን እየመዘበረ ነው፤ ይህንን የሚክድ ኢትዮጵያን አያውቅም፤ የውጭ ጠላት ሲመጣ የአዳፍኔ ሠራዊት በየዳር-ድንበሩ ተጋድሷል፤ የአዳፍኔዎች ፋክክር ባለበት ጊዜ ደግሞ የእንግሊዝ ጦር አንድ ጊዜ፣ የኢጣልያ ጦር ሁለት ጊዜ ድንበር አየጣሱ ወደውስጥ ዘልቀዋል፤ ሁለቱን ጊዜ የኢትዮጵያ አዳፍኔዎች በውጭ ኃይሎች ተሸንፈዋል።

ማስረጃ ለማቅረብ በማይቻልበት ጉዳይ ላይ ጥያቄ ማቅረብ አይከለከልም፤ ስለዚህም የኢትዮጵያ ጦር ቢኖር የእንግሊዝ ጦር ሰተት ብሎ መቅደላ ይደርስ ነበር? የኢትዮጵያ ጦር ቢኖር በ1928 ዓ.ም. የኢጣልያ ጦር ትግራይን አቋርጦ አምባ አላጌ ላይ መሽጎ ምኒልክን ይጠብቅ ነበር?

የኢትዮጵያ ባህላዊ አገዛዝ እስከአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ቀጥሎ ነበር ለማለት ይቻላል፤ በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በጎጃም ንጉሥ ተክለሃይማኖት፣በወሎ ንጉሥ ሚካኤል፣በትግራይ ራስ ሥዩም፣ በወላይታ ጦና፣ በወለጋ ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር፣ በኦጋዴንም፣ በአፋርም ባለሙሉ ሥልጣን ገዢዎች ነበሩ፤ ምኒልክ በንጉሠ ነገሥትነት ከሁሉም በላይ ቢሆንም የየስፍራው ባህላዊ ገዢዎች ባለሙሉ ሥልጣን ሆነው የራሳቸው ሁለ-ገብ ኃይል ነበራቸው፤ ይህንን ለማረጋገጥ ለፈለገ ጳውሎስ ኞኞ ያሳተመውን የምኒልክ ደብዳቤዎች ማንበብ ይበቃል።[23]

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የኢትዮጵያ ባህላዊ አገዛዝ በኢጣልያ ወረራ ተሰበረ፤ ከኢጣልያ ወረራ በኋላ የቀጠለው የንጉሠ ነገሥቱ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ከባህላዊው አገዛዝ ወጥቶ ነበር፤ እንዲያውም ግራ የገባው አገዛዝ ነበር ለማለት የሚቻል ይመስለኛል፤በአንድ በኩል የአድዋ ድልን በልበ-ሙሉነት የሚያንጸባርቁ የኢትዮጵያዊነት የክብርና የኩራት ስሜት፣ በሌላ በኩል በማይጨው ተሸናፊነትና ውርደት የሚያሸማቅቅ ስሜት፣ በአንድ በኩል የኢጣልያ ወረራ ያጎደፈውን የኢትዮጵያን ክብርና ታሪክ መንኮታኮት የሚያመለክቱ ማስረጃዎች በሥልጣን መንበሮች ላይ ተጎልተው በኢትዮጵያ ላይ የሚሳለቁበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች አንገታቸውን ቀና ደረታቸውን ነፋ አድርገው ክብርና ኩራት እንዳልጎደፈ የሚያሳዩ

[23] በዚህ ጉዳይ ላይ በተረጋገጠ እውቀትና በሙሉ እምነት ሲናገር የሰማሁት ዶር. ፍቅሬ ቶሎሳን ብቻ ነው፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ በራሱ ያደረገው ጥናትና የደረሰበት መደመደሚያ በጣም የሚያስደንቅ ነው።





አርበኞች ነበሩ፤ በዚህ ምስቅልቅል ሁኔታ ውስጥ ዘመናዊው ታሪካዊ መክሸፍ የጀመረ ይመስለኛል፤ የኢጣልያ ዘመናዊ አገዛዝ በባህላዊው አገዛዝ ላይ ተለጥፎ የነበረበት ጊዜ ነበር።

ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ በአንድ በዘመናዊ አስተዳደርና ወታደራዊ ማእከላዊ ሥልጣን ስር ገባች፤አጼ ኃይለ ሥላሴ በስራቸው አንድም ንጉሥ አልነበረም፤ራስና ደጃዝማቾቹም በስራቸው ምንም ጦር ያልነበራቸውና እነሱም ራሳቸው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ሙሉ ቁጥጥር ስር ነበሩ፤የምኒልክ ንጉሦች፣ራሶችና ደጃዝማቾች የሚመስሉ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አልነበሩም፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻቸውን የሥልጣን ሁሉ ባለቤት ነበሩ፤ የጦር ኃይሎቹ (የምድር ጦር፣የዓየር ኃይል፣የባሕር ኃይል፣) ብሔራዊ ጦር፣ ፈጥኖ ደራሽ፣ ክብር ዘበኛ፣ ፖሊስ … ጸጥታ … ሁሉም በአጼ ኃይለ ሥላሴ ስር ነበሩ፤ የሁሉንም አዛዦች የሚሾሙና የሚሽሩ እሳቸው ነበሩ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን በአንድ ሰው እጅ እንደተቋጠረ ለመረዳት አምባሳደር ዘውዴ ረታ የጻፈውን ‹‹የኤርትራጉዳይ›› እስከመጨረሻው ማንበብ በቂ ማስረጃ ያስጨብጣል፤ በኤርትራም የተጀመረውን ችግር ማን እንደፈጠረው በግልጽ ለመገንዘብ ይቻላል፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድም ሆኑ መሳፍንቱና መኳንንቱ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስና ተከትሎም ለመጣው ሹም-ሽር ምንም ኃላፊነት የለባቸውም፤ ኃላፊነቱ በሙሉ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ነበር።

ነገር ግን አጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻቸውን አልነበሩም፤ ብዙ ጉልበት የሆኑላቸው ሰዎችና ድርጅቶች ነበሩ፤ በስራቸው ሆነው በአደባባይ የሚያጨበጭቡና ለብቻቸው ሲሆኑ ‹‹ምን እናድርግ!›› የሚሉ ኃላፊነትን ከመካፈል አይድኑም፤ ሕጋዊ ኃላፊነት ባይኖርባቸውም ከመንፈሳዊ ኃላፊነት አያመልጡም፤ በኤርትራ የፖሊስ አዛዥ የነበረው ጀኔራል ተድላ ዕቁባይ ብቻ መንፈሳዊ ኃላፊነቱን ተገንዝቦ ራሱን ገደለ፤ ሌሎች በየታዘዙበት ተሰማሩ፤ የአገዛዝ ሥርዓቱን ለመለወጥ ከሚያስፈልጉት ዋና ተግባሮች አንዱ ለእንጀራ ተብሎ አገልጋይ ቢኮንም ሕገ-ወጥ ግዑዝ መሣሪያ ላለመሆን እምቢ ማለት ነው፤ እምቢ ማለት እስርን፣ ግድያን፣ ግዞትን ያስከትላል፤ ይህንን ለመቀበል ያልፈለገ የጀኔራል ተድላ ምርጫ አለው፤ስለዚህ እኛ ምን እናድርግ! እያሉ አምባ-ገነኖችን ማገልገል እንደጥፋት አይቆጠርም ማለት ራስን ከማታለል አያልፍም፤ የሃይማኖት ሰዎችም እንዲሁ ለተቀባው፣ ለተመረጠው ተገዙ እያሉ መስበካቸው በእኔ አስተያየት ከመንፈሳዊ ኃላፊነት አያድናቸውም።

በአለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ከደርግ ሠራዊት ውስጥ ከአሥር አለቃ እስከጀኔራል ታሪክ ጸሐፊዎች ሆነዋል፤ የሁሉም ተረት ‹‹እኛ ምን እናድርግ!›› በሚል የሚቋጭ ነው፤ አንድ የበላይ መኮንን ለሃምሳ አለቃ ሰላምታ ሲሰጥና በሃምሳ አለቃ ሲታዘዝ የተማረውን ሁሉና የውትድርና ሥርዓትን በፍርሃት ቀብሮና ራሱን አዋርዶ እንደሆነ ልቡናው ያውቀዋል፤[24] አንድ ቀን ማታ በቴሌቪዥን ላይ በዓየር ኃይል ውስጥ አንድ የበታች መኮንን በመድረኩ ላይ ወጥቶ ንግግር ሲያደርግ እንደፋንታ በላይ ያሉ ከፍተኛ መኮንኖች በእጆቻቸው አገጫቸውን እየደገፉ ቁጭ ብለው ይመለከቱ ነበር፤ ማዳመጣቸውን እግዚአብሔር ይወቀው! በበነጋታው ጥቂት መኮንኖች በነበሩበት ግብዣ ላይ በቴሌቪዥን ያየሁትን አሳፋሪ ትእይንት አንሥቼ ቁስላቸውን አሸቄባቸው ነበር፤ ባይናገሩትም በመንግሥቱ ኃይለማርያም እንደሚያሳብቡ ተሰማኝ፤ እሱ በበኩሉ ጣቱን ወደሌሎች እየጠቆመ እሱ ዝንብም የማይገድል መሆኑን ይናገር ነበር።

የደርግ ሠራዊት አደባል የሚሉ ሰዎች ‹‹የኢትዮጵያ›› የሚባል ሠራዊት በአጼ ኃይለ ሥላሴም ሆነ በደርግ ዘመን፣ አሁንም እንደነበረና እንዳለ ማስረዳት አለባቸው፤ ከላይ እንደተጠቀሰው ባህላዊው ውትድርናም በአንድ ማእከል ስር አልነበረም፤ ንጉሥ፣ ራስ፣ ግንጥራር፣ ደጃዝማች፣ ... የየራሳቸው ወታደሮች ነበሯቸው፤ በዚህም ምክንያት ወታደሩ አንዱ ገገር ካልተስማማው ለሌላው የማደር አማራጭ ነበረው፤ የውጭ ጠላት ካልመጣ በቀር እነዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የተለያዩ ሠራዊቶች አይገናኙም ነበር፤ በአገር ውስጥ የሚገናኙት በእርስበርስ ውጊያ ላይ ነበር፤ በኢትዮጵያ ያለው ጦር ሁሉ በአንድ ላይ የተጠቃለለው በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፣ ከኢጣልያ ወረራ በኋላ ነበር።

በዚህ ጊዜም በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የጦር ኃይል የኢትዮጵያ ነበረ ለማለት አያስደፍርም፤ ብዙ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ሲያወሩ ‹‹ከሕዝብ አብራክ የወጣ ነው፤›› የሚሉት ነገር አለ፤ ወሬ ለማሳመር ካልሆነ በቀር ምንም ትርጉም የለውም፤ ማን ከሕዝብ አብራክ ያልወጣ ገዳይ፣ ደብዳቢና አሰቃይ፣ አሳሪና ገራፊ አለ፤ ራሳቸው አምባገነኖቹም ከሕዝብ አብራክ የወጡ ናቸው፤ ጥያቄው ከሕዝብ አብራክ ወጥተው የሕዝብ ወገን አለመሆናቸው ነው፤ እኔ የምለው የሕዝብ ወገን አይደሉም ነው፤ የአገዛዙ መሣሪያ ሆነው ሕዝቡን የሚያስጠቁና

[24] በዚህ ጉዳይ ላይ ካሣ ከበደ ሲናገር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በትከሻው ላይ ልዩ ምልክት ነበረው ይላል፤ ግን ሌሎቹ የደርግ አባሎችስ ብሎ የጠየቀው አልነበረም።





የሚያስጨቁኑ፣ የሚያስበዘብዙና የሚያደኸዩ ናቸው፤ ይህ እውነት አይደለም ብሎ የሚከራከር ሰው አስተሳሰቡን አቃንቶ መቅረብ አለበት፤ ፖሊሱም፣ ዓቃቤ ሕጉም፣ ዳኛውም፣ አስተዳዳሪውም ሆነ ሌሎች የአገዛዝ ሥርዓት መሣሪያዎች ራሳቸውን ከጎሲና ወቀሳ ለማዳን የሚያደርጉት ጥረት የአእምሮንና የኅሊና መክሸፍን በመሸፋፈን መክሸፍን እንደጥሩ ነገር ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚያስተላልፍ ነው።

ይህ አስተሳሰብ መክሸፍን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተከለ ነው አርበኞች የተመሰገኑና የተወደሱ እንደሆነ ባንዳዎችና ስደተኞች ስለሚኮማተሩ የአርበኞችን ተጋድሎና መስዋእት ሁሉ ማዳፈን አስፈለገ፤ ከዚህ በፊት የጻፍሁት የደጃዝማች የማነ ሀሰን ጉዳይ አለ፤ ብዙ ጊዜ በግብዣ ላይ ሳገኛቸው ስለአርበኝነት ዘመን ታሪክ ተራራውን፣ ሸንተረሩን፣ ወንዙን እያነሱ በዝርዝር ሲናገሩ በአድናቆት አዳምጣቸው ነበር፤ በዚህም ምክንያት ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ ጋበዝኳቸው፤ በጣም ደነገጡ፤ተቆጡ፤ ‹‹ወዳጄ መስለኸኝ ነበር!›› አሉኝ፤ አርበኞች ታሪካቸውን ሲናገሩ ጊዜ የሰጠው ባንዳና ስደተኛ ሁሉ ይኮማተራል፤ይህ ከሚሆን የአርበኞች ታሪክ ይዳፈን! አዳፍኔ የማይፈልገው እውነት ይዳፈናል፤ አዳፍኔ የሚፈልገው ሐሰት እየለባበሰና እየተቀባ ለሕዝብ ይቀርባል።

ዞሮ ዞሮ ከሕዝብ አብራክ የወጡ ናቸው የሚለው ክርክር ኃላፊነትን ላለመቀበል የሚደረግ አጉል ሸሸት ነው፤ የትም አያደርስም፤ ፖሊሱም፣ ወታደሩም፣ አስተዳዳሪውም በሥራቸው ላይ ባሉበት ጊዜ ከሕዝብ አብራክ የወጡ መሆናቸውን ተረድተው ሕዝቡን ለማጥቃትና ለመጨቆን በሚደረገው ሁሉ መሣሪያ ባይሆኑ ለሕዝብና ለሀገር ያለባቸውን ኃላፊነት የተወጡ ናቸው ለማለት ይቻል ነበር፤ ጥቂትም ቢሆኑ ይህንን ኃላፊነት ከነውጤቱ የተቀበሉ ሰዎች አሉ፤ የእነዚህ ሰዎች ታሪክ እንደአርበኞች ታሪክ ሌላውን የሚያኮማትር ሆኖ ይታያልና አይነገርም፤ እኔ በአጋጣሚ የማውቃቸውንና ከሌሎች የሰማሁትን ለናሙና ያህል ላቅርብ።

1. እሬ ንጉሥ ገብረ መድኅን ኃይለ ማርያም[25] --- እኚህን ሰው በልዑል ራስ እምሩ ቤት ተዋውቄአቸዋለሁ፤ ለብዙ ዓመታት እግሮቻቸውን ታስረው ከአዲስ አበባ ውጭ ኖረዋል፤ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ነበሩ፤ እንደሰማሁት በአንድ ጉዳይ ላይ ዳንሆይ መሆን

[25] ተድላ ዘዮሐንስ ገ. 514

ነገን አለማሰብ

የነገ ኑሮ ከትናንትም ከዛሬም የተሻለ እንዲሆን ሁኔታዎችን የምናመቻቸው እኛ ነን፤ የዛሬው ትውልድ ምንም ነገር ሳያደርግ ቢቀር ዛሬ እንደትናንቱ ይሆናል፤ ወይም ነገ እንደዛሬ ይሆናል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው፤ ምንም ነገር አለማድረግ ምንም ነገር አይሆንም ማለት አይደለም፤ የሰው ልጅ ማድረግ የሚገባውን ሳያደርግ ቢቀርም ተፈጥሮ ማድረግ የሚገባውን ማድረጉን ይቀጥላል፤ ስለዚህም የሚሸግተው ይሸግታል፤ የሚበሰብሰው ይበሰብሳል፤ የሚሞተው ይሞታል፤ የሰው ልጅ ማሰብ ስላቆመ ተፈጥሮ ሥራውን አያቆምም።

ስለነገ ማሰብ ጠቃሚ የሚሆነው ዛሬ ነው፤ ነገ ሲደርስ ሙሽራ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ይሆናል፤ ከዚያም በላይ ነገ የሚታሰበው ከትናንትናና ከዛሬ ጋር ነው፤ የትናንትናና የዛሬ ችግሮች ወደነገ እንዳይተላለፉ፤ የትናንትና የዛሬ እውቀትና ጥበብ በተጠናከረ መልኩ ለነገ እንዲተላለፍ ማድረግ የአስተዋይ ማኅበረሰብ ጉዞ ይሆናል፤ ነገን ሳያስቡ መጓዝ በጨለማ እንደመሄድ ነው፤ መንገዱንም ሆነ መድረሻውን አለማወቅ ነው፤ በትናንትናው የስሕተት ጎዳና ላይ መጓዝ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ወደባሰ ስሕተት የሚወስድ መንገድ ሊሆን ይችላል።

ገና የነገ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የትናንቱንና የዛሬውን ስሕተትና ጉድለት በትክክል ተረድቶ ያንን ለማስተካከል የሚያስፈልገውን እውቀትና መሣሪያ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፤ ጣራው የሚያፈስ ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው ጣራውን ለመሥራት ክረምት እስቲገባ አይጠብቅም፤ ትናንትናና ዛሬ ምግቡን ለመሥራት ውሀና እሳት ለማግኘት የተቸገረ ሰው ከዚህ ችግር ለመገላገል ነገ ደግሞ እስቲቸገር መጠበቅ አያስፈልገውም፤ ዋናው ትምህርት የትናንቱ ችግር ነገም እንዳያጠቃ ከተፈለገ ዛሬ አስቀድሞ ማሰብና አስፈላጊውን መፍትሔ ይዞ መገኘት ነው የሚል ይሆናል፤ ዛሬ የትናንቱን ችግር ካላስታወሱ ነገ መፍትሔውን ለመፈለግ ጊዜ አይኖርም ይሆናል፤ ለችግሩ ካልተጨነቁ ለመፍትሔው መጨነቅ አይኖርም፤ ለመፍትሔው ካልተጨነቁ ከችግሩ ጋር መቀጠል ግዴታ ሊሆን ነው።





# ምዕራፍ ፫
# የታሪክ ጉዞ

*መንገዱን የማያውቅ በጉዞ ላይ ያለ ሰውን ብልህ የሚያሰኘው በያዘው የተሳሳተ መንገድ በከፍተኛ ጥድፊያ መገስገሱ አይደለም፤ ቆም ብሎ ትክክለኛውን መንገድ መፈለጉ ነው።*
R.H. Tawney

ነጻነት፣ እውነት፣ እውቀት፣ እድገት

እውቀት የእውነትና የነጻነት ፍሬ ነው፤ እድገት የእውቀት ፍሬ ነው፤ እንግዲህ በግልብጡ ስናየው እውነትና ነጻነት በሌለበት እውቀት ሊያብብ አይችልም፤ እውቀት ከሌለ እድገት አይኖርም፤ ዛሬ ከትናንት አይለይም፤ ነገ ከዛሬ የተለየ ይሆናል ብሎ ተስፋ ማድረግ አይቻልም፤ አንዱ ትውልድ የወረሰውን ምንም ሳይጨምርበትና ምንም ሳያሻሽለው እንደተረከበው ለሚቀጥለው ትውልድ የሚያስተላልፍ ከሆነ ትውልዶቹ የቁልቁለት መንገድ የያዙ ናቸው፤ ቁልቁል የሚያወርደው መስላል መክሸፍን የሚያሳይ ታሪክ ነው።

በተለያዩ ጸሐፊዎች የሚተረከው የኢትዮጵያ ታሪክ ጉድለት አለበት፤ አንደኛ ብዙ ሁነቶችን ይገድፋሉ፤ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚጀምሩት ከመሀሉ ወይም ከአሁኑ ነው፤ በዚህም ምክንያት አዲስ ታሪክ ለመድረስ ምቹ እየሆነ ነው፤ ኤርትራ የኢትዮጵያ መሠረት መሆንዋን ማስካድ ለጊዜውም ቢሆን ተችሏል፤ **ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል** እንደሚባለው በጠመንጃ ታጅበው አዲስ አበባ የገቡት የሁለተኛ ደረጃ ምሩቆች፣ የወያኔ ሊቃውንት እነመለስ ዜናዊ፣ በረከት ስምዖን፣ ዓባይ ጸሐይ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ከነሱ የባሱትን ጀሌዎቻቸውንም

ሁሉ ለማሳመን አልቻሉም፤ ግን ሲአይኤን አሳምነዋል፤ በአማርኛ ድንጋይ ራስ የምንለውን ኢጣልያኖች ቴስታ ዲ ጋሊና (የዶሮ ጭንቅላት) ይሉታል፤ እንዲህ ካልሆነ ወንድሞቻቸውን ባዕድና ጠላት ለማድረግ አገራችን የሚሏትን ኢትዮጵያን ለመገዳት እንዴት ቻሉ? የኤርትራን ሕዝብ ባዕድና ጠላት አድርገውስ ለትግራይ ምን ዘለቄታ ያለው ጥቅም ያስገኛል ብለው ገመቱ?

## ታሪክ ምንድን ነው?[26]

ታሪክ ለአንድ ሰከንድም የማያቋርጥ የኑሮና የአኗኗር ጅረት ነው፤ ያለፈውን ትውልድና የዛሬውን እያለፈ ያለውን ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚያደርስና የቆየውና አዲሱ የሚረካከቡት ትዝብት ነው፤ መሞትና መወለድ እስካሉ ድረስ የትውልዶች መረካከብ ስለማያቋርጥ ታሪክም አያቋርጥም፤ ሰዎች በጥፋት ውሀም ሲያልቁ የተረፉ ስለነበሩ ታሪካቸው ወደእኛ ደርሶአል፤ አልተቋረጠም፤ ይህ በአጠቃላይ ሲታይ ነው፤ ነገር ግን በተጨባጭ እውነት፣ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ዘመኖች የሆነውን ስንመለከት የምናየው ያልተቋረጠ የእድገት ጉዞ አይደለም፤ በአውሮፓ ውስጥ የግሪክ ታሪክ አልከሸፈም? የሮም ታሪክ አልከሸፈም? በመሀከለኛው ምሥራቅ የግብጽ፣ የፋርስ፣ የሶርያ ... ታሪኮች አልከሸፉም? የምዕራባውያን የቅኝ ግዛት ታሪክ አልከሸፈም? የሶቭየት ኅብረት የኮሚዩኒስት ታሪክ አልከሸፈም? የታሪክ ባለሙያዎች ጭምር ታሪክን በሁለት እግሩ ብቻውን ቆሞ የሚሄድ ነፍስ ያለው ነገር አድርገው ይወስዱታል፤ አግርም

[26] ስለኢትዮጵያ ታሪክ ለማወቅ የፈለገ ሰው ፕሮፌሰር ዓለሜ እሸቴ (ነፍሱን ይማረውና) ፕሮፌሰር ተከስተ ነጋሽ፣ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ የጻፉትን ፈልጎ በማንበብ ቢጀምር ወደትክክለኛው ግንዛቤ ሊደርስ ይችላል፤ ሌላ ቢቀር እነዚህ ሦስት ምሁራን ጊዜ ከሰጣቸው ጥራዝ ነጠቆች የተለየ መሠረት እንዳላቸው መረዳቱ የሚጠቅም ይመስለኛል፤ ሁሉም የጻፉት በእንግሊዝኛ ስለሆነ አንድ ሰው ወይም ድርጅት ሰብስቦ ቢተረጉመውና ቢያሳትመው ለወጣቱ ትውልድ ከፍተኛ ስንቅ ይሆንላቸዋል፤ መንግሥት ቢኖር ተከስተ ነጋሽንና ፍቅሬ ቶሎሳን ጋብዞ ከ6-12 ወራት ያህል የጥንት የኢትዮጵያን ታሪክ በአማርኛ እንዲያዘጋጁ ያደርግ ነበር።





የለው፤ ምንም የለው፤ የአንድ ሕዝብ የሥራ መዝገብ ነው፤ ሥራ ከሌለ መዝገቡ ምንም አያሳይም፤ ባዶ ይሆናል፤ የተከታታይ ዘመናት ሁኔታ ባዶ ይሆናል፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት መሳቂያ የነበረ የአሜሪካ ምክትል ፕሬዚደንት ነበረ፤ አንድ ሰው የዚህን ሰው ታሪክ ጻፍሁ ብሎ አንድ ባዶ ወረቀቶች የተጠረዙበት መጽሐፍ አሳተመ፤ መጽሐፉ ብዙ ገጾች ቢኖሩትም ከርእሱና ከጸሐፊው ስም በቀር አንድም ቃል አልነበረበትም፤ አዘጋጁ የዚያ ሰው ታሪክ ሙሉ በሙሉ የከሸፈ መሆኑን ለማሳየት ፈልጎ ያደረገው ነበር።

ምንም ያልተመዘገበ ነገር መኖሩ፣ ታሪክ ከበላ-ጠጣ-ተኛ-ተነሣ-በላ-ጠጣ-ተኛ ... የማያልፍ ሲሆን ወይም በላ-ጠጣ-ተኛ-ተነሣ-ተራበ-ተጠማ- ... ብቻ ሲሆን መክሸፍ የማይታየው ሰው እንደገና ያስብበት።


## የትውልዶች መወራረስ

የአንድ ሕዝብን፣ የአንድ አገርን እድገትና መሻሻል በየትም አገር ቢሆን አብዛኛው ሰው የሚመኘውና ዓላማው አድርጎ የሚመለከተው ይመስለኛል፤ **ወንድ ልጅ እንደአባቱ፣ ሴት ልጅ እንደእናትዋ ወይም ልጅ ለእናትዋ ምጥ አስተማረች** እያሉ በመተረት እየኖሩ እድገት አይመጣም፤ እድገት ማለት ወንድ ልጅ ከአባቱ የተሻለ፣ ሴት ልጅ ከእናትዋ ኑሮ መሻገር ሲችሉ ነው፤ **ልጆች በእውቀት ከወላጆቻቸው እየተሻሉ ሲቀጥሉ እድገት** ይሆናል፤ በሌላ አነጋገር የኑሮ ችግር ከወላጆች ወደልጆች እየቀለለ እንጂ እየከበደ እንዳይሄድ መጣር ነው፤ እንዲያውም ከተቻለ ችግሩን ፈጽሞ ለማጥፋት መሞከር የተሻለ ይሆናል።

ከዚህ በታች ባለው **በምስል አንድ (የማኅበረሰብ እውቀት እድገት)** የሚታየው የትውልዶች መወራረስን የሚያሳይ ነው፤ ለምሳሌ በአንድ መቶ ሃያ ዓመታት ውስጥ ስድስት ትውልዶች ይፈጠራሉ ብንል የመጀመሪያው ትውልድ የወረሰው ምንም ስለሌለው ከዜሮ ይነሣል፤ ሌሎቹ በተከታታይ 2፣3፣4፣5፣6 ይሆናሉ፤ በምስሉ ላይ እንደሚታየው ከመጀመሪያው ትውልድ

ቀጥለው የመጡት ሁሉ አንድ ክምር እየተጨመረባቸው አድገዋል፤ ይህም ተከታታይ ትውልዶች የየራሳቸውን አንድ ክምር አስተዋጽኦ እያበረከቱ የማኅበረሰቡን እውቀት አሳድገዋል ማለት ነው።

### ምስል አንድ
***የማኅበራዊ እውቀት እድገት የተለያዩ ትውልዶች አስተዋጽኦ***



ሀ ለ ሐ መ ሠ ረ

አንድ ትውልድ ምንም ካላደረገ የሚቀጥለው ትውልድ ችግር እንደሚወርስና እንደሚቸገር ሳይታለም የተፈታ ነው፤ በቀላሉ እንየው፤ የአንድ አገር የሕዝቡ ቁጥር አንድ መቶ ቢሆን (ጅቦች የሉም ብለን በመገመቴ) በአገሩ ውስጥ ያለው ሀብት ሁሉ ለመቶ ይከፈላል፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ግን የሕዝቡ ቁጥር ሦስት ከመቶ ቢጨምር፣ አንድ መቶ ሦስት ስለሚሆን የእያንዳንዱ ሰው ድርሻ በዚያው መጠን ይቀንሳል፤ ሁኔታው በያመቱ ካልተለወጠ






የእያንዳንዱ ሰው ድርሻ እየቀነሰ ስለሚሄድ ሕዝቡ ወደድህነት አዘቅት መንሸራተቱ ግዴታ ይሆናል፤ ይህንን ሳይገነዘብ አሥር ዓመታት፣ መቶ ዓመታት፣ አንድ ሺህ ዓመታት የሚያሳልፍ ሕዝብ በሽርተቱ ታሪኩ ይጎዳል፤ በመክሸፉ እየኮራና እያቅራራ ቁልቁቱን ይንደረደራል፤ ውድቀት የተረጋገጠ የመክሸፍ ውጤት ይሆናል።

**በምስል ሁለት፣** በአጠቃላይ ማኅበራዊ እድገት ላይ እንደሚታየው (ሀ) ተብሎ በተሰየመው አገር ጥንት አንድ ትውልድ የሠራው ነገር በአገሩ ሕዝብ ታሪክ ሆኖ ይነገራል፤ ከዚያ ጥንት ከነበረው ትውልድ በኋላ በተከታታይ የመጡት ሁሉ ምንም ነገር በአገሩ ላይ አልጨመሩም፤ ስለዚህም ማኅበረሰቡ በደረቱ እየተሳበ የሚሄድ፣ ኋላ-ቀርነትንና ደህነትን እየተወራረሰ የሚጓዝ ማኅበረሰብ ነው፤ በአፍሪካም ሆነ በእስያ፣ በደቡብ አሜሪካም ዛሬም እርቃናቸውን የሚሄዱ የጥንት አባቶቻቸው ከነበሩበት ያልወጡ ማኅበረሰቦች አሉ፤ ሌሎች አገሮች ደግሞ በአንድ ዘመን በከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ላይ ደርሰው ብዙ ድንቅ የሚባሉ ሥራዎችንም ሠርተው፣ እድገታቸው በመቋረጡ ቁልቁለቱን የወረዱና አሁንም በመውረድ ላይ ያሉ አገሮች አሉ፤ እነዚህ **በምስል ሁለት** (ለ) የሚታየው ዓይነት የታሪክ ጉዞ ያላቸው ናቸው፤ ዳገቱን ወጥተው ቁልቁለቱን የሚወርዱ!

**በምስል ሁለት** (ሐ) የሚታየው ሁኔታ በጣም የተለየ ነው፤ በእንደዚህ ያሉት አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች መጨረሻው የማይታወቅና የማያቋርጥ እድገት የሚያስመዘግቡ የነቁና ተንቀሳቃሽ የሆኑ ናቸው፤ በማኅበረሰቦች መሀከል እንዲህ ያሉ ከፍተኛ ልዩነት የሚታይበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ብዙ ጥናቶች ተደርገዋል፤መጻሕፍትም ታትመዋል፤[27] እንዱ ሕዝብ ኑሮን

[27] ለምሳሌ፣ Daron Acemoglu and James A. Robinson, Why Nations Fail: The Origins of Power, Prosperity, and Poverty, New York, 2012.

## ምስል ሁለት
### አጠቃላይ የማኅበራዊ እድገት አቅጣጫዎች




አስረጂ:—

1. ሣጥን ውስጥ ያለው ወፍራም መስመር የብዙ ትውልዶችን ጉዞ ያመለክታል፤ ወደላይ እድገት ነው፤ ቁልቁል ውድቀት ነው::
2. የተጋደመው ቀስት ዘመናትን ከጥንት ወደአሁን ያሳያል::
3. የቆመው ቀስት የእድገትን አቅጣጫን ያምለከታል::

ከዕለት ምግብና ከዓመት ልብስ ባሻገር ማየት የማይችል ወይም የማይፈልግ ይሆንና ያለፈው ትውልድ በተወለት ቅርስ እየተጠቀመ ጊዜውን ያሳልፋል፤ ለሥራም ያለው ክብር ዝቅተኛ በመሆኑ:--





ዓለም አላፊ ነው፤
መልክ ረጋፊ ነው፤
አዱኛ ጠፊ ነው፤

እያለ ለሚቀጥሉት ትውልዶች ቅርስ ሊያስቀምጥ በማይችልበት የችግር ኑሮ ውስጥ እየተንገዳገደ ያልፋል፤ በእውነቱ ግን አያልፍም፤ ምክንያቱም ችግሩንና ደህነቱን፤ ድንቁርናውንና ሕመሙን ያወርሳል፤ በዚህ ላይ የሕዝብ ቁጥር ከፍ ከማለቱ ጋር ሕዝቡ ከነበረበት ደረጃ ይወርዳል፤ በቁሞ-ቀሩ (ሀ) አገር የሚያጋጥመን እንዲህ ያለ የማይነቃነቅ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ሕዝብን ነው፤ በ**ምስል ሁለት** (ሀ) የሚታየው ማኅበረሰቡ ከገነት ከተባረረ በኋላ ግራ ገብቶት ምንም ሳያደርግ ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል እያለ፣ ሁልጊዜም ትናንትን እያመሰገነ የሚኖር ነው፤ ነገም ከዛሬ የባሰ እንደሚሆን ስለሚጠረጥር የባሰ አታምጣ እያለ የሚጸልይ ነው፤ ወደታች ይወርድ እንደሆነ እንጂ ወደላይ የመውጣት ዝንባሌ የለውም፤ እንደእባብ በደረቱ እየተሳበ የሚጓዝ ማኅበረሰብ ነው፤ ችግር የተዋጎደው ስለሆነ ችግርን እንደባዕድ፣ እንደጠላት አይመለከተውም፤ ከዕለት እንጀራና ከዓመት ልብስ[28] የበለጠ ነገር አይመኝም፤ በእንደዚህ ያለ ማኅበረሰብ ጊዜ ይጫወትበታል፤ መምሸቱን ሳያውቅ ይጨልማል፤ መንጋቱን ሳያውቅ ረሀብ ይቀሰቅሰዋል፤ ሰው መሆኑን ሳያውቅ ይሞታል፤ በእንደዚህ ያለው ማኅበረሰብ ጊዜ የሚጫወተው በሰው ላይ ብቻ አይደለም በመሬትም ላይ ነው፤ መሬቱ በሰዎች ጭነት ምክንያት ይቆሽሻል፤ ይደኸያል፤ ይጠባል፤ ሀብታሞች ወደላይ ግንብ-ሰናኦርን

[28] ምናልባት በዘመናችን ሁሉም ቀርቶ የዕለት ጫት አታሳጣኝ የሚባልበት ዘመን ሳንገባ አልቀረንም፤ አንድ ጊዜ ኃይለኛ ዝናብ እየወረደ ወደቤቴ ልገባ ስል ሁለት ሰዎች መንገዱ ዳር ካርቶን ላያቸው ላይ ጭነው ተኝተው አየሁ፤ ቤቴ እንደገባሁ በሁለት ፌስታል ለእያንዳንዳቸው አንድ ሱሪ፤ አንድ ሹራብ፤ አንድ ትልቅ ፎጣ ከተትሁና ስሮጥ ወስጄ ሰጠኋቸው፤ አንድ ቀን ለብሰውት አየሁ፤ በቃ፤ በሌላ ቀን አንድ ሰው በጣም ብርድ በሆነ ሌሊት ድንጋይ ተንተርሶ ኩርምት ብሎ ጉልበቱን አቅፎ አየሁትና ስለሱ በረደኝ፤ አንድ ጥሩ ኩታ ወስጄ አለበስሁት፤ በሦስተኛው ቀን ኩታው አልነበረም፤ ከዚያ በኋላ ቤት ያጣብባል እንጂ ልብስ መስጠት ተውሁ::

ሲክቡ ደሀው አግሩን ዘርግቶ የሚተኛበት ያጣል፤ በሀ) የሚታየው ምስል የሚያመለክተው ይህንን ነው።

በለ) የሚታየው ስዕል የሚያመለክተው **አይቶ ከማጣት ያድናችሁ** የሚል ነው፤ በድንጋይ ዳቦ ዘመን በአንጻራዊ ግምት በከፍተኛ ደረጃ ላይ የነበረ ማኅበረሰብን ያሳያል፤ ማኅበረሰቡ በሚያስደንቅ ትጋት ያለማቋረጥ ቁልቁለቱን ተያይዞታል፤ አያቅም እንዳይባል በእድገት ጫፍ ላይ የነበሩ ቅማያቶቹ ቅርስ ትተውለታል፤ ኩራትና ክብር ምን እንደሆኑ ባያውቅም ከአባት ከእናቱ ሰምቷል፤ መስማቱ የሚረጋገጠው በፉከራውና በሽለላው፣ በቀረርቶው፣ ሌሎች በጻፉለት ታሪክ፣ አንዳንዴም ሌሎች በሠሩለት ሐውልት፣ በዘፈኖቹና በግጥሞቹ ነው፤ ዛሬ እሱና እስዋ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ሲጠየፏቸው ለነበሩ ሰዎች አገልጋዮች ሆነው በሚሰማቸው ውርደት ነው።

የደሀነትና የጉስቁልና ገደል ውስጥ ሆነው ቀና እያሉ አባቶቻቸው የነበሩበትን ተራራ እያዩ **‹አይቶ ከማጣት ያድናችሁ!›** የሚል ልመና ባህላቸው አድርገው የሚኖሩ ናቸው፤ ሥራን በንግግር፣ ልማትን በልመና፣ እውቀትን በድንቁርና፣ ሕዝባዊ ስሜትን በጎሠኛነት እየተኩ ቁልቁለቱን የሚንደረደሩ ማኅበረሰቦች ናቸው፤ አንድ የእንግሊዝ ጸሐፊ ይመስለኛል የሚከተለውን የተናገረው፡ ---- **‹በጀግኖች አያቶቻቸው የሚሸልሉ ሕዝቦች እንደድንች ናቸው የሚኮሩበት ሀብት ሁሉ ከመሬት በታች ነው፤›** ድንች ከላይ የሚታየው ቅጠሉ ነው፤ ዋናው ፍሬው በመሬት ውስጥ ተቀብሮ የማይታይ ነው፤ በምስል ሀ)ና በምስል ለ) መሀከል ያለው ልዩነት የደረጃ ሳይሆን የልምድ ነው፤ በለ) ያሉት ከበስተጀርባቸው የሚያኮራ ወሬ አላቸው እንጂ በሁኔታቸው በሀ) ካሉት እምብዛም አይለዩም።

በሐ) የሚታየው ምስል ከሌሎቹ ከሁለቱ በጣም የተለየ ነው፤ እንደዚህ ያለው ሁኔታ የሚታይባቸው ማኅበረሰቦች የሚያሳዩት የእድገት አቅጣጫ ነው፤ ከታች ጀምረው ወደላይ፣ ከደሀነት ጀምረው ወደሀብታምነት፣ ከደካማነት ጀምረው ወደኃይለኛነት አቀበቱን በመውጣት የሠለጠኑ ናቸው፤ የሠለጠኑ ማለት ከሚያጋጥሟቸው ማናቸውንም ዓይነት ችግሮች ጋር





በኅብረት እየተጋፈጡ መፍትሔዎችን የሚያገኙላቸው ናቸው፤ እንደዚህ ያሉት ማኅበረሰቦች የሚታወቁባቸው ዋና ዋና ነገሮች እውቀት፣ ሥልጣኔ፣ ሥራ፣ ምርታማነትና ሀብት ናቸው።

ብዙዎች በሐ) ደረጃ ውስጥ የገቡ አገሮች የዕለት ኑሮ የሚባለውን አሸንፈው ለሩቁ የሚተልሙ፣ በስሜት ሳይሆን በአእምሮ የሚገዙ፣ ነጻነት፣ እውነት፣ እውቀት ሲረጋገጡ እድገት፣ እኩልነት፣ ፍትሕና ብልጽግና እንደሚከተሉ የታመነ ነው።

ከላይ የተመለከቱትን ሦስት በጣም የተለያዩ ምስሎች በመመልከት የከሸፈውንና ያልከሸፈውን ለመገንዘብ የሚያስቸግር አይመስለኝም፤ በኋላ እንደምንመለከተው አንዳንዶች ብልጣብልጥ ለመሆን የሞከሩ ተቺዎች ታሪክን እንደባዶ ቅል አይተውት ታሪክ እንዴት ይከሽፋል የሚል ጥያቄ ሰንዝረዋል፤ ታሪክ ገዞ ላይ ያለ ባቡር ነው፤ ባቡሩ ማኅበረሰቡን ይዞ ሲከሽፍ ጉዞው ይከሽፋል።

የአንድ ዓመት መክሸፍ ትምህርት ካልሆነ፣ የአሥር ዓመት መክሸፍ ትምህርት ካልሆነ፣ የመቶ ዓመትና የሺህ ዓመታት መክሸፍ ትምህርት ካልሆነ መክሸፍ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ባህልም ይሆናል፤ ብዙ ሰዎች ይህንን መረዳት ለምን እንዳቃታቸው አልገባኝም፤ እንደሚመስለኝ ለመራቀቅ ሲፈልጉ ተጨባጭ ታሪክን ከረቂቅ ሀሳብ ለይተው ለማየት ባለመቻላቸው ነው፤ ሁለትና ሁለት አራት ነው ሲባል ምንም ምንም በሌለበት በረቂቅ ሀሳብ ደረጃ ነው፤ ሁለት እንቁላልና ሁለት ድንች አራት አይሆኑም የምንለው መሬት ወርደን በተጨባጭ ሁኔታ ስንናገር ነው።

## የታሪክ መሠረት

የታሪክ ድርና ማግ ቦታና ጊዜ ናቸው፤ ቦታ ድር ሲሆን ማጉ ደግሞ ጊዜ ነው፤ ታሪክ በአግባቡ ቦታንና ጊዜን እያገናኘ ይፈትላል፤ ያለጊዜና ያለቦታ ታሪክ የሚባል ነገር አይኖርም፤ ነገር ግን ቦታም ሆነ ጊዜ በማናውቀው ዓለመዓለምና በዘለዓለም

የተወሰነ ነው፤[29] ዓለመዓለምና ዘለዓለም ለተፈጥሮ ታሪክና ለሰው ልጆች ታሪክ የተለያዩ ትርጉሞች አሏቸው፤ ሰፊው ዓለም ከተፈጠረ አሥራ አምስት ቢልዮን ዓመታት ሆኖታል ይላሉ የእውቀቱ ባለቤቶች፤[30] በአንጻሩ የኛ ዓለም በጣም ሕጻን ነው፤ ስለዚህም የአሥራ አምስት ቢልዮን ዘለዓለምና የጥቂት ሚልዮኖች-ዘለዓለም በጣም የተለያዩ ናቸው።

በምድራችን ዓለም ውስጥ ማናቸውም ነገር ቦታ አለው፤ ማናቸውም ነገር ዕድሜ አለው፤ ቦታው ታሪክ የሚሠራበት መድረክ ነው፤ ጊዜ ሥራው መጀመሪያ፣ አካሄድና ፍጻሜ የሚመዘገብበት ነው፤ ስለዚህም ከቦታና ከጊዜ ውጭ ታሪክ የምንለው ነገር አይኖረንም።

## የተፈጥሮ ታሪክ

የተፈጥሮ ታሪክ መሠረቱ ጂኦሎጂ የሚባለው የግዙፉን የዓለም ታሪክ የሚያጠና የእውቀት ክፍል ነው፤ ጂኦሎጂ ከድንጋዮች ጋር እየተነጋገረና እየመረመራቸው የተፈጥሮን ታሪክ ያጠናል፤ዘመናቸውን እየጠበቀ ዕጸዋትም፣ እንስሳትም ሰውም ድንጋይ ይሆናሉ፤ የሳይንስ ተመራማሪዎች እንደሚሉት የሰው ልጅ በምድር ላይ ብቅ ያለው ከዛሬ አሥራ አንድ ሺህ ዓመታት በፊት ነው፤ የኖዩቱ ሰው-መሳይዎ ድንቅነሽ ወደሦስት ሚልዮን ዓመታት ይሆናታል መሰለኝ፤ የሰው ልጅ አሁን ታሪኩን መቁጠር ከጀመረ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሁለት ሺህ አንድ መቶኛውን ዓመት ገና መያዙ ነው።

በተፈጥሮ ታሪክ የሚከሰቱ ‹አብዮቶች› አሉ፤ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ኃይለኛ ጎርፍ፣ ኃይለኛ አውሎ ነፋስ፣ ኃይለኛ ዝናብ ወይም በረዶ፣ የመሬትንና በላይዋ ላይ ያሉትን ሁሉ መልካቸውን

---

[29] በአማርኛ ቃል መኖሩን እርግጠኛ አይደለሁም፤ በእንግሊዝኛ «ዩኒቨርስ UNIVERSE» የሚባለው ገና ድንበሩ ያልታወቀ እጅግ ሰፊ የሆነ እየሰፋም የሚሄድ ገና ያልተደረሰበትና በቅጡ ያልታወቀ እኔ ዓለመዓለም ያልሁት ነው፤ በአንዳንዶቹ ከዋክብት መሀከል ያለው ርቀት እስከአንድ መቶ ሚልዮን የብርሃን ዓመታት ይሆናል፤ አንድ የብርሃን ዓመት ማለት ብርሃን በአንድ ዓመት ውስጥ የሚጓዝበት ርቀት ሲሆን (የብርሃን ፍጥነት በአንድ ሰኮንድ 299 792.5 ኪሎሜትር) ነው።

[30] በኢትዮጵያ አቆጣጠር ገና ስምንተኛው ሺህ ላይ ነን፤ 7507 ዓመተ ዓለም ይመስለኛል።






ፈጽሞ የሚለውጥ ኃይል አለ፤ በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የሚባለው አንዱ የተፈጥሮ አብዮት ውጤት ነው፤ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ተራሮችም የአብዮት ውጤቶች ናቸው፤ በተፈጥሮ አብዮት ተራራ የነበረው ሜዳ ወይም ገደል ይሆናል፤ሜዳ ወይም ገደል የነበረው ተራራ ይሆናል፤ ውሀ ተሸክሞ የነበረው መሬት ከውሀው በላይ ይሆናል፤ የወንዝ ሸለቆው ይገደብና ሐይቅ ይፈጠራል፤ሐይቁ ይደርቅና መሬት ይሆናል፤ከነዚህ ለውጦች ጋር ተያይዞ የዓየር ጠባዩና የዕጸዋቱ ዓይነትና ብዛት ሊለወጥ ይችላል፤ ብዙ የተለያዩ ማዕድኖችም የሚፈጠሩት በዚህ የተፈጥሮ አብዮት ጊዜ ነው፡

## የሰው ልጆች ታሪክና ችግር

ችግር የኑሮ ቅመም ነው፤ ያለችግር ኑሮ እንደውሀ ጣዕም የሌለው ነገር ይሆን ነበር፤ ችግር ሳይሰማቸው የሚኖሩ ሰዎች ኑሮን አያውቁም፤ አንድ ሰው ከውጭ ከሚመጣበት ኃይል ወይም ግፊት ጋር ብቻ ሳይሆን ከውስጥም ከራሱ ከሚመነጭ ግፊት ወይም ኃይል ጋር ይታገላል፤ ከውስጥ ስሜቱ ደስ የሚለውን ነገር እያመለከተ፣ ሀሳቡ ደግሞ ትክክለኛውን ነገር እያሳየው ግጭት ወይም ጦርነት ያስተናግዳል፤ ከዚህ ጦርነት ድል አድርጎ የሚወጣው አዲስ አቅጣጫን ያስይዝ ይሆናል፤ ለውጥ የተፈጥሮ ዕዳ ነው፤ ማደግ የተፈጥሮ ዕዳ የሆነውን ያህል መበስበስም የተፈጥሮ ዕዳ ነው፤ ከዚህ ዕዳ ግለሰብም አያመልጥም፤ ማኅበረሰብም አያመልጥም፤ ሕዝብም አያመልጥም፤ ድንጋይም እንኳን አያመልጥም፤ ማናቸውም ነገር ይለወጣል፤ አፈር ድንጋይ ይሆናል፤ ድንጋይ አፈር ይሆናል።

ለሰው ልጆች የግዴታ ለውጥ እንዳለ ሁሉ የውዴታ ለውጥም አለ፤ ማርጀት፣መሞት፣ መበስበስ የግዴታ የተፈጥሮ ለውጦች ናቸው፤ በድንቁርና መጨነቅ፣ በበሽታ መሰቃየት፣ በደሀነት መቆርቆዝ፣እርስ-በርስ በመጠላለፍ መዳከም፤ በአቅመ-ቢስነት መዋረድ በግዴታም በውዴታም የሚመጡ ለውጦች ናቸው፤ መጥፎው ለውጥ የሚመጣው ያሉበትን ሁኔታ አጥርቶ ለማወቅ ጠልመሞከርና ለታወቁት ችግሮች መፍትሔዎችን

ለማግኘት ባለማሰብ ነው፤ በሌላ አነጋገር ድንቁርና፣ በሽታ፣ ደሀነት፣ ጥላቻ፣ ደካማነት እየተጠኑና እየተመረመሩ በየጊዜው ያለማቋረጥ መፍትሔዎች ካልተገኙላቸው ለውጥ ማለት መበስበስ ብቻ ይሆናል፤ ከዚህ የመበስበስ አቅጣጫ ለመውጣት ከተፈለገ ከሁሉ በፊት የመበስበስ አቅጣጫ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ይህ የተያዘው የመበስበስ አቅጣጫ ከአንድ ግለሰብ የመነጨ አይደለም፤ በአንድ ግለሰብም የሚቀለበስ አይደለም፤ ተደጋግፈው የተኙበት መበስበስ ስለሆነ ተደጋግፈው መነሣት ያስፈልገዋል፤ ወደጉዳት የሚያመራውን አቀጣጫ ለመተውና ወደእውቀት፣ ወደጤንነት፣ ወደትብብር፣ ወደብልጽግናና ወደብርታት ወደሚወስደው አቅጣጫ ለመዞር ፍላጎትንና ቁርጠኛነትን ይጠይቃል።






*ተሰባብሮ የወደቀው የሚጠግነው ትውልድ እንኳን አላገኘም፤*







*ይህ ሕንጻ አ... ድንጋዩ*
*ብሎ በአክሱም የሚገኙ ብዙ የ...*
*የተሠሩ ናቸው፤ ዛሬ ግማሾቹ ወደ...*
*አልመጣም።*



*ይህ ከድንጋይ የተሠራ ሕንጻ ...*


ለማግኘት ባለማሰብ ነው፤ በሌላ አነጋገር ድንቁርና፣ በሽታ፣ ደህነት፣ ጥላቻ፣ ደካማነት እየተጠኑና እየተመረመሩ በየጊዜው ያለማቋረጥ መፍትሔዎች ካልተገኙላቸው ለውጥ ማለት መበስበስ ብቻ ይሆናል፤ ከዚህ የመበስበስ አቅጣጫ ለመውጣት ከተፈለገ ከሁሉ በፊት የመበስበስ አቅጣጫ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ይህ የተያዘው የመበስበስ አቅጣጫ ከአንድ ግለሰብ የመነጨ አይደለም፤ በአንድ ግለሰብም የሚቀለበስ አይደለም፤ ተደጋግፈው የተኙበት መበስበስ ስለሆነ ተደጋግፈው መነሣት ያስፈልገዋል፤ ወደጉዳት የሚያመራውን አቀጣጫ ለመተውና ወደእውቀት፣ ወደጤንነት፣ ወደትብብር፣ ወደብልጽግናና ወደብርታት ወደሚወስደው አቅጣጫ ለመዞር ፍላጎትንና ቁርጠኛነትን ይጠይቃል፡፡

ተሰባብሮ የወደቀው የሚጠግነው ትውልድ እንኳን አላገኘም፤









ይህ ሕንጻ አለት ድንጋዩ በአለበት እየተፈለፈለ የተሠራ ነው፤ ከዚህ ቀደም ብሎ በአክሱም የሚገኙ ብዙ የቆሙ ሐውልቶችም እንዲሁ ከአንድ ድንጋይ የተሠሩ ናቸው፤ ዛሬ ግማሾቹ ወድቀው ተሰባብረዋል፤ የሚጠግናቸው ትውልድ ገና አልመጣም፡፡



ይህ ከድንጋይ የተሠራ ሕንጻ በደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ነው፤

ለማግኘት ባለማሰብ ነው፤ በሌላ አነጋገር ድንቁርና፣ በሽታ፣ ደሀነት፣ ጥላቻ፣ ደካማነት እየተጠኑና እየተመረመሩ በየጊዜው ያለማቋረጥ መፍትሔዎች ካልተገኙላቸው ለውጥ ማለት መበስበስ ብቻ ይሆናል፤ ከዚህ የመበስበስ አቅጣጫ ለመውጣት ከተፈለገ ከሁሉ በፊት የመበስበስ አቅጣጫ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ይህ የተያዘው የመበስበስ አቅጣጫ ከአንድ ግለሰብ የመነጨ አይደለም፤ በአንድ ግለሰብም የሚቀለበስ አይደለም፤ ተደጋግፈው የተኙበት መበስበስ ስለሆነ ተደጋግፈው መነሣት ያስፈልገዋል፤ ወደጉዳት የሚያመራውን አቀጣጫ ለመተውና ወደእውቀት፣ ወደጤንነት፣ ወደትብብር፣ ወደብልጽግናና ወደብርታት ወደሚወስደው አቅጣጫ ለመዞር ፍላጎትንና ቁርጠኛነትን ይጠይቃል።።







ተሰባብሮ የወደቀው የሚጠግነው ትውልድ እንኳን አላገኘም፤








ይህ ሕንጻ አለት ድንጋዩ በአለበት እየተፈለፈለ የተሠራ ነው፤ ከዚህ ቀደም ብሎ በአክሱም የሚገኙ ብዙ የቆሙ ሐውልቶችም እንዲሁ ከአንድ ድንጋይ የተሠሩ ናቸው፤ ዛሬ ግማሾቹ ወድቀው ተሰባብረዋል፤ የሚጠግናቸው ትውልድ ገና አልመጣም።።



ይህ ከድንጋይ የተሠራ ሕንጻ በደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ነው፤




የነበረው የድንጋይ ሥራ ጥበብ የሚያስገርም ነው፤









የዛሬው ትውልድ የሚኖርባቸው ጎጆዎች እነዚህ ናቸው፤ ይህ መከሸፍ አይባልም?



የከሸፈ ትውልድ የሚኖርበት ጎጆ!



የደብረ ዳሞ ገዳም

ወደጥሩው ለውጥ የሚወስደውን አቅጣጫ ለመያዝ
የማያስችለው ጋሬጣ አዳፍኔ ነው፤ የአዳፍኔ ዋናው ሥራ
ጤንነት፣ እውቀት፣ ትብብር፣ ብልጽግና፣ ማኅበራዊ ጥንካሬ
እንዳይፈጠሩና ሕዝቡ ወይም ማኅበረሰቡ ደካማና ተስፋ-ቢስ ሆኖ
በቀላሉ ለመገዛት የሚመች እንዲሆን ነው፤ ጤና-ቢስነትና አቅመ
ቢስነት የማኅበረሰቡ መለያ ባህል ሲሆኑ፣ በተናጠል እያሰበ
በመነታረክ ለአዳፍኔ መመቸት ባህል ሲሆን ማኅበረሰቡ የማደግ
የመሻሻል ተስፋ ሊኖረው አይችልም፤ አዳፍኔ የሕዝቡን አእምሮ
የሕዝቡን ልብ ረግጦ ቆምበታል ማለት ነው፤ አእምሮና ልብ
ከቆመ ለሰው ልጅ ምን ቀረ? ሆዱ ብቻ! ሆዱ የአዳፍኔ መጫወቻ
ያደርገዋል።

የአዳፍኔ መጫወቻ የሆነ ማኅበረሰብ ወይም ሕዝብ
ከአለበት የኑሮ ሁኔታ ሳይነቃነቅ፣ ትውልዶችና ዓመቶች እያለፉ
ባለበት ቆሞ ይቀራል፤ ልጅ እንዳባቱ እየተባለ በልማድና በወግ
ተሳስሮ አዳዲስ ሀሳቦችን፣ ጥበቦችንና ብልሃቶችን እንዳይመ
እንኳን ካበድ ተጽእኖ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ያርፋል።

ችግር የማይነካቸው ሰዎች ከላይም ከታችም አሉ
የላይኞቹ እንደደላቸው ኑሮ ሰልችቷቸውና እነሱም ተሰልችተው
ይሞታሉ፤ የታችኞቹ ደግሞ በማያቋርጥ ስቃይና መከራ ደንዝዘው
ከቆዩ በኋላ ወደዘለዓለማዊ መደንዘዝ ይተላለፋሉ፤ እነዚ






ከላይም ከታችም ያሉና ችግር የማይሰማቸው ሰዎች በተፈጥሮ ቁጥጥር ስር ናቸው፤ የተፈጥሮ ኃይሎች ሁሉ ጊዜን ተገን አድርገው እየገዘገዙ የተፈጥሮ የለውጥ ወፍጮ ውስጥ እየከተቱ አፈር ያደርጓቸዋል፤ የግዴታ ለውጥ ይህ ነው።

ስሜትን የሚያቆስልና ብሶትን የሚያጎላ፣ አእምሮን የሚኮረኩርና የሚያሳስብ ችግር ነው፤ የዛሬ ችግር ለነገ እንዳይደገም ዘዴ ሲፈለግለት ሥራ ይፈጠራል፤ አሜሪካኖች ችግሮች የሚኖሩት መፍትሔዎች እንድንፈልግላቸው ነው፤ ይላሉ፤ እንዲያውም እድገትና መሻሻል የሚመጣው ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን እየተንተራሰ ነው፤ በችግሮች ብቻ ተተብትቦ መፍትሔዎቹን ለመፈለግ ሁኔታዎች የማይፈቅዱለት ሕዝብ እድገትን አያይም፤ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየው ይህንን ነው፤ መክሸፍ ማለት የወረሷቸውንና እነሱም የፈጠሯቸውን ችግሮች ለተከታታይ ትውልዶች እያሳለፉ ማለፍ ነው።

ለዘመናት ችግሮች ያለመፍትሔ እንዲባዙና የኢትዮጵያን ሕዝብ ኑሮ እንዲያቆረቁዝ የሆነበት አንዱ ምክንያት በችግር መኖርን የሚጠላና የሚነቅፍ አለመኖሩ ነው፤ አንድ ደሀ ሕዝብ ትምህርት ቤት አሠርቶና አስተማሪዎች ቀጥሮ አሥራ ሁለት ዓመት ያስተማረው ልጅ ከአባቱ ጋር ደበሎ ለብሶ ሲያርስ አይቻለሁ፤ ደበሎ ለብሶ ከአባቱ ጋር ማረሱን አሥራ ሁለት ዓመት በትምህርት ቤት ሳያሳልፍና ሳይለፋ ሊያደርገው ይችል ነበር!

ነቀፌታ ሁለት ዓይነት ነው፤ አንዱ ስሜት ነው፤ መጥላት ነው፤ አለመውደድ ነው፤ ይህ ዓይነቱ ነቀፌታ ራሱ ሊታረም አይችልም፤ ለማረምም አይችልም፤ ሌላው ነቀፌታ ከስሜት ሳይሆን ከአስተሳሰብ የሚመነጭ ሊሆን ይችላል፤ አለዚያም ስሕተቱን በማስወገድ ሰዎችን ለመርዳት ነው፤ ለምሳሌ አንድ ጊዜ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስታወቂያ በባንኩ ውስጥ ያለው የውጭ ምንዛሪ በሚልዮን እያለ የሚያስከትለው



የደብረ ዳሞ ገዳም

ወደጥሩው ለውጥ የሚወስደውን አቅጣጫ ለመያዝ የማያስችለው ጋሬጣ አዳፍኔ ነው፤ የአዳፍኔ ዋናው ሥራ ጤንነት፣ እውቀት፣ ትብብር፣ ብልጽግና፣ ማኅበራዊ ጥንካሬ እንዳይፈጠሩና ሕዝቡ ወይም ማኅበረሰቡ ደካማና ተስፋ-ቢስ ሆኖ በቀላሉ ለመገዛት የሚመች እንዲሆን ነው፤ ጤና-ቢስነትና አቅመ-ቢስነት የማኅበረሰቡ መለያ ባህል ሲሆኑ፣ በተናጠል እያሰቡ በመነታረክ ለአዳፍኔ መመቸት ባህል ሲሆን ማኅበረሰቡ የማደግና የመሻሻል ተስፋ ሊኖረው አይችልም፤ አዳፍኔ የሕዝቡን አእምሮና የሕዝቡን ልብ ረግጦ ቆሞበታል ማለት ነው፤ አእምሮና ልብ ከቆመ ለሰው ልጅ ምን ቀረ? ሆዱ ብቻ! ሆዱ የአዳፍኔ መጫወቻ ያደርገዋል።

የአዳፍኔ መጫወቻ የሆነ ማኅበረሰብ ወይም ሕዝብ ከአለበት የኑሮ ሁኔታ ሳይነቃነቅ፣ ትውልዶችና ዓመቶች እያለፉ ባለበት ቆሞ ይቀራል፤ ልጅ እንዳባቱ እየተባለ በልማድና በወግ ተሳስሮ አዳዲስ ሀሳቦችን፣ ጥበቦችንና ብልሃቶችን እንዳይመኝ አንኳን ካበድ ተጽእኖ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ያርፋል።

ችግር የማይነካቸው ሰዎች ከላይም ከታችም አሉ፤ የላይኞቹ እንደደላቸው ኑሮ ሰልችቷቸውና እነሱም ተሰልችተው ይሞታሉ፤ የታችኞቹ ደግሞ በማያቋርጥ ስቃይና መከራ ደንዝዘው ከቆዩ በኋላ ወደዘለዓለማዊ መደንዘዝ ይተላለፋሉ፤ እነዚህ



የደብረ ዳሞ ገዳም

ወደጥሩው ለውጥ የሚወስደውን አቅጣጫ ለመያዝ የማያስችለው ጋሬጣ አዳፍኔ ነው፤ የአዳፍኔ ዋናው ሥራ ጤንነት፣ እውቀት፣ ትብብር፣ ብልጽግና፣ ማኅበራዊ ጥንካሬ እንዳይፈጠሩና ሕዝቡ ወይም ማኅበረሰቡ ደካማና ተስፋ-ቢስ ሆኖ በቀላሉ ለመገዛት የሚመች እንዲሆን ነው፤ ጤና-ቢስነትና አቅመ-ቢስነት የማኅበረሰቡ መለያ ባህል ሲሆኑ፣ በተናጠል እያሰቡ በመነታረክ ለአዳፍኔ መመቸት ባህል ሲሆን ማኅበረሰቡ የማደግና የመሻሻል ተስፋ ሊኖረው አይችልም፤ አዳፍኔ የሕዝቡን አእምሮና የሕዝቡን ልብ ረግጦ ቆሞበታል ማለት ነው፤ አእምሮና ልብ ከቆመ ለሰው ልጅ ምን ቀረ? ሆዱ ብቻ! ሆዱ የአዳፍኔ መጫወቻ ያደርገዋል።

የአዳፍኔ መጫወቻ የሆነ ማኅበረሰብ ወይም ሕዝብ ከአለበት የኑሮ ሁኔታ ሳይነቃነቅ፣ ትውልዶችና ዓመቶች እያለፉ ባለበት ቆሞ ይቀራል፤ ልጅ እንዳባቱ እየተባለ በልማድና በወግ ተሳስሮ አዳዲስ ሀሳቦችን፣ ጥበቦችንና ብልሃቶችን እንዳይመኝ እንኳን ካበድ ተጽእኖ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ያርፋል።

ችግር የማይነካቸው ሰዎች ከላይም ከታችም አሉ፤ የላይኞቹ እንደደላቸው ኑሮ ሰልችቷቸውና እነሱም ተሰልችተው ይሞታሉ፤ የታችኞቹ ደግሞ በማያቋርጥ ስቃይና መከራ ደንዝዘው ከቆዩ በኋላ ወደዘለዓለማዊ መደንዘዝ ይተላለፋሉ፤ እነዚህ





ከላይም ከታችም ያሉና ችግር የማይሰማቸው ሰዎች በተፈጥሮ ቁጥጥር ስር ናቸው፤ የተፈጥሮ ኃይሎች ሁሉ ጊዜን ተገን አድርገው እየገዘገዙ የተፈጥሮ የለውጥ ወፍጮ ውስጥ እየከተቱ አፈር ያደርጓቸዋል፤ የግዴታ ለውጥ ይህ ነው።

ስሜትን የሚያቆስልና ብሶትን የሚያጎላ፣ አእምሮን የሚኮረኩርና የሚያሳስብ ችግር ነው፤ የዛሬ ችግር ለነገ እንዳይደገም ዘዴ ሲፈለግለት ሥራ ይፈጠራል፤ አሜሪካኖች ችግሮች የሚኖሩት መፍትሔዎች እንድንፈልግላቸው ነው፤ ይላሉ፤ እንዲያውም እድገትና መሻሻል የሚመጣው ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን እየተንተራስ ነው፤ በችግሮች ብቻ ተተብትቦ መፍትሔዎቹን ለመፈለግ ሁኔታዎች የማይፈቅዱለት ሕዝብ እድገትን አያይም፤ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያሳየው ይህንን ነው፤ መክሸፍ ማለት የወረሷቸውንና እነሱም የፈጠሯቸውን ችግሮች ለተከታታይ ትውልዶች እያሳለፉ ማለፍ ነው።

ለዘመናት ችግሮች ያለመፍትሔ እንዲባዙና የኢትዮጵያን ሕዝብ ኑሮ እንዲያቆረቁዝ የሆነበት አንዱ ምክንያት በችግር መኖርን የሚጠላና የሚነቅፍ አለመኖሩ ነው፤ አንድ ደሀ ሕዝብ ትምህርት ቤት አሠርቶና አስተማሪዎች ቀጥሮ አሥራ ሁለት ዓመት ያስተማረው ልጅ ከአባቱ ጋር ደበሎ ለብሶ ሲያርስ አይቻለሁ፤ ደበሎ ለብሶ ከአባቱ ጋር ማረሱን አሥራ ሁለት ዓመት በትምህርት ቤት ሳያሳልፍና ሳይለፋ ሊያደርገው ይችል ነበር!

ነቀፌታ ሁለት ዓይነት ነው፤ አንዱ ስሜት ነው፤ መጥላት ነው፤ አለመውደድ ነው፤ ይህ ዓይነቱ ነቀፌታ ራሱ ሊታረም አይችልም፤ ለማረምም አይችልም፤ ሌላው ነቀፌታ ከስሜት ሳይሆን ከአስተሳሰብ የሚመነጭ ሊሆን ይችላል፤ አለዚያም ስሕተቱን በማስወገድ ሰዎችን ለመርዳት ነው፤ ለምሳሌ አንድ ጊዜ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስታወቂያ በባንኩ ውስጥ ያለው የውጭ ምንዛሪ በሚልዮን እያለ የሚያስከትለው

ቁጥር በጭራሽ የማይደረስበት ነበር[31] ይህንን ግልጽ ስሕተት በጋዜጣ አወጣሁት፤ ከዚያ በኋላ ስሕተታቸውን ያርሙ ጀመሩ፤ የኔ ድርሻ ስሕተቱን ከመጠቆም አያልፍም ነበር።

ችግሮች መፍትሔዎችን እያገኙ የሕዝብን ኑሮ የሚያሻሽሉ ሲሆን ለውጥ ይመጣል፤ በሰዎች ሥራ ላይ፣ በሰዎች የሥራ ዘዴ ላይ፤ በሰዎች የኑሮ ደረጃ ላይ የሚመጣ ለውጥ ውሎ-አድሮ ሌሎች ለውጦችን ይወልዳል፤ የማያቋርጥ የለውጥ ፍላጎትን ማስተናገድ ባህል ይሆናል፤ የለውጥ ፍላጎት በበኩሉ የፈጠራን ችሎታ ያዳብራል።

ማናቸውም ጥሩ ነገር ያለምንም ጥረት በቀላሉና ያለዋጋ በነጻ አይገኝም፤ በምኞት ብቻም አይገኝም፤ ቁርጠኛ ፍላጎትና የማያቋርጥ ጥረትን ይጠይቃል፤ ጥረቱ ውጤት እስኪያስገኝ ድረስ መቀጠል አለበት፤ አንዳንድ ጊዜ አንዱ ትውልድ የጀመረውን ሌላው ትውልድ ይጨርሰው ይሆናል፤ ሰው በሁሉም ነገር ከተደሰተ፣ ለውጥ አንድ ነገር ብቻ ይሆናል፤ ተፈጥሮ በራሱ ዘዴና ጊዜ የሚፈጽመው ለውጥ ብቻ ተወደደም ተጠላ በግዴታ ይካሄዳል፤ ተፈጥሮ በማናቸውም ነገር ላይ የሚያመጣው ለውጥ ደስ ሊያሰኝ ይችላል፤ ወይም ሊያስከፋ ይችላል።

ጥያቄ፦ የውጭ ሰዎችና ታሪካችን

የእኔ ትውልድ ከውጭ አገር ሰዎች የተማረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነባህሉ የአረብ ውላጅ ተደርጎ ነው፤ የኛ ነው የምንለው ነገር ሁሉ ከአረብ ያገኘነው መሆኑን እየነገሩን እኛም በተራችን ያንኑ ለተከታዩ ትውልድ ስናስተምር ቆየን፤ የሴም ቋንቋ፣ ነገረ መንግሥት፣ እርሻ፣ ጽሕፈት … ሁሉም ነገር ከባሕር ማዶ ያገኘነው እየተደረገ ተማርን፤ እኛም በበኩላችን አስተማርን።

[31] ለምሳሌ በሚልዮን ብሎ 948 675 564 ቢጽፍ የሚሆነው 948 675 564 000 000 ነው፤ ይህንን ያህል ዶላር ቢኖር! አንዳንዴ 948.7 ተብሎ በሚልዮን ሲባል አይተው ነው!





እአአ በ1987 በእንግሊዝ አገር በኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲና በአሜሪካ በኮርኔል ዩኒቨርሲቲ ነገረ መንግሥት መምህር የነበረ ማርቲን በርናል የተባለ ሊቅ (Black Athena: The Afro-Asiatic Roots of Classical Civilization) የሚባል መጽሐፍ አሳተመ፤ ዝርዝር ውስጥ አልገባም፤ ግን በርናል የተማርነውን ሁሉ ገለበጠው፤ የሴም ቋንቋዎች ከኢትዮጵያ ወደባሕር ማዶ ተሻገሩ እንጂ ከዚያ ወደዚህ አልመጡም አለ! የአሥር ዓመታት የምርምር ውጤት ነበር፤ በአለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ውስጥ የበርናልን ፈር ተከትሎ የኢትዮጵያን ታሪክ ለመከለስ የሞከረ አንድም ባለሙያ መኖሩን አልሰማሁም፤ የታሪክ ተመራማሪ የሚባሉ ግን አሉ።

በርናል የጥንታውያን ግሪኮች ሥልጣኔ ከግብጽ፣ ከአፍሪካ ሊመጣ አይችልም በማለት ነጮች ግሪክን የሥልጣኔ እምብርት አድርገው ታሪክን በማወላገዳቸው ነበር፤ ይህ ሰው ማናቸውንም መረጃና እርዳታ እንደልቡ በሚያገኝበት ሁኔታ ዓሥር ዓመት የፈጀ ምርምሩን አወጣ፤ ውጤቱ የዓለም አቀፍን ታሪክ፣ በተለይም የመሀከለኛው አፍሪካን ታሪክ፣ በተለይም የኢትዮጵያን ታሪክ እንዳልነበረ አድርጎ ለወጠው፤ ባለሙያዎቹ ይቀበሉትም አይቀበሉትም።

ወደመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ ስንመጣ መጽሐፉን ከተቹት አዋቂዎች ውስጥ (እነታምራት ነገሬን ጨምሮ) ስንቱ ከላይ የተጠቀሰውን የእንግሊዝኛ መጽሐፍ አንብበዋል? ስንቱ ዜና መዋዕሎቹን አንብበዋል? ስንቱ አሁን በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ የወጣውን ፍቱሐ አል ሀበሽ አንብበዋል? እነዚህ ጥያቄዎች የተሰነዘሩት ለተቺዎቹ ብቻ አይደለም፤ በተቺዎቹ አዋቂነት ለሚደነቁ ሁሉ ነው፤ ወደድሁት፤ ወይም አልወደድሁትም ማለት መተቸት አይደለም፤ ስሜትን መግለጽ ነው፤ ስሜቱን ለመግለጽ ማንም ሰው መብት አለው፤ ነገር ግን ስሜቱን ወደአዋቂነት ለውጦ በአስመሳይነት ሲጽፍ ራሱን ከማታለሉ በላይ ሌሎች ከሱ ያነሱትን በጣም ይጎዳል፤ መክሸፍን ብሔራዊ ባህል ለማድረግ

የሚረዱት እንደዚህ ያሉ አስመሳዮች ናቸው፤[32] ልንነቃባቸውና መሰናክልነታቸውን ልንቋቋም ይገባናል።

አንድ ጊዜ በአሜሪካ በኬምብሪጅ ከተማ (ቦስተን) የታወቀው ናኦሚ ቾምስኪ የሚባለው ሊቀ ሊቃውንት በአንድ አዳራሽ ንግግር እንደሚያደርግ ማስታወቂያ ወጥቶ ነበርና ሄድሁ፤ ስደርስ ሰፈሩ በወጣት ሴቶችና ወንዶች ይሁዲዎች ይተራመሳል፤ ንግግሩን ለመስማት የመጣውን ሰው ለመመለስና ቾምስኪ ንግግሩን የሚሰማው እንዳያገኝ ለማድረግ ነበር፤ ቾምስኪ ራሱ ይሁዲ ነው፤ ሆኖም እሥራኤል በአረቦች ላይ የሚፈጽመውን ግፍ በጣም ይቃወማል፤ አሜሪካም በተለያዩ አገሮች ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እየገባ ጦርነት መቀስቀሱንም ሆነ ማፋፋሙን፣ ዴሞክራሲ እንዳይሰራጭ ማድረጉን በመጻፍና በመናገር የታወቀ የኤም አይ ቲ ዩኒቨርሲቲ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ነው፤ (የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር እንደተራ ፕሮፌሰር በአንድ የትምህርት መስክ የተከለለ አይደለም ማለት ነው፤) ለማናቸውም እነዚያ ከያለበት ተጠራርተው የመጡ ወጣቶች የሚሰማቸው አላገኙም፤ ሰውዬው በጣም የታወቀና የተከበረ ስለነበረ እነሱን ከቁም-ነገር የቆጠራቸው አልነበረም፤ አዳራሹ ጢም ብሎ ሲሞላ በመጨረሻ ወጣቶቹም ሁሉ መለፈፋቸውን ትተው ወደአዳራሹ ገቡ፤ ፕሮፌሰር ቾምስኪ ተናግሮ ሲጨርስ በጥያቄው ጊዜ አንድ ወጣት ተነሥቶ ‹ለምንድን ነው አሜሪካን እንዲህ የምትጠላው? ብሎ ጠየቀ፤ ፕሮፌሰሩ እየሳቀ ‹‹የፍቅርና የጥላቻ ነገር አልገባህም፤ አሜሪካን የምጠላ ቢሆንማ ስለስሕተቱ ምን ያስጨንቀኝ ነበር፤የምጨነቀው አሜሪካን ስለምጠላ ሳይሆን ስለምወድ ነው፤›› በማለት መለሰለት።

እኔንም የኢትዮጵያ የታሪክ ቁልቁለት የሚያሳዝነኝና የሚያስጨንቀኝ (ለታምራት ነገራ ዓይነቱ መሳለቂያ ቢሆንም) ሀገሬን ስለምወድ ነው፤ የምወድበት ምክንያት መሬት ወይም

[32] ብዙዎቹ ተቺዎች ስለኔ ትችትን ያለመቀበል ጠባይ፣ ስለትሕትና-ቢስነት፣ እኔ የምለውን ብቻ ሰሙ ባይነት ... ተግተው ይጽፋሉ፤ ይህንን የሚጽፉት እኔን ማወቃቸውን የማላውቀው ሰዎች ናቸው፤ ከራሳቸው አንጎል ጭቃ ዝቀው እኔ ላይ በመለጠፍ ያደት ይመስላቸዋል፤ ይህም አንዱ የአስመሳይነት ዝንባሌ ነው፤ የማየውቁትን ከመዘባረቅ መጽሐፉን አለመውደዳቸውን መግለጹ ብቻ ይበቃ ነበር።





ሹመት፣ ወይም ሀበት አግኝቼባታለሁ በማለት አይደለም፤ ከኔ በፊት አባቴ፣ አያቴና ቅድማያቴ ለኢትዮጵያ ቆስለዋል፤ሞተዋል፤ ኢትዮጵያን የምወድደው የወደዷት ስለሞቱላት ነው፤ ኢትዮጵያን የምወድደው ዓጽማቸው በየተራራውና በየሸለቆው የተበተነውን፣ ደማቸው በየሸንተረሩና በየወንዙ የፈሰሰውን ወገኔን ስላቀፈችልኝ ነው፤ ለእኔ ክብርን ለማውረስ የሞቱትን ሞት በማስታወስ ነው፤ እኔ ኢትዮጵያን የምወድደው ሕዝብዋን ወገኔ አድርጌ ስለምወደው ነው፤ ለራሱ ሳይጠግብ እያደረ እኔን እያበላ ስላሳደገኝ ነው፤ በዚህ ሕዝብ ልፋትና ላብ ያላገኘሁት በውስጤ ምንም ነገር የለም፤ ለእንደታምራት ነገራ ዓይነቱ እንዲህ ያለው ፍቅር፣ እንዲህ ያለው ቃል ኪዳን ሊገባው አይችልም፤ ማላገጫ የሚያደርገውም ለዚህ ነው፤[33] የሀሳቤ ድሩም ማጉም፣ የእምነቴ ድሩም ማጉም፣ የስሜቴ ድሩም ማጉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፤ የፈረንጅ ብስኩት ሳልበላ ቀርቼ አይደለም፤ መሸጦ ላለመሆን በመወሰኔ ነው እንጂ!

ለማናቸውም መጽሐፉ እንዲያገለግል የታሰበው የኢትዮጵያን የእድገት አቅጣጫ ከልባቸው በእውነት ለሚከታተሉ ሰዎች ነበር፤ ኢትዮጵያን መውደድ ተፈላጊ ቢሆንም አስፈላጊ አይደለም፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ለኢትዮጵያ ከአለን የፍቅር ስሜት ብንነሣም የመጽሐፉ ርዕስና እያንዳንዳችን ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ጉዞ ያለንን ስጋትና ጭንቀት በግልጽና በእውነተኛ የእውቀት መንገድ ለመነጋገር በር እንዲከፍት ነበር፤ ከዚህም ተነሥቶ ምናልባት አንዳንድ ወጣቶች ለምርምር የሚሆኑ የተለያዩ ጉዳዮች ያገኙበትና የበለጠ ግንዛቤ እናገኛለን በሚል ተስፋ ነበር፤ የመጽሐፉን መሠረታዊ መልእክት በሁለት አቅጣጫዎች ለማየት የሚቻል ይመስለኛል፤ አንደኛ፣ ከወደኋላችን ታሪካችንን በእውነት፣ ያለምንም ሽንገላ ስንመለከተው ምን ያሳየናል? ከየት ተነሥተን፣ በየት በኩል አድርገን አሁን ያለንበት ላይ ደረስን? የተላለፈልንን የታሪክ ቅርስ ሁሉ እናውቀዋለን ወይ? ካላወቅነው ለምን አላወቅነውም? በታሪካችን ላይ ላለን የእውቀት ጉድለት ተጠያቂው ማን ነው? ሁለተኛ፣ አሁን ከአለንበት ተነሥተን

[33] «ኢትዮጵያን አጅግ ከመውደዳቸው የተነሳ ለማቀፍ ሲንደረደሩ ሊያንቋት ከሚዳዳቸው ...» ይላል፤ ወፈፌነቱን ሊያጋብብኝ፣

የምንሄደው ወዴት ነው? አሁን ወዳለንበት የውድቀት ደረጃ ያደረሱንን ታሪካዊ ጉድለቶች ሳናውቃቸውና ሳናርማቸው የወደፊቱ ጉዞአችን አቅጣጫው ወዴት ይሆናል? የሚሉ ጥያቄዎችን ያካትታሉ።

የአገር ፍቅር ባይኖርበትም፣ ለእውቀት ወይም ለእውነት ፍለጋ የተነሣ ሰው የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያውቅ ከሆነ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ስሕተቶች በመጠቀም አንባቢንም፣ ደራሲውንም እንዲረዱ ለማድረግ ይቻል ነበር፤ የማያውቁ ሰዎች ደግሞ እስቲያውቁ ድረስ ከትችት ቢታቀቡ ብልህነት ነበር።

አንዱ ምሁር ደግሞ ፍትሐ ነገሥትንና ክብረ ነገሥትን ታመናቸዋለህ ወይ? ብሎ በኑፋቄ ይጠይቀኛል፤ በጠጣሩ የእውነት ድንጋይ ላይ ሳር ይበቅላል፤ ንጹሕ ተረትም ቢሆን የእውነት ቅንጣት አለበት፤[34] ይህንን ያለው የተሪክ ሊቅ የኋላ-ቀርና መሀይም ሕዝቦች የማስታወስ ችሎታ ከአንድ መቶ ሃምሳ ዓመታት አይበልጥም፤ ይላል፤[35] በዚህም ምክንያት እውነቱ ወደተረት እየተለወጠ ለበዙ ዘመናት ለመተላለፍ ይችላል፤ ይህ እውነት ከሆነ ተረት የሚመስሉትን የታሪካችንን ክፍሎች ሙሉ በሙሉ ከማጣጣል እያጠናን በውስጣቸው የተደበቁትን ፍሬ ነገሮች እንቅሰም፤ ከላይ የጠቀስሁትን የማስታወስ ችሎታ በጊዜ ብዛት መቀነስ በአሕመድ ኢብራሂምና (ግራኝ) በፈረሱ የሚወራውን ማስታወሱ ይበቃል፤ከዚያም በተጨማሪ ጽሑፍ ቢኖረንም እንደመሀይም የኖርን ሕዝብ ነን።

---

[34] <<On the granite of hard fact grows the moss of legend, and even pure myth contains its grains of stony reality. >> Allan Nevins, The Gateway to History, New York, 1962, p. 82.

[35] ዝኒ ከማሁ፣ ገ.83.





# ምዕራፍ ፯
# የኢትዮጵያ ህልውናና አርበኝነት



አቡነ ጴጥሮስ





ራስ አበበ አረጋይ　　　　በላይ ዘለቀ

((ስለእነዚህ አርበኞች በገጽ 273 የተጻፈውን ማንበብ ይቻላል))

## መሬትና ህልውና

በመጀመሪያ ለአዲሱ ትውልድ አንድ መሠረታዊ ሀሳብ ልናገር፤ በዝርዝር ልገባበት ሕልፈልግም፤ አንድ በኀብረተሰብ

# ምዕራፍ ፯
# የኢትዮጵያ ህልውናና አርበኝነት



አቡነ ጴጥሮስ



ራስ አበበ አረጋይ



በላይ ዘለቀ

((ስለእነዚህ አርበኞች በገጽ 273 የተጻፈውን ማንበብ ይቻላል))

## መሬትና ህልውና

በመጀመሪያ ለአዲሱ ትውልድ አንድ መሠረታዊ ሀሳብ ልናገር፤ በዝርዝር ልገባበት አልፈልግም፤ አንድ በኅብረተሰብ

ጥናት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ተማሪ ቢያጠናው ጠቃሚ ይሆናል፤ የኢትዮጵያ ህልውና ሳይከሽፍ የኖረበት መሠረታዊ ምክንያቱ ምንድን ነው? እኔ እንደሚመስለኝ በኢትዮጵያ የነበረው ባህላዊ ሥርዓት በዜጎችና በመሬት መሀከል የፈጠረው ቁርኘት የኢትዮጵያን ህልውና ጠብቋል፤ ጠላት ሲመጣ ርስት ያለው ሁሉ የመዝመት ግዴታ ነበረበት፤ እንዲያውም በወለንኮሚ አካባቢ በአደረግሁት ጥናት ብዙ ሽማግሌዎች እንደነገሩኝ ብዙ ሰዎች የመሬት ባለቤት ሳይሆኑ የቀሩት ገባርነት የሚያስከትለውን ጣጣ (ለምሳሌ ጦርነት ሲመጣ መዝመት፣ በሰላም ጊዜ ወር-ተራ እየገቡ እንደፖሊስ ያለ ሥራ መሥራት ... አራሽ፣ወይም ጭሰኛ የተወሰነውን የምርቱን ውጤት ለባለመሬቱ ካፈሰሰ በኋላ ሌላ ጣጣ የለበትም፤) በመጥላት ለባለመሬት ማረስን እየመረጡ መሆኑን ነግረውኛል::[36]

የኢትዮጵያን ማኅበረሰብ ለማወቅ ዜጋው ከመሬቱ ጋር የተያያዘበት ሰንሰለት ግልጽ መሆን አለበት፤ በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ሥርዓት ግለሰቡ፣ ማኅበራሰቡና መንግሥት የሚገናኙበትና የሚያያዙበት መሬት ነው፤ የግለሰቡ የኑሮ መሠረት፣ የማኅበረሰቡ የጋራ ኃላፊነትና የመንግሥት አስተባባሪነት በአንድ ላይ የሀገረ-መንግሥትን ህልውና ሲጠብቁ ኖረዋል ማለት ነው፤ ዓጽመ-ርስት ማለት አባቶች የሞቱለትና የሞቱበት መሬት ነው::

ከግብርና ውጭ ሌሎች አስፈላጊ ሙያዎች መኖር ስላለባቸው ማኅበረሰቡ ከኤርትራ እስከቦረና ከጋምቤላ እስከጂጂጋ ከእርሻ ውጭ ያሉ ሥራዎችን ከግል ርስት ባለመብትነት ሰረዛቸው፤ ሸማኔ፣ ቀጥቃጭ፣ ... በአጠቃላይ ባለጅ የሚባሉ ሁሉ የመሬት መብት የሌላቸው ሆነዋል፤ ይህም ማለት ለአገር ህልውና ተጠያቂዎች አይደሉም፤ በሌላ አነጋገር ማኅበረሰቡ በሥራቸው ስያሜ ሰጥቶ ከጥበቃና ከውትድርና ሥራ ውጭ ያደረጋቸው ዜጎች የተጣለባቸው ኃላፊነት በቀጥታ ከአገር ህልውና ጋር የተያያዘ

[36]Mesfin Wolde Mariam and others, Shell, Welenkomi: Socio-Economic and Nutritional Survey of a Rural Communityin the Central Highlands of Ethiopia, The World Land Use Survey, Occasional Papers, No. 11, Tonebridge England, 1971.





አይደለም፤ ይህ ጉዳይ ራሱን የቻለ መጽሐፍ የሚወጣው ነው፤ የኢትዮጵያንም ሕዝብ የፖሊቲካ መሠረት የሚያስረዳ ነው::

## ህልውናና የአርበኝነት ተጋድሎ

እስከዛሬ ድረስ የተጻፈ የአርበኞች ታሪክ በጣም ጥቂት ነው፤ ይህም በግለሰቦች፣ ተቆርቋሪ ልጆች ባላቸው አርበኞች (አብዛኛው የእሳት ልጅ አመድ እየሆነ) የታደሉት አርበኞች ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ጀኔራል ጃገማ ኬሎ፣ ሻቃ በቀለ ወያ፣ በላይ ዘለቀ፣... አንዳንዶች ያልተጣራና ያልተዘመደ ቢሆንም ዋናውን ነገር አቅርበውልናል፤ ከዚያም አልፎ ገሪማ ታፈረ፣ ጳውሎስ ኞኞ፣ ተድላ ዘዮሐንስ ትንሽ ሰፋ ያለ የአርበኞች ታሪክ አበርክተዋል፤ እስካሁን በተለያዩ ግለሰቦች የተጻፈው ሁሉ ተዳምሮ የአምስቱን ዓመታት የመረረ የአርበኞች ትግል አያክልም፤ የአርበኞች ታሪክ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ መካነ ጥናት በዝርዝር በተቀናጀና በተቻለ መጠን የሚመለከታቸውን ሰዎች ሁሉ በአሳተፈ ሁኔታ የተዘጋጀ መሆን ነበረበት፤ የአገር ጉዳይ ስለሆነ በአገር ደረጃ መሠራት ይገባው ነበር፤ የአርበኞችን ስም ዝርዝር፣ የሞቱትን ስም ዝርዝር፣ የቆሰሉትን ስም ዝርዝር፣ የደረሱበት ያልታወቁትን ስም ዝርዝር ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ተገቢ ይሆን ነበር፤ ስደተኞችና ባንዳዎች፣ ወይም ልጆቻቸው በነገሡበት ለአርበኞች የሚያስብ አልተገኘም፤ በእውነት ከሆነ የአርበኞች ታሪክ ጥቅሙ ለአርበኞቹ ሳይሆን ለአገርና ለተከታታይ ትውልዶች ነው::

አርበኝነት የሚፈጠርበት ጊዜ የሕዝቡ ኩራትና ክብር ሲገፈፍ፣ ጥላ-ከለላ የሚሆን መሪ ሲጠፋ፣ ሕጋዊ ሥርዓትን የሚያስከብር መንግሥት ሳይኖር ነው፤ በዚህ ጊዜ ልበ-ሙሉ የሆኑና መንፈሳዊ ወኔ ያላቸው ሰዎች ተሰባስበው የማኅበረሰቡ ህልውና የሚጠበቅበትንና ሚከበርበትን መንገድ ይቀይሳሉ፤ አርበኝነት የዚህ ዓላማ ጉልበት ነው፤ በየቦታው የሚገኙ አርበኞች አለቆቻቸውን እየመረጡ በዩአለቃቸው እየሆኑ ተከፋፍለው በደፈጣ ውጊያ የጠላቱን የበለጠ የሰው ኃይል፣ በጣም

የበለጠ መሣሪያና መንጓዣ እያሰናከሉና እየማረኩም ራሳቸውን ሲያጠነክሩ ጠላትን የሚያዳክሙበት ዘዴ ነው፤ አርበኛ ማለት የቀድሞዎቹን አባቶቹን ታሪክ የሚያከብር፣ ራሱን የሚያከብር፣ ወገኑን የሚያከብር፣ አገሩን የሚወድ ዜጋ ነው።

በእስያ ጃፓን ለምዕራቡ አገር ስጋት የሆነችውን ያህል ባይሆንም ኢትዮጵያ ከአድዋ ጦርነት ወዲህ ምዕራባውያንን ማስደንገጥዋ አልቀረም፤ አሁንም በጃፓን ላይ የደረሰውን ያህል ባይሆንም ኢትዮጵያ ከምዕራባውያን የጭካኔ በትር አላመለጠችም፤ ጃፓን አቶሚክ ቦምብ ተሞከረባት፤ ኢትዮጵያም የመርዝ ቦምብ በያይነቱ ተሞከረባት፤ ከአውሮጵላንና ከታንክ ጋር መርዝ ሳይቀር የተለያዩ ዘመናዊ መሣሪያዎችን የታጠቀው የፋሺስት ኢጣልያ ጦር ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ታሪኩ አጋጥሞት የማያውቀውን የጦር ሜዳ ስቃይ አሳየው፤ አዋርዶ አሸነፈው፤ የድፍድፍ ኩራት ውሀ እስቲገባበት እንዲሉ ቆሞ የቀረ ኋላ-ቀር ሕዝብ ኩራቱንና ክብሩን በቀላሉ እንደሚገፈፍ ማረጋገጫ ሆነች፤ የኢጣልያ ዓላማ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማሸነፍ ብቻ አልነበረም፤ በኋላ መለስ ዜናዊ ይለው እንደነበረ አከርካሪቱን ሰባብሮ ሁለተኛ እንዳያንሰራራ ለማድረግም ነበር፤ ከዘመናዊ መሣሪያው --- ከመድፍና መትረየሱ፣ ከታንኩና ከመርዝ ቦምቡ፣ ከአውሮጵላኑም ጋር ኢጣልያ ያሰለፈችው የኢጣልያኖች የሠለጠነ የጦር ሠራዊት ከከዱ ወገኖቻችን (ከባንዶች) ጋር ተዳምረው ቁጥራቸው ከፍተኛ ነበር፤ በጉልበት ሲመዘን ምንም ዳዊት ባያሸንፍም የዳዊትና የጎልያድ ያህል ልዩነት ነበረ።

አቶ ተድላ ዘዮሐንስ *የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ኢጣልያ በኢትዮጵያ፣ ከወልወል እስከጎንደር፣ ግንቦት 1927- ኅዳር 1934 ዓ.ም.* በሚል ርዕስ ያዘጋጀውና በ2004 ዓ.ም የታተመው መጽሐፍ ስለአርበኝነት ብዙ ይናገራል፤ በመጀመሪያ መጽሐፉ በ2004 ዓ.ም. ከስድሳ አንድ ዓመታት በኋላ መታተሙ አንድ ነገር ይናገራል፤ አቶ ተድላ ራሱ አርበኛ ነበር፤ ዕድለኛ ሆኖ በደኅና የኃላፊነት ሥራዎች ላይ ቆይቶ የዘመናዊ ትምህርት ዕድል ቢያገኝም ይህንን ዝርዝር የአርበኝነት ተጋድሎ የያዘ መጽሐፍ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አላሳተመውም፤ ለብዙ ዓመታት





በትምህርት ሚኒስቴር ሲሠራ ይህ መጽሐፍ ለተማሪዎች መጥቀሙን ሳይረዳ ቀርቶ አይመስለኝም፤ ለማናቸውም አሁን ያቀረበልንን እንየው፤ እኔ ገና ተማሪ በነበርሁበት ጊዜ አቶ ተድላ በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ከሹሞቹ አንዱ ነበር፤ በዚያን ዘመን ይህንን መጽሐፍ ለገበያ ለማቅረብ ዕድሉን ቢያገኝም ሥራውን ያጣ ነበር፤ ስለዚህም ስለአርበኞች ሮሮና መከራ የሚያውቀውን ሁሉ ቀብሮ ሳይጠፋበት ወደእኛ አደረሰልን፤ ለታሪክ ግብአት የሚሆን ነገር ዘግይቶም ቢሆን ስላበረከተ አመሰግነዋለሁ፤ ስንቶች ሌሎች አርበኞች ስንቱን የቅሬታና የጸጸት መረጃዎቻቸውን ሳያቀብሉን አልፈዋል!

አቶ ተድላ ዘዮሐንስ እንደሚገልጸው በኢጣልያ ወረራ ጊዜ የሸዋ (የቡልጋ) የገጠር ነዋሪዎች እየተሰበሰቡ የጎበዝ አለቃ እየመረጡ እንሸፍት ወይስ ኢጣልያንን እንቀበል በሚለው ዓላማ ላይ በደንብ ከተከራከሩ በኋላ አብዛኛው ሕዝብ እንሸፍት የሚለውን በመደገፉ፣ ከዚህ ውጭ እንሆናለን ያሉትን በመጀመሪያ ከማኅበራዊ ኑሮ በማስወጣት፣ ከዚያም የባሰ እርምጃ በመውሰድ አስገዳጅ አድርገውታል፤ የተለያዩ ሹመቶችንም በመስጠት ሥርዓትን ፈጥረዋል፤ በፈቃዳቸው ከዚህ የሹም-ሽር ሥርዓት ውጭ ሆነው የቀሩት ኃይለ ማርያም ማሞ ብቻ ናቸው፤ ወደአርበኝነት የገቡት በእኩልነት ከጠላት ጋር ለመዋጋት ነው እንጂ ለመሹዋሹዋም አይደለም በማለት አልተቀበሉትም፤ ነገር ግን ባላመባራስ የነበሩት ራስ አበበ አረጋይ የተባሉት በአርበኞችና በጊዜው ንጉሠ ነገሥት ተብለው ተሹመው ከነበሩት ከልጅ ኢያሱ ልጅ ነው።[37]

አርበኝነት ዓላማውና ስሙ የተለወጠ ሽፍትነት ነው፤ ሽፍትነት ሁለት ዓይነት ነው፤ አንዱ የወሮበሎችና የቀማኞች መኖሪያ ሥራ ነው፤ መንገደኞችንና ነጋዴዎችን በወንዝ መሻገሪያ ላይ እየጠበቁ መዝረፍ የወረበላ ሽፍቶች ተግባር ነው፤ ሁለተኛው የመሸፈት ዓይነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም መብቱንና ክብሩን ለማስጠበቅ ለሚፈልገው ክፍል የተለመደ ባህላዊ መሣሪያ ነው፤

[37] ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፡- ኢጣልያ በኢትዮጵያ፣ ከወልወል እስከጎንደር፣ ግንቦት 1927-ኅዳር 1934 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ 2004 ዓ.ም.

ያኮረፈ ‹የጨዋ ልጅ› ሁሉ ያለውን ይዞ ጫካ ይገባል፤ በዚያም ሆኖ ለተሰማው ውርደት ምክንያት የሆነውን ሥልጣን እየተጋፋና እየቆነጠጠ ይቆያል፤ አርበኝነት ደግሞ የግል መብት በመደፈሩና የግል ክብር በመዋረዱ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በአገርና በወገን ላይ በመጣ ውርደት ላይ ዓምጾ መነሣት ነው፤ ለውርደቱ ምክንያት የሆነውን ኃይል በእምቢተኛነት መቋቋምና መዋጋት ነው፡፡

የኩራትና የክብር ጉዳይ በሊሬ ተመዘነ፤ በሰንጠረጆቹ ላይ የተዘረዘሩትና ሌሎችም በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በኢጣልያ ጫማ ስር ወደቁ፤ ነገር ግን በዚህም ክፉ የፈተና ጊዜም ቢሆን ኩራታቸውንና ክብራቸውን በሊሬ አንሸጥም ያሉ ጀግኖች ልጆችም ኢትዮጵያ ነበሩላት፤ በሰማይ ቢመጣ፣ እሳት ቢወረውር ሳይበገሩ በቆራጥነት እስከመጨረሻው የተፋለሙት፣ ኮርተው የሚያኮሩ፣ ተከብረው የሚያስከብሩ ልጆች ነበሯት፤ የአርበኞች ጉዳይ ገና የሚገባውን ትኩረት አግኝቶ አልተጠናም፤ ዱሮ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያን አርበኞች ስታጠና የነበረች ሰሎሜ ገብረ እግዚአብሔር የምትባል አስተማሪ ነበረች፤ ስደት በልቷት ድምጽዋ ጠፋ፤ በብዙ ምክንያቶች ኢጣልያኖች የኢትዮጵያን አርበኞች ቁጥር ማሳነስ ዝንባሌ ቢኖራቸውም ሰንጠረጅ 1 አንድ ዓይነት ምልክት ስለሚሆን ጠቃሚ ነው፡፡

## የፋሺስት ኢጣልያ ወረራና የኢትዮጵያ አርበኞች

በሰንጠረጅ 1 የሚታየውን ቁጥር ሙሉ በሙሉ ለመቀበል የሚያስቸግር ቢሆንም ብዙም ከእውነት የማይርቅ መሆኑን መጠራጠር አይቻልም፤ ኢጣልያኖቹ አርበኞች አይለውባቸው የሚገኙባቸውን ቦታዎች ያውቃሉ፤ የወታደሩም ሆነ የሰለማዊው ደኅንነት ድርጅት ከተሟላ መሣሪያ ጋር አላቸው፤ በዚያ ላይ ታላላቅ ባንዶችና ጭፍሮቻቸው ለማሳበቅና ፍርፋሪ ለማግኘት ይወዳደራሉ፤ ስለዚህ ቁጥሮቹን እንደአመላካች አድርገን ብንወስዳቸው ለወደፊቱ ትምህርት ይሰጡ ይሆናል፡፡





መጀመሪያ በቁጥሮቹ ላይ እንነጋገር፤ በጠቅላላ በኢትዮጵያ የተሰማሩ አርበኞች አንድ መቶ ሃያ ሦስት ሺህ ግድም ብቻ ነበሩ? እአአ በ1936 በኢጣልያኖቹ ግምት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ወደሰባት ሚልዮን ግድም ነበረ፤ እንግዲህ ከዚህ ውስጥ ሴቶችን፣ ልጆችን፣ ደካሞችን ካስወጣን በኋላ የመዋጋት አቅም አላቸው የሚባሉ አንድ ሚልዮን ያህል ሰዎች ነበሩ ብዬ እገምታለሁ፤ አሁንም በኢጣልያኖቹ ግምት 123350 (አንድ መቶ ሃያ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሃምሳ) አርበኞች ነበሩ፤ ይህም የመዋጋት አቅም ካላቸው ሰዎች ከአሥራ ሁለት ከመቶ በላይ ናቸው ማለት ነው፤ ቁጥሩ ትንሽ ቢመስልም ከሕዝቡ ቁጥር ጋር ሲታይ መጠኑ ትንሽ የሚባል አይደለም፤ ያውም በዱር በገደሉና በበረሀው እየተተዘዋወሩ ለሚዋጉ አርበኞች ከፍ ያለ ቁጥር ነው፡፡

የአርበኞቹ ስርጭትና በሦስት ዓመታት ውስጥ ያሳየው ለውጥ ብዙ ሊያነጋግር የሚችል ነው፤ በመጀመሪያ ዋናው ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ ጎጃም ዋናው ያርበኝነት ቦታ መሆኑ ነው፤ እአአ በ1938፣ ከጦርነቱ ሦስት ዓመታት በኋላ ማለት ነው፣ ከጠቅላላው የኢትዮጵያ አርበኞች ውስጥ በጎጃም የነበሩት ሰማንያ ከመቶው ይሆናሉ፤ (ሰንጠረጅ 2)፤ የጎንደር ድርሻ አሥራ ሁለት ከመቶ ሲሆን፣ የኦሮሞና ሲዳሞ ስድስት ከመቶ፣ ሸዋ ሁለት ከመቶ ብቻ ነበር፡፡

ስለዚህ በመጀመሪያውም ይሁን በመጨረሻው የኢጣልያ የወረራ ዘመኖች ጎጃም በአርበኝነት ቅድሚያውን ስፍራ ይይዛል፤ በዚህ ላይ ብዙ ጥርጣሬዎች፣ ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንደሚነሡ አልጠራጠርም፤ ወደትክክለኛውና ወደእውነቱ ለመጠጋት ጥርጣሬዎችና የተለያዩ አስተያየቶች ጠቃሚ ናቸው፤ እንዲያውም ጉዳዩ ወደነበላይ ዘለቀ ሞትና ወደጎጃም ለብዙ ዓመታት መዳፈን ላይ የሚያመራ ሊሆን ይችላል፡፡



አርበኞች በልበ ሙሉነትና በኩራት ሲፎከሩ

የሰንጠረጅ አንድን አሐዞች መጠራጠር እንችል ይሆናል፤ ሆኖም ኢጣልያኖች በየት በየት የኢትዮጵያ ክፍሎች ችግር እንዳጋጠማቸው ያውቁ ነበር ብለን ለመቀበል አያዳግትም፤ የቁጥሮቹ ትክክለኛነት እንደሚያጠራጥር አያከራክርም፤ እፍኝ የማይሞሉ ወንበዴዎች የሚለውን አባባል በደርግ ዘመን ሰምተናል፤ ሆኖም አመልካችነታቸውን ብንቀበል አንዳንድ ነገር ለመጠየቅና ለማጣራትም መንገድ ይከፍታል፤ ለምሳሌ በጎጃም ውስጥ የሚታየው የአርበኞች ቁጥር ብዛትና በትግራይ ምንም አለመኖሩ ጥያቄዎችን የሚያስነሡ ናቸው።

እንደዚያም ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኤርትራ ኢጣልያንን ከድተው ከወገናቸው ጋር ከተደባለቁት ጋር በኢጣልያኖች ላይ ብዙ ጉዳት አድርሷል፤ በዚህም ምክንያት ፋሺስት ኢጣልያን እያሰጋትና እያስፈራት በመሄዱ ትጥቅ ማስፈታትን በሰፊው ተያያዘችው፤ ሆኖም ከመለመለቻቸውና ከአሰለፈቻቸው ባንዶች ውስጥም አንዳንዶቹን ኢትዮጵያዊነት እየቀሰቀሳቸው ለወገኖቻቸው መሣሪያ የሚያቀብሉ ነበሩ፤ የኢጣልያ ጦር በመጀመሪያ የተማመነው በኢጣልያን ወታደሮች ላይ ነበር፤ ባንዶችንም እንደልብ ለመመልመል አልተመቸም ነበር ይሆናል፤ ከሰንጠረጁ እንደሚታየው በአራተኛው ዓመት ላይ የኢጣልያ ወታደሮች ቁጥር





በጣም አራት ጊዜ ያህል ሲቀንስ በአንጻሩ የባንዳዎቹ ቁጥር በእጥፍ አደገ።

**ሰንጠረጅ 1**
**በኢጣልያኖች ግምት የአርበኞች ስርጭት**
**እአአ 1937-1938**

| እአአ | ላስታ | በጌም | ጎጃም | ሸዋ | አሮ-ሲዳ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1937* | 4500 | | 14000 | 7000 | 400 | 25900 |
| 1937* | 500 | 5000 | 14600 | 2400 | 400 | 22900 |
| 1937* | 150 | 1800 | 14600 | 2500 | 3000 | 22050 |
| 1937* | - | 2000 | 20000 | 3000 | 2500 | 27500 |
| 1938* | - | 3000 | 20000 | 500 | 1500 | 25000 |
| ድምር | 5150 | 11800 | 83200 | 15400 | 7800 | 123350 |

ምንጭ፡ Alberto Sbacchi[38]
*የተለያዩ ወሮችን እንጂ ዓመቶችን አያመለክቱም።

በአልቤርቶ ስባኪ መረጃ መሠረት የተጎዱ ኢጣልያኖች እአአ ከ1935 እስከ1940 ድረስ 188000 (አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ) ይሆናሉ፤ በዚያው ጊዜ ውስጥ የሞቱ 16212 (አሥራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ አሥራ ሁለት) ነበሩ፤[39] ለኢጣልያ ይህ ቀላል የሚባል ጉዳት አልነበረም፤ የኢጣልያ አገዛዝ በአምስት ዓመታት ውስጥ ተደላድሎ ለመግዛት እንዳልቻለ ያሳያል።

**ሰንጠረጅ 2 (በሰንጠረጅ 1 ላይ የተመሠረተ)**
**በሰንጠረጅ 1 ያለው የአርበኞች ስርጭት በመቶኛ**

| እአአ | ላስታ | ጎንደር | ጎጃም | ሸዋ | አሮ-ሲዳ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1937 | | | | | | |
| 1937 | | | | | | |
| 1937 | | | | | | |
| 1937 | | | | | | |
| 1938 | | | | | | |
| አማካይ | | | | | | |

[38] ዝኒ ከማሁ ገ. 177
[39] አለቤርቶ ስባኪ (2)፤ ገ.99.



አርበኞች በልበ ሙሉነትና በኩራት ሲፎክሩ

የስንጠረጅ አንድን አሐዞች መጠራጠር እንችል ይሆናል፤ ሆኖም ኢጣልያኖች በየት በየት የኢትዮጵያ ክፍሎች ችግር እንዳጋጠማቸው ያውቁ ነበር ብለን ለመቀበል አያዳግትም፤ የቁጥሮቹ ትክክለኛነት እንደሚያጠራጥር አያከራክርም፤ እፍኝ የማይሞሉ ወንበዴዎች የሚለውን አባባል በደርግ ዘመን ሰምተናል፤ ሆኖም አመልካችነታቸውን ብንቀበል አንዳንድ ነገር ለመጠየቅና ለማጣራትም መንገድ ይከፍታል፤ ለምሳሌ በጎጃም ውስጥ የሚታየው የአርበኞች ቁጥር ብዛትና በትግራይ ምንም አለመኖሩ ጥያቄዎችን የሚያስነሡ ናቸው።


እንደዚያም ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኤርትራ ኢጣልያንን ከድተው ከወገናቸው ጋር ከተደባለቁት ጋር በኢጣልያኖች ላይ ብዙ ጉዳት አድርሷል፤ በዚህም ምክንያት ፋሺስት ኢጣልያን እያስጋትና እያስፈራት በመሄዱ ትጥቅ ማስፈታትን በሰፊው ተያያዘችው፤ ሆኖም ከመለመለቻቸውና ከአሰለፈቻቸው ባንዶች ውስጥም አንዳንዶቹን ኢትዮጵያዊነት እየቀሰቀሳቸው ለወገኖቻቸው መሣሪያ የሚያቀብሉ ነበሩ፤ የኢጣልያ ጦር በመጀመሪያ የተማመነው በኢጣልያን ወታደሮች ላይ ነበር፤ ባንዶችንም እንደልብ ለመመልመል አልተመቸም ነበር ይሆናል፤ ከስንጠረጁ እንደሚታየው በአራተኛው ዓመት ላይ የኢጣልያ ወታደሮች ቁጥር

የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን በሙሉ ቁጥጥሩ ስር ለማስገባት ኃይሉን በሙሉ ይጠቀም ነበር፤ ይህንን በሰንጠረጅ 2 እናያለን፤ እአአ በ1936 ኢጣልያውያን ወታደሮች የጦሩ ከመቶ ሰባ ሰባት ያህሉ ነበሩ፤ በዚያው ዓመት የባንዳዎቹ ድርሻ ከመቶው ሃያ ሦስት ግድም ብቻ ነበረ፤ እአአ በ1940 ደሞ የኢጣልያኖቹ ድርሻ በጣም ወርዶ ከመቶ ሠላሳ ግድም ደረሰ፣ የባንዳቹ ወደሰባ አንድ ግድም ከፍ ብሎ ነበር።

**ሰንጠረጅ 2**
**የኢጣልያ የጦር ኃይል**

| እአአ. | ኢጣልያ | ባንዳዎች | ድምር |
|---|---|---|---|
| 1936 | 358000 | 108000 | 466000 |
| 1937 | 157000 | 60000 | 237000 |
| 1938-39 | 120000 | 160000 | 280000 |
| 1940 | 91000 | 200000 | 291000 |

ምንጭ አልቤርቶ ስባኪ[40]




የኢጣልያን ወታደሮች

[40] ገዘኢ ከማህ ገ. 178





የባንዳዎቹ ቁጥር በመቶ ሰማንያ አምስት ከመቶ በላይ ሲጨምር የኢጣልያናውያኑ ቁጥር ከሦስት መቶ ዘጠና ሦስት ከመቶ በላይ ቀነሰ፤ ይህ የሚያሳየው ባንዳ ለመሆን የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን እንደበረከቱ ነው፤ ምክንያቱ ምንድን ነው? ምናልባትም የኢጣልያ ጦር በአውሮፓ ለነበረው ጦርነት የበለጠ ይፈለግ ነበር ይሆናል፤ ምናልባት በኢጣልያ ጦር ላይ ጉዳት በዝቶ ይሆናል።

በአልቤርቶ ስባኪ መረጃ መሠረት የተጎዱ ኢጣልያኖች እአአ ከ1935 እስከ1940 ድረስ 188000 (አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ) ይሆናሉ፤ በዚያው ጊዜ ውስጥ የሞቱ 16212 (አሥራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ አሥራ ሁለት) ነበሩ፤[41] ለኢጣልያ ይህ ቀላል የሚባል ጉዳት አልነበረም፤ የኢጣልያ አገዛዝ በአምስት ዓመታት ውስጥ ተደላድሎ ለመግዛት እንዳልቻለ ያሳያል፡

በአንጻሩ ደግሞ የአርበኞች ቁጥርም እየቀነሰ ነበር፤ ይህንን በሁለት መንገድ ማረጋገጥ ይቻላል፤ አንደኛ ከሰንጠረጅ 1 እንደምናየው እአአ በ1937 መጀመሪያ ላይ 25900 የነበረው ወደ25000 ወርዶአል፤ ሁለተኛ በሰንጠረጅ 3 እንደሚታየው ትጥቅ ማስፈታቱ የኢጣልያን እያየለ መሄድ ያሳያል፤ በአምስት ዓመታት ውስጥ ኢጣልያ ወደአራት መቶ ሺህ የሚጠጋ ጠመንጃ ሰብስቦአል፤ መረጃው የለም እንጂ በውስጥ አርበኞች በኩል ከኢጣልያ ጦር ወደአርበኞች የሚሳክ ጠመንጃም ነበረ፤ የውስጥ አርበኞች የሚባሉት ትልቁ አስተዋጽኦ ጠመንጃና ጥይት ከባንዳዎቹ እየገዙ ለአርበኞች መላክ ነበር።

ትጥቅ መፍታት የመክሸፍ ምልክት ነው፤ ትጥቅ ማስፈታት በኢጣልያ ወረራ ጊዜ የተጀመረ ይመስለኛል፤ ከዚያ በኋላ በደርግና በወያኔ አገዛዝ ዘመኖች ቀጥሎ እየተሠራበት ነው፤ ይህም ጉዳይ ብዙ ውይይትና ጥናት የሚያስፈልገው ነው፤ የኢትዮጵያ ህልውና ከመክሸፍ የዳነበት ዋናው ምክንያት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ራሱን ለመጠበቅ የራሱ ኃላፊነት መሆኑና ይህንን ተከትሎም አገሩን መጠበቅ ራስን,ከመጠበቅ ጋር የተያያዘ

[41] አለቤርቶ ስባኪ (2)፣ ገ.99.


የኢጣልያ ጦር ኢትዮጵያን በሙሉ ቁጥጥሩ ስር ለማስገባት ኃይሉን በሙሉ ይጠቀም ነበር፤ ይህንን በሰንጠረጅ 2 እናያለን፤ እአአ በ1936 ኢጣልያውያን ወታደሮች የጦሩ ከመቶ ሰባ ሰባት ያህሉ ነበሩ፤ በዚያው ዓመት የባነወዶቹ ድርሻ ከመቶው ሃያ ሦስት ግድም ብቻ ነበረ፤ እአአ በ1940 ደሞ የኢጣልያኖቹ ድርሻ በጣም ወርዶ ከመቶ ሠላሳ ግድም ደርሶ፣ የባንዶቹ ወደሰባ አንድ ግድም ከፍ ብሎ ነበር።

ሰንጠረጅ 2

የኢጣልያ የጦር ኃይል

| እአአ. | ኢጣልያ | ባንዳዎች | ድምር |
|---|---|---|---|
| 1936 | 358000 | 108000 | 466000 |
| 1937 | 157000 | 60000 | 237000 |
| 1938-39 | 120000 | 160000 | 280000 |
| 1940 | 91000 | 200000 | 291000 |

ምንጭ አልቤርቶ ስባኪ.[40]




የኢጣሰያን ወታደሮች

[40] ዝኒ ከማሁ ገ. 178



የባንዳዎቹ ቁጥር
ሲጨምር የኢጣልያናው
ከመቶ በላይ ቀነሰ፤ ይ
ኢትዮጵያውያን እንደበ
ምናልባትም የኢጣልያ
ይፈለግ ነበር ይሆናል፤
ይሆናል።

በአልቤርቶ ስባኪ
እአአ ከ1935 አስከ194
ስምንት ሺ.ህ) ይሆናሉ፡
(አሥራ ስድስት ሺ.ህ
ለኢጣልያ ይህ ቀላል የ
በአምስት ዓመታት
ያሳያል፡

በአንጻሩ ደግሞ የ
በሁለት መንገድ ማረ
እንደምናየው እአአ በ1
ወደ25000 ወርዶአል፤
ትጥቅ ማስፈታቱ የኢጣ
ዓመታት ውስጥ ኢጣል
ሰብስቦአል፤ መረጃው
ከኢጣልያ ጦር ወደአር
አርበኞች የሚባሉት
ከባንዳዎቹ እየገዙ ለአር

ትጥቅ መፍታት
ማስፈታት በኢጣልያ
በኋላ በደርግና በወያኔ
ይህም ጉዳይ ብዙ
የኢትዮጵያ ህልውና
እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ
ይህንን ተከትሎም አገሩ

[41] አለቤርቶ ስባኪ. (2)፣ ገ.99

መሆኑ ነበር፤ በኢጣልያ፣ በደርግና በወያኔ የአገዛዝ ዘመኖች እያንዳንዱ ዜጋ ራሱን የመጠበቅ ኃላፊነቱን ተነጠቀ፤ በዚህም ምክንያት ትጥቅ ማስፈታት የእነዚህ ሥርዓቶች ዋና ተግባር ሆነ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትጥቅ ማስፈታት የአገዛዝ ሥርዓቶቹን ህልውና ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ የአገዛዝ ሥርዓቶቹ ህልውና ከኢትዮጵያ ህልውና የተለየ፤ የሚበልጥና የሚቀድም ሆኖ መገመቱን ያረጋግጣል።

ሰንጠረጅ 3

ከኢትዮጵዮውያን የተቀማ መሣሪያ በቁጥር[42]

| ዓ.ም. | ጠመንጃ | ሽጉጥ | መትረየስ | መድፍ |
|---|---|---|---|---|
| 1935 | 25441 | 107 | 348 | 150 |
| 1936 | 93401 | 1113 | 263 | 5 |
| 1937 | 179856 | 374 | 402 | 4 |
| 1938 | 62080 | 419 | 133 | -- |
| 1939 | 18080 | 185 | 72 | -- |
| 1940 | 4723 | 61 | 21 | -- |
| ድምር | 383359 | 2259 | 1238 | 169 |

ምንጭ አልቤርቶ ስባኪ

በኢጣልያ የወረራ ዘመኖች በአራት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደአራት መቶ ሺህ የሚጠጉ ጠመንጃዎችን ለጠላት ሲያስረክብ ምን ያህል በመዳከም ላይ እንደነበረ የሚያሳይ ነው፤ በሦስተኛው የወረራ ዓመት ላይ በጣም ብዙ ሰው ትጥቅ ፈቶ ነበር፤ ጠላት የተረከበው የጠመንጃ ቁጥር ከአርበኞች ቁጥር ከሦስት እጥፍ በላይ መሆኑ የሚናገረው አያጣም።

የአርበኞቹ ተጋድሎ ያስገኘው ክብር

የኢትዮጵያ ስም ገናናነትና የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ለአፍሪካ ሕዝቦች ነጻነት በብዙ በኩል ያበረከተው ከፍተኛ

[42] Alberto Sbacchi, ...(ገ. 180) ይኸው መጽሐፍ በአምሻው ዓለማየሁ፣ ኢትዮጵያ፡ በኢጣልያ ፋሺስቶች የወረራ ዓመታት (1928-1933)፣ 1995 አዲስ አበባ ታትሟል፤





አስተዋጽኦ፣ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የብቻቸው ቁርጠኛነት የአፍሪካ አንድነትን ለመመሥረት ያስቻለ መሆኑን በራስ መተማመን ላልተፈጠረባቸው፣ ኩራትና ክብር ከውስጣቸው ተራግፎ ለቀለላቸው የወያኔ መሪዎች የበለጠ የሚያቀላቸው መስሎ ስለታያቸው ለሌላና ለማይገባው ሰው በአዲስ አበባ ውስጥ ሐውልት እንዲሠራ አደረጉ፤ ደርግ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ባለሥልጣኖች ሁሉ ስለጨረሳቸው ትክክለኛው መረጃ በይፋና በሙሉ ባይወጣም፣ ከአልጄርያ እስከደቡብ አፍሪካ፣ በኬንያና በዚምባብዌ ለአፍሪካውያን የነጻነት ትግል ኢትዮጵያ ያበረከተችው ገና በሙሉ ለታሪክ ማኅደር የደረሰ አይመስለኝም፤ የመክሸፍ አባዜ ስለተጠናወተን ቀደም ያለው የሠራውን በኋላ የሚመጣው ያፈርሰዋል ወይም ይደብቀዋል፤ ታሪክን የአገርና የሕዝብ አድርጎ በመመልከት ፋንታ የግል በማድረግ ታሪክ ያስባሕርዩ እንዲያጥርና በሰው ዕድሜ እንዲለካ ይደረጋል፤ ታሪክ የሚከሸፍበት አንዱ መንገድ ይህ ነው።

እዚህ ላይ ሌላ ዋናና በጣም ትልቅ ገና ወጌሻ ያልተገኘለት የታሪክ ስብራት ያጋጥመናል፤ እስከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ዐውስጥ ብቸኛና ዝነኛ አገር ነበረች፤ በደርግ ዘመን በቀይና በነጭ ሽብር አረመኔያዊ ጭፍጨፋ የኢትዮጵያ ታሪካዊ የመንፈሳዊ ቅርስ ክምችት ተናደ፤ ይህ ከመክሸፍ የባሰ መራቆት ነው፤ በእኔ ግምት በደርግና በወያኔ የአገዛዝ ዘመኖች የተፈጸመው መክሸፍ በፋሺስት ኢጣልያ አሸናፊነት ከተፈጸመው መክሸፍ ጋር ሲወዳደር የባሰ ነው፤ እንዴት? መጀመሪያ ተከታታይነቱን ልብ እንበል፤ እንደኛ ፋሺስት ኢጣልያ ለብዙ ሺህ ዓመታት በውጭ ኃይል ሳይበገር የኖረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ፋሺስት ኢጣልያ ድል በማድረግ የዘመኑን አዲስ የእድገት ከፍታ አሳየች፤ በአንጻሩም ኢትዮጵያ ያለችበትን በጣም ዝቅተኛና ቆሞ-ቀር ደረጃ በተግባር አስመሰከረች፤ ይህ አዲስ እውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የነበረውን አልበገር-ባይነት ከኩራቱና ከነክብሩ ገፈፈው፤ የመንፈስ ኃይሉ ደቀቀ፤ አንገቱን ደፋ።

ሁለተኛ የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ በፋሺስት ኢጣልያ መሸነፉን እንደተቀበለ ቀጠለ፤ የዘመኑ ወጣቶች በውሸት «ድል

አድራጊው ንጉሣችን›› እያልን እንድንዘምርና ሸሽተው ከሄዱበት ከስደት የተመለሱትን ንጉሠ ነገሥት ማወደስ ጀመርን፤ ቆም ብሎ ያሰበና ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልሶችን ለመስጠት የሞከረ ሰው አልነበም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን ተሸነፈ? ዓለም በሰማይ ላይ መሄድ እስኪጀምር ድረስ እኛ የት ነበርን? ኢትዮጵያ እንደአገር መንና ገዳም ገብታ ነበር? የኢጣልያን ኃያልነትና የእኛን ደካማነት በማያጠራጥር መንገድ ከተረዳንና ልካችንን ካየን በኋላ ወደነበርንበት መመለሳችን ምንን ያሳያል?

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኩራትና ክብር ፈጽሞ ደብዛው እንዳይጠፋ በዱር በገደሉ እየተሧሧሩ ኢትዮጵያዊ አልበገር-ባይነትን ለፋሺስት ኢጣልያና ለዓለም ያሳዩትን አርበኞችን ከስደተኞችና ከባንዶች በታች በማድረግ ፋሺስት ኢጣልያ ያደቀቀችውን የኢትዮጵያውያንን የመንፈስ ኃይል የስደተኛው የአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ይበልጥ አደቀቀው፤ ይህ የእኔና ተከታታይ ትውልዶች ያለፍንበት የከሸፈ ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፋሺስት ኢጣልያ ድል አድራጊነት ቀንበር ገና ያልተላቀቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ስደተኞችና ባንዶች የኢትዮጵያን ሕዝብ የገዙበት ዘመን ነው፡

## የላዩ ታች፣ የታቹ ላይ

ልብ በሉ፤ የፋሺስት ኢጣልያ አገዛዝ በስደተኞችና በባንዶች አገዛዝ ተተካ፤ ይህ አገዛዝ የማርክስና የሌኒን ፍልስፍ ተከታዮች ባላንጣዎች ሆኑበት፤ የማርክሳዊ-ሌኒናዊ ፍልስፍና ወይም ሃይማኖት የዓለምን ወጣቶች ያስከረበት ዘመን ነበር፤ የኢትዮጵያ ወጣቶችም ለወጉ ብቻ የሃይማኖቱ ተከታዮች መስለው እርስበርሳቸው የተጫረሱት ዘመን መጣ፤ ኢሕአፓ፣ መኤሶን፣ ሕወሓት-ወያኔ፣ ሻቢያ፣ በኋላም ደርግ-ኢሠፓ --- ሁሉም ሃይማኖታቸው ማርክሳዊ-ሌኒናዊነት ነው፤ ለጭካኔና ለመገዳደል ሙሉ ፈቃድ የሚሰጥ ይህ ሃይማኖት ብቻ ነበር፤ ለመገዳደል ሁሉም ተጠቀሙበት፤ ኢትዮጵያም በሺህ የሚቆጠሩ ያሳደገቻቸውን ልጆች አጣች፤ ከሞት የተረፉት የአብዮት መሪዎች ሁሉ ዛሬ በአውሮፖና በአሜሪካ ቤት መሥርተው ይነግዳሉ፤ የሞቱት ተጎዱ::

ሦስተኛ፤ ተከታትለው ሥልጣን የያዙት የደርግና የወያኔ አገዛዞች ናቸው፤ ሁለቱንም በእውቀትና በትምህርት ስንመዝናቸው ገለባ ናቸው፤ በዚህም አያበቃም፤ ዋናውና ክፉው ነገር ገለባነትን ባህልና ሥርዓት አድርገው በወጣቱ ላይ መጫናቸው ነው፤ ቀድሞውንም ደርግና ወያኔ መሠረታቸው ወጣቱ ነበር፤ የተማሩትና ለሥልጣን የጓጉት ወጣቶች ገና ያልተማሩትን ሠራዊታቸው አድርገው መንበሩ ላይ ለመውጣት ትግል ሲጀምሩ፤ መጀመሪያ በወታደሩ ቀጥሎም በወያኔ ተቀደሙ፤ የተሸነፉት እንደአጼ ኃይለ ሥላሴ ስደትን የሙጢኝ ብለዋል::

የዚህ የአደገኛ መክሸፍ ውጤት ኢትዮጵያን ወደኋላ እየገፋና ታሪክዋን እያደበዘዘ፣ኢትዮጵያዊነትን በመደፍጠጥና ሌላ ሌላውን ወደላይ በማውጣትና በማድመቅ የመክሸፉን ጉዞ እያፋጠነና እያጠናከረ ነው፤ ይህንን ማንም ለማመን እንደማይፈልግ ይገባኛል፤ ማመን የሚያስቸግርበትም ምክንያት ራስን ወደመውቀስና ወደንስሐ፣ ከግለሰብ ወደአገር ከጊዜያዊ ወደዘለቄታዊ፣ ከአፍአዊ ወደመሠረታዊ ለውጥ በቁርጠኛነት መሸጋገር ግዴታ ስለሚሆን ነው፤ የዘመናዊው መክሸፍ ምንጭ የሆነው አብዛኛው ከአርባ ዓመት በላይ ዕድሜ ያለውና የተማረ የሚባለው ትውልድ ስለንስሐ አያስብም፤በጥፋቱ ደንድኗል፤ እንዲያውም ለአገሩና ለወገኑ ከፍተኛ መስዋእት የከፈለ፣ ብዙ ሰማዕታትን ያፈራና ሳይሳካለት ቀርቶ ከፖሊቲካው መድረክ የተገፋ በመሆኑ እያላዘነ ታሪክን በተቃራኒው እያየ የሚኖር ለመምሰል ይሞክራል፤ ከአርባ ዓመታት በላይ የራሱን ውዳሴ እየደገመ የቆየ በመሆኑ ለመለወጥ የሚቸገር ትውልድ ነው::

ውሸት እውነትን አይወልድም፤ መጀመሪያ ሁኔታውን ለመረዳት የሚያስፈልጉ ጥያቄዎችን ሁሉ ለመጠየቅ የአእምሮና የመንፈስ ዝግጁነት ያስፈልጋል፤ ከሁሉም በላይ እውነትን መቀበል የሚያስከትለውን ድፍረት መቀበል ያሻል፤ ይህ ቀላል አይደለም፤ እውነትን ለመቀበል የሚያስቸግረው አንዱ ከባዱና ዋናው ስጋት ከኃላፊነት ጋር የተያያዘ ነው፤ በመክሸፉ ውስጥ የነበሩ ሁሉ

ኃላፊነትን ለመቀበልና ለምንጊዜም የመከሸፉን መንገድ ለመዝጋት መበረታታት ያስፈልጋቸዋል።

መከሸፍ ጠንካራ የአስተሳሰብ ባህል መሆኑን በአንድ አፍታ ለመገንዘብ በአዲስ አበባ በአንድ ሦስትና አራት መንገዶች በሚገናኙበት አካባቢ ፈንጠር ብሎ ቆሞ ለአሥር ደቂቃ ያህል የመኪና ነጂዎቹን አነዳድ በማስተዋል መከሻሸፍ ምን ያህል ጠልቆ የገባ ባሕርይ እንደሆነ ይታያል፤ መኪናዎቹን እያቆላለፉ ማንም እንዳይንቀሳቀስ ወይም ሁሉም ጭንቀት ውስጥ እንዲወድቅ መደራረግ ነጂዎች ሁሉ የተማሩት ሕግ ይመስላል፤ ዓላማው ወደፈለጉበት በፍጥነት ለመድረስ አይደለም፤ ዓላማው ሌላው ወደፈለገበት በፍጥነት እንዳይደርስ ለማድረግ ነው፤ በእንጻሩ ለምሳሌ አንዳንድ በጣም ጠቃሚ የሆኑ የእርሻ አሠራሮች በጭራሽ አይሰራጩም፤ በጅሩ የሚታየው የጥቁር አፈር እርሻ ከዚያው ከአካባቢው አያልፍም፤ በኮንሶና በየጁ የሚታዩ የመስኖ ሥራና የእርከን እርሻ ጥበብ ከዚያው ከአካባቢው አይወጡም፤ የአዲስ አበባውን ትራፊክ ሁኔታና እነዚህን የጠቀስኳቸውን የእርሻ ዘዴዎች አብራችሁ አስቡአቸው፤ ለምንድን ነው ጥሩውና ጠቃሚው ዘዴ በሰፊውና በፍጥነት የማይሰራጨው? በእንጻሩ ለምንድን ነው ጠቃሚ ያልሆነው አጉል እልህ በቶሎና በሰፊው የሚሰራጨው? እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች በጥሞና ቢያስባቸውና ቢፈታቸው መከሸፍ ከውስጣችን ይወጣል ብዬ አምናለሁ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ተመልሰው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በተተከለ ጊዜ የኢትዮጵያ አርበኞች በኩራትና በልበ-ሙሉነት የአገሩ ባለቤት የሆኑበት ሁኔታ የመጣ መስሎአቸው ነበር፤ ነገር ግን ሁኔታው ተለውጦ ስደተኞችና ባንዶች በአገሩ የበላይነትን እያገኙ መጡ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ገና ከሎንዶን ሳይነሡ አርበኞቹን ለመቆጣጠር እየሞከሩ ነበር፤ በእንግሊዞች እርዳታ ልዩ ልዩ ጽሑፎች ለአርበኞቹ በአውሮፕላን ይበተኑ ነበር፤ በሐምሌ 1/1932ዓ.ም፤ የሚከተለው ተበተነ፤–





...

*የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች*

*የእያንዳንዳችሁን ሙያ አውቀዋለሁ፤ ወደፊትም የምትሠሩትን ጀግንነት ሥራ ለማየት እናፍቃለሁ፤ አርበኞች በጀግንነታችሁ፣ ካህናቶችና ሽማግሌዎች ለሕዝባችን መልካም ምክር በመስጠት፣ ዘበኞች፣ ነጋዴዎች ሌሎችም ሠራተኞች ስላገራችሁ ጥቅም በሠራችሁ ብርቱ፤ ሁላችሁም የድካማችሁን ዋጋ ታገኛላችሁ።*[43]

የድካማችሁን ዋጋ ታገኛላችሁ የሚሉትን ሲያጠናክሩ በሌላ ቡተቢተን ወረቀት ‹‹እንግሊዞች ብዙ ገንዘብ ሰጥተውናል፤ ስለዚህ ወደፊት በኛ ምክንያት ጉዳት ለሚያገኘው ሁሉ ካሣውን እንሰጠዋለን።›› ይላሉ፤[44] በሌላ ወረቀት ደግሞ የሚከተለውን ትእዛዝ ለአርበኞች አስተላለፉ፤

*ለኢትዮጵያ አርበኞች*

*ከዳብሬ ማርቆስ ወይም ከያለበት ስለንጉሠ ነገሥቱና ሰንደቅ ዓላማው ክብር ስለአገሩም ፍቅር የሚወጣው በኢጣልያ ውስጥ የነበረ ባንዳ እየወጣ በመጣ ጊዜ እወደደበት አርበኛ ዘንድ እየገባ በየበኩልህ በመልካም እየተቀበልህ አቅርበው እንጂ እየተፋለምህ እንዳታጉላላው እንዳትገፈው ይሁን፤ እየገፈፍህ መንገድ እያሳጣህ ያስቸገርህ እንደሆነ ከትእዛዝ መውጣት ለጠላት መርዳት ሆኖ ይቆጠርብሃል።*

በዚህ ትእዛዝ ስደተኛው ንጉሠ ነገሥት የጦር መሪ መስለው የጠርነት ስልት ያስተላልፋሉ፤ ምናልባትም ሀሳቡ የሳቸው ሳይሆን የእንግሊዞች ይሆናል፤ በዚህም የተነሣ በአርበኛውና በባንዳው፣ በአርበኛውና በስደተኛው ማህል ልዩነት

[43] ደጃዝማች ከበደ ተሰማ፣ የታሪክ ማስታወሻ ፤ ገ. 455
[44] ዝኒ ከማሁ፣ ገ. 461

ጠፋ፤ እንዲያውም ጃንሆይ ደብረ ማርቆስ ገብተው የአርበኞችን ሰልፍ በሚመለከቱበት ጊዜ ድጃዝማች ከበደ የታዘቡት

**አርበኞች በጃንሆይ ፊት እየቀረቡ በባህላችን መሠረት ሲፎክሩና ሲሸልሉ ‹‹ከራስ ኃይሉ ጋር የነበረው ባንዳ ወታደር ማንንም ሳያስፈቅድ በሰልፉ ውስጥ ተቀላቅሎ እንደአርበኞችም ለመናገርና ጀብዱ ለመቁጠር በሥራው እያፈረ ቢቀርበትም ያለይሉኝታ በሰልፉ ተራ ገብቶ ሰልፍ ሲያሳይ ዋለ::[45]**

እንዲህ እንደ.ጋብቻ ቅልቅል ተጀምሮ የአርበኛው ውርደትና የባንዳ ክብር እያደገ መጣ፤ በአንድ በኩል አርበኞች አምስት ዓመታት በሙሉ በዱርና በገደል እየተንከራተቱ ሰንደቅ ዓላማቸውን ሳያሳጥፉ ሲዋጉና የመጨረሻውን መስዋእትነት ሲከፍሉ ቆይተዋል፤ የተዋጉለትና የሞቱለት ነጻነት ከተገኘ በኋላ ግን እነሱ ወደኋላ ተገፍተው በስደተኞችና በባንዶች መቀደማቸው አዲስ ሁኔታን ፈጠረ፤ ይህ ሁኔታ አርበኝነት መክሸፉን የሚያመለክት ነው፤ ከዚያም በላይ ባንዳነትና ስደተኛነት የሚያቀጣና የተሻለ ምርጫ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፤ አርበኝነት ከሸፎ ባንዳነትና ስደተኛነት ሲከበር የታሪክ መዘውር ተለወጠ ማለት ነው፤ የሚከተለው ትውልድ ከአርበኝነት ይልቅ ባንዳነትንና ስደተኛነትን ይመርጣል ማለት ነው፤ ዛሬ ይህንን እያየን ካልሆነ መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ የተሟላ መልእክት አልያዘም ማለት ነው፤ ይህንን ገሀድ ነገር ከዚህ በላይ ለማስረዳት አልሞክርም::

አንድ ፈረንጅ ስለማይጨው ዘመቻ በጻፈው ውስጥ አንድ አብቹ ስለሚባል የሰላሌ ጀግና ወጣት አንብቤ ከልቤ አልወጣ ብሎኛል፤ መረጃ ለማግኘት ሱሉልታ ተመላልሼ አልሆነልኝም፤ ጉልበት ካለቀ በኋላ ሆነና ... ከደጃዝማች አበራ ካሣ ጋር ማይጨው ዘምቶ የነበረው የሰላሌ ወጣት ‹‹ይቺ ልጅ›› በመባል ይታወቅ ነበር፤ አብቹ፤ ሊረሳ አይገባም፤ አንድ ሰው ታሪኩን ቆፍሮ ማውጣት አለበት::

[45] ደጃዝ. ከበደ ተሰማ፣ የታሪክ ማስታወሻ፣ ገ. 409.





ጃንሆይ በመጀመሪያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰጡት መመሪያዎች አንዱ በኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩ ፋሺስት ኢጣልያኖችና ባንዶች ላይ ምንም የበቀል እርምጃ እንዳይወሰድባቸው መከልከል ነበር፤ ይህን ትልቅ የመንፈስ ገናናነትን የሚያሳይ የምሕረትንና የይቅር ለእግዚአብሔር ባይነትን በበኩሌ እደግፈዋለሁ፤ ነገር ግን የአጼ ኃይለ ሥላሴ ዓላማ የመንፈስ ገናናነት ሳይሆን ሌላ እንደነበረ በግልጽ እየታየ መጣ፤ አርበኞችን በመፍራት ባንዳዎችንና ስደተኞችን በአጋርነት ለመያዝ እየተዘጋጁ ነበር፤ ነገር ግን የቂም እርምጃን መከልከል ፋሺስት ኢጣልያ ከፋሺስት የኢጣልያ ወታደሮችዋ ጋር ኢትዮጵያን መውረርዋንና በጋዝ ጭስ ጭምር የኢትዮጵያን ሕዝብ መጨፍጨፍዋን አይፍቀውም፤ ለኢጣልያ የገበሩና አሽከርነት ያደሩ ወገኖች ባንዶች ሆነው በወገኖቻቸውና በአገራቸው ላይ የፈጸሙዋቸውን አስነዋሪ፣ አሳፋሪና ጎጂ ድርጊቶች ይቅርታ አይፍቀውም፤ ንስሐ ባልገቡበት ወንጀል ይቅርታ ከየት ይመጣል?

አጼ ኃይለ ሥላሴ በአርበኝነት ክብርና ኩራት፣ በበስደተኞች እፍረትና በባንዳዎች ውርደት መሀከል ያለውን ልዩነት ወደፖሊቲካ መሣሪያነት ለወጡት፤ ቁስል ያለባቸውን ስደተኞችና ባንዶች ዋና ባለሟሎችና መሣሪያዎች በማድረግ የአርበኞችን ኩራት ለማስተንፈስና ልበ-ሙሉነታቸውን ለመደምሰስ ቻሉ::

የአጼ ኃይለ ሥላሴን መሰደድ ብዙ መኳንንት አልወደዱትም ነበርና ስደት ለሳቸው ቁስል ነበር፤ እንደደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ያሉ ከጊዜያቸው ቀድመው የተራመዱ ነበሩና ከእነዚህ ለመከላከል አጼ ኃይለ ሥላሴ ከባንዶች ጋር መጎደን ሳያስፈልጋቸው አልቀረም ይሆናል፤ ባንዶች ለኢጣልያ አሽከሮች በመሆናቸው ያገኙት ሥልጠናም እንደሚያገለግላቸው ሳይገምቱ አልቀሩም ይሆናል፤ ለማናቸውም አጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥታቸውን በባንዶችና በስደተኞች ሞሉት፤ ለዚህ ነው ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት የሚከተለውን ያሉት፡—

***ሌሎች ቀድሞ ከነበሩበት በጣም መቅረባቸውንና ተደማጭ መሆናቸውን ቲምልክቺ ሳልገረም አልቀረሁም፤***

*ከእነሱም መካከል ለምሳሌ አቶ ዓምደ ሚካኤል ደሳለኝ፣ አቶ ለማ ወልደ ገብርኤል አቶ ተፈሪ ሻረው፣ አቶ ከበደ ሚካኤል፤ አቶ አድማሱ ረታ፤ አቶ ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅ፤ ብላታ ዳዊት ዕቁበ እግዚእ*፣ ደጃዝማች አስፍሃ ወልደ ሚካኤል*፣ ጄኔራል መኮንን ደነቀና ሹሉቃ አሰፋ ለማ በጣም ተጠሪዎችና ተደማጮች በመሆን እሰን እሰን ሲሉ በማየቴ እጅግ ተገሬምሁ፤ የተገረምኩትም እነዚህ ሰዎች ሁሉም የጣልያን አገልጋዮችና ታማኞች ነበሩ ‹ባንዳ› የሚል ቅጽል ከህዝብና በተለይም ከአርበኞችና ከስደተኞች የተሰጣቸው ሰዎች በመሆናቸው ነው፤ ... ይህንን ሁሉ ሳይ ከመገረም አልፎ ከማቅለሽለሽ አደረሰኝ::* [46]

ልብ በሉ፤ ደጃዝማች ግርማቸው አርበኛ አልነበሩም፤ እሳቸውን ያቅለሸለሻቸው ነገር አርበኞቹን ምን አድርጓቸው ይሆን? ስለአርበኞች፣ ስለስደተኞችና ስለባንዶች በምናስብበት ጊዜ ቁም ነገሩ ያለው በግለሰቦች ላይ አይደለም፤ ዋናው ትኩረታችን አርበኝነትም ሆነ ስደተኛነት፣ ወይም ባንዳነት እንደባህል ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፈው እንዴት ነው? የእያንዳንዱ ታሪክ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፈው ጥቅሙንና ጉዳቱን፣ ክብሩንና ውርደቱን እየለዩ ነው? ወይስ በአንድ ዓይነት መልክ ነው? የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ተብሎ ለሚቀጥሉት ትውልዶች የሚተላለፈውስ በምን መልክ ነው? እንግዲህ የታሪክ ዋናው ትምህርት የአለፉት ትውልዶች የሠሩትን ስሕተት እንዳይደገም ለመከላከል ነው::

አጼ ኃይለ ሥላሴ ባንዳነትን እንዳከበሩት ሁሉ እንደሚመስለኝ የስደትን ውርደት ወደክብር የለወጡት የደርግና የወያኔ አገዛዞች ናቸው፤ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ

46 የደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት የሕይወት ታሪክ፣ ያልታተመ፤ እንደሚመስለኝ ዘመዶቻቸው ደጃዝማች የጻፉትን እውነት ፈርተው ገና አላሳተሙትም፤ በስማቸው ላይ ምልክት ያደረግሁባቸው የኤርትራ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ ብላታ ዳዊት ቀደም ብለው ከኮሎሬንዞ ታእዛዝና ኤፍሬም ተወልደ መድኅን ጋር ኢጣልያን ከድተው ወደኢትዮጵያ የመጡ ይመስለኛል::





ለትምህርት በገፍ ወደአሜሪካ የሄደው የእኔ ትውልድ ነው፤ እንደምገምተው ዓላማው በአንድ ጊዜ በየመስኩ ብቁ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን አፍርቶ አገሪቱን ወደእድገት ጎዳና ለመግፋት ነበረ፤ በአንዳንድ ቀልጭ መሥሪያ ቤቶች ሲታይ ዓላማው ተሳክቶ ነበር ለማለት ይቻላል፤ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ በኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን፣ በኢትዮጵያ ዓየር መንገድ፣ በኢትዮጵያ መብራት ኃይልና በኢትዮጵያ ባንኮች የታየው እመርታ የሚያስደንቅ ነበር፤ በአፍሪካ ውስጥ በብዙ መስኮች ኢትዮጵያ ቀድማ ስለነበረ ከብዙ የአፍሪካ አገሮች ለተለያዩ ትምህርቶችና ሥልጠናዎች ወደኢትዮጵያ ይመጡ ነበር፤ ብዙዎቹም በአገራቸው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትርት ጀምሮ አስከአምባሳደርና የተለያየ ሚኒስትርነት ደረጃ ደርሰው ነበር፤ በዓየር መንገዱ በኩል ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ያደረገችው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው::

## የውርደት አፋፍ

እስቲ የመጨረሻውንና ዋናውን፣ የኢትዮጵያን ታሪክ የውርደት ጥላሸት የቀባውን የቅርቡን ሁኔታችንን እናስታውስ፤ በ1928 ኢጣልያ እኛ በማናውቀው መንገድ በሰማይ በአውሮጵላን መጥታ፣ እኛ በማናውቀው የጋዝ መርዝ የኢትዮጵያውያንን አካል እያነፈረችና እያስለቀሰች ሠራዊቱን ከጥቅም ውጭ አደረገችው፤ በጦር መሀል ገብቶ ዮሐንስ በመቶማ አንገቱን በተቀላበት አገር፣ ቴዎድሮስ እጁን

አልሰጥም ብሎ በእጁ በወደቀበት አገር፣ አጼ ኃይለ ሥላሴ መትረየስ ሲተኩሱ ፎተግራፍ ተነሥተው ወደአውሮፓ አመሩ፤ ጦርነቱን ወደዲፕሎማሲ ለመለወጥ የቃጡት ሙከራ ለሽሽት ሰበብ ሆናቸው፤ ይህ ሰበብ ዛሬም ለብዙዎች እያገለገለ ነው፤ ኢትዮጵያ አውራዋ የከዳት አገር ሆነች፤ ለኢጣልያ በሩ ክፍት ቢሆንላትም ሰተት ብላ አልገባችም፤ ይሁን እንጂ ይህንን ተከትሎ የኢጣልያ ወታደሮች ኢትዮጵያውያንን በእርግጫ እያሉ ለብዙ ሺህ ዓመታት በውስጣቸው ሲጋገር የቆየውን ኩራታቸውንና

ክብራቸውን ከውስጣቸው አንጠፍጥፈው አስወጡባቸው፤ በሎሌዎቻቸውና በሰላዮቻቸው አማካይነት ኢትዮጵያውያንን ትጥቅ ለማስፈታት የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ፤ ኢትዮጵያውያን እንዲህም ተዋርደው የዘርዓይ ደረስንና የአብዲሳ አጋን ነፍስ ይማርና የኢትዮጵያንና የኢጣልያን ጦርነት ለኢጣልያም ምድር አድርሰውታል![47]

እነዚህ ሁለት ኢትዮጵያውያን በሰው አገር፣ በሰው ምድር ለአገራቸውና ለወገናቸው የነበራቸው ፍቅር አላስችላቸው ብሎ በኢጣልያን አገር አርበኛነታቸውን አሳዩ፤ ሌላው በአገሩ ባንዳ ሲሆን እነዚህ ጀግኖች በሰው አገር አርበኝነታቸውን አስመሰከሩ፤ የዘመኑ ትውልድ የእነዚህን
ጀግኖች ስም ያውቃል? ለምን? ባንዳ በሠለጠነበት አገር የአርበኛን ስም ማን ያነሣል? ዘርዓይ ደረስ ለኢትዮጵያ ክብር በሮማ ተጋድሎ ዛሬ ኢትዮጵያ አገሩ አይደለችም፤ ለኢትዮጵያ ብሎ፣ የራስ አሉላን ጎራዴ ይዞ በሮማ ከተማ የተጋደለው ዘርዓይ ደረስ ዛሬ የኤርትራ ተወላጅ በመሆኑ ብቻ የኢትዮጵያ ጠላት፣ የትግራይ ጠላት የሚለው አይጠፋም፤ በዘመነ ግርምቢጥ ታሪክ ሲከሽፍ ባለቤቱ ባዳ፣ ባዳው ባለቤት ይሆናል።

የአብዲሳ አጋንም ከኢትዮጵያ ታሪክ ሊፍቁት የሚፈልጉ አይጠፉም፤ አብዲሳ በሕይወት ቆይቶ በኢጣልያ ተራሮች ላይ ያደረገው የአርበኝነት ተጋድሎ የሚገባውን ዋጋና ክብር እንዳላስገኘለት ለመረዳት የቻለ ይመስለኛል፤ በባንዳ ስር ሆኖ በእንጋችነት ሲሠራ ነበር፤ ለማ?

ሌላም ሰው አለ፤ አቋ ሰለባ የሚባል የኢጣልያ ባንዳ ሠራዊት ውስጥ ሲሠራ የቆየ ሰው በድብቅ እንደሰው ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ የሆኑ ሃያ ዘጠኝ ባንዶችን አስተባብሮ 13 500 ጠመንጃ፣ አምስት መድፎች፣ ሠላሳ አልፓይን መድፎች፣ አሥራ

[47] እዚህ ላይ ደጃዝማች የማነ ሐሰንን ማንሣት አለብኝ፤ አርበኛ ነበሩ፤ በኢጋጣሚ ተዋወቅቸውና ታሪካቸውን ስሰማ ወደድኳቸው፤ ለኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉልኝ ጠየቅኋቸው፤ መልሳቸው የሚያስደንቅ ነበር፤ «ወዳጄ መሰለኸኝ! ምን በደልሁህ! እንዲያውም እኔ አርበኛ አይደለሁም! እረፈው!» እንደሚኮሩበት የማውቀውን ታሪካቸውን እንዲክዱት ያደረጋቸው በአርበኞች ላይ የነበረውን ጫና የሚያመለክት ነበር።





ሁለት ረጃጅም መድፎች፣ ይዘው በሌሊት ተጉዘው መቀሌ ገቡና እጅ ሰጡ፤ አዲስ አበባ ሲደርሱም ከደጃዝማቾች በየነ መርዕድ ጋር፤ ቀጥሎም ከራስ ደስታ ጦር ጋር ተደባለቁ፤ በኋላም ትግሉን በሲዳሞ ውስጥ ቀጥሎ በክብረ መንግሥት በተደረገ ጦርነት ላይ አቋ ሰለባ ሞተ።[48]

አርበኛነት ዋጋ አጥቶ የፈረንጅ አሽከርነት አስከበረ፤ በዚህም የተነሣ በ1933 ዓ.ም. በኢትዮጵያውያን ነፍስ ውስጥ ሠርጾ የገባ የፈረንጅ አምላኪነት ተጀመረ፤[49] በአፍጢሙ የተደፋው ኩራትና ክብር እስከዛሬም ቀና የሚያደርገውን ትውልድ ሆነ መሪ አላገኘም፤ መጥፎ ዓይነት መክሸፍ ብቻ ሳይሆን መክሸፍን የሚያመርት ኃይል ከውስጣችን ይፈልቅ ጀመር።

እንዴት የኢትዮጵያውያን ኩራትና ክብር በአፍጢሙ እንደተደፋ በትክክልና በዝርዝር ለማወቅና ለማሳወቅ የሚፈልጉ የአእምሮ ሰዎች ለመሆን ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች ሁሉ በጃቸው ሁሉ በደጃቸው ነው፤ አዲስ ዘመንንና ‹‹ኢትዮፒያን ሄራልድ›› ጋዜጦችን ይዘው፣ ፕሮፓጋንዳውን ትተው ሁነቶችን ብቻ እየነቀሱ አውጥተው፣ ሌሎች ምንጮችን ማመሳከሪያ እያደረጉ በተለያዩ መስኮች -- በትምህርት፣ በልማት ተቋሞች፣ በጦር ኃይሎች፣ በውጭ ጉዳይ፣ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ የነበራትን ደረጃ -- በትክክል ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አልጠራጠርም፤ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያውያን የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን ፍላጎት ስላልነበራቸው ጥቂት አርመኖችና ግሪኮች በኢትዮጵያ ድርሻ ይጠቀሙ ነበር፤ የትም አገር ለመሄድ ለኢትዮጵያውያን በሩ ክፍት ነበር፤ በአንዳንድ አገሮች ኢትዮጵያውያን ቪዛም አያስፈልጋቸውም ነበር።

ከወያኔ በፊት የኢትዮጵያ ህልውና ያጋጠመው መራር ፈተና በፋሺስት ወረራ ነበር፤ በዚያን ጊዜ የተደረገውን የአርበኝነት

[48] ጳውሎስ ኞኞ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት፣ 1980፣ አዲስ አበባ።

[49] ይህ ማጋነን አይደለም፤ ወጣቶችን ለማሠልጠን ኀሐ ጽዮን ሄጄ የወረዳ ገዢው ኃላፊው ማነው ብለው ሲጠይቁ እኔ መሆኔን ስነግራቸው «ጥጋበኛ ፈረንጁ እያለ አንተ አለቃ ነኝ ትላለህ!» ብለው ፖሊሱ እንዲያስረኝ አዘዙ፤ በበነጋታው ለኮሎኔል ወርቅነህ ዝበየሁ ደውዬ ተፈታሁ፤ ሰውዬውም በወረዳው ላይ ብዙም አልቆዩም።

ቅድመ አባቶቻችንና እናቶቻችን ለአገራቸውና ለወገናቸው፣ ለራሳቸውም የነበራቸውን ክብር በሚገባ ያሳየናል፤ የኢጣልያንን የጦር መሣሪያ፣ ከመድፍና መትረየስ ጀምሮ እስከታንክና አውሮጵላን አስልፈው፣ አግረኛውንና ፈረሰኛውን ባንዳ አሠልጥነው በኢትዮጵያ ላይ ጊዜያዊ የበላይነትን ተቀዳጅተው ብዙዎቹን የኢትዮጵያ ክፍሎች ተቆጣጠሩ፤ በዚያን ጊዜ ወኔ የከዳቸውና የራሳቸውንና የወገናቸውን ክብር ለፋሺስት ኢጣሊያ ያነጠፉ የሚከተለውን ሲዘምሩ

*በሰማይ ሲበሩ ነፋስ አይነካቸው፤*
*በመንገድ ሲሄዱ እንቅፋት የላቸው፤*
*በባሕር ቢሄዱ ማዕበል አይነካቸው፤*
*ከክርስቶስ በታች ከኛ በላይ ናቸው፤*
*እንዲህ አድርጎ ነው እምላክ የሰጣቸው።*[50]

አንበገርም ያሉት ከነክብራቸው ለንደቅ ዓላማቸውን ይዘው የአገራቸውን ህልውና በዱርና በገደሉ እየተጋደሉ ያስከብሩ ነበር፤ የእነዚህን ኢትዮጵያውያን አርበኞች ታሪክ በሙሉ መልኩ የሚጽፍላቸው መንግሥት ገና አልመጣም፤ ከዚህ በታች የማቀርበው መረጃ ከኢጣልያኖች የተገኘ ነው።

እጨ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ተመልሰው ዙፋናቸው ላይ ከወጡ በኋላ ከሰሜን ክፍለ-ሀገሮች በትግራይና በጎጃም ላይ የተለየ ቂም አላቸው እየተባለ ይወራ ነበር፤ ይህ ወሬ መጣራት ያለበት ነው፤ ግን ይህንን ወሬ ተከትሎም በሁለቱ ክፍለ-ሀገሮች የነበረው የልማት ምልክት በጣም ዝቅተኛ ነበር፤ ለብዙ ዓመታት ከአዲስ አበባ ወደጎጃም መመላለሻ ያለው ቦሮ በወሉ፤ በትግራይና በጎንደር በክፉ ነበር፤ በትምህርት ቤትም ቢሆን በጎጃምና በትግራይ ሁኔታው ዝቅተኛ ነበር፤ በዚህ ጉዳይ ላይ በዘመኑ እኔም ጽፌበታለሁ፤ የትግራይ መዳፊን እጨ ኃይለ ሥላሴ በ1934 ግድም በትግራይ ከገጠማቸው ትግል ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፤ በጎጃም ደግሞ ከአርበኞቹ ጥንካሬና ከነበላይ ዘለቀ ተቃዋሚነት

50 ዝኒ ከማሁ፣ ገ. 4





ጋር ይያያዛል ለማለት የሚቻል ይመስለኛል፤ በተጨማሪም በሁለቱም ክፍለ ሀገሮች ዋናዎቹ ራስ ሥዩምና ራስ ኃይሉ ባንዳዎች ስለነበሩ ሊሆን ይችላል፤ እነዚህ ጉዳዮች ጥናት የሚያስፈልጋቸው ናቸው።

በ1937 በላይ ዘለቀ ተሰቀለ
በ1953 ራስ አበበ አረጋይ ተረሸኑ
በ1967 ራስ መስፍን ስለሺ ተረሸኑ
ለናሙና ያህል እንጂ የገደልናቸው ብዙ ናቸው!
ሐውልት እንዳንሠራላቸው እንገድላቸዋለን!

በየጦር ሜዳው ላይ ያለቀባሪ የቀሩት፣ ጀብና አሞራ የበላቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች ልጆችዋ ድምጽ ተራሮችዋን እያርበደበደ፣ ወንዞችዋን እያስጋለበ፣ «ብድር መልሱ! ዕዳ ክፈሉ!» እያለ በዓለም በሙሉ ያስተጋባል፤ እነዚህ የኢትዮጵያ ጀግኖች ለኢትዮጵያ አፈር ማዳበሪያ ሆነው በሞታቸውም ሲመግቡን ቆይተዋል፤ በሕይወታቸው ክብርና ኩራት፣ በሞታቸው ሕይወት የለገሱንን የአባቶቻችንንና የእናቶቻችንን ድምጽ ማዳመጥና ከመንፈሳቸው መታረቅ አለብን፤ ውቃቢ የራቀው ትውልድ ከመሆን ለመዳን!